# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል


አዘጋጆች

ትጃኒ ምትኩ

መላኩ ጽጌ

አርታኢ

ግሩም ጥበቡ

የጥራት ተቆጣጣሪዎች

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

ግራፊክስ

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የስዕሎችን የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


መግቢያ.................... iv

ምእራፍ አንድ .................... 1

ተፈጥሮን ማድነቅ.................... 1

ምዕራፍ ሁለት .................... 13

የቤተሰብ ምጣኔ .................... 13

ምእራፍ ሶስት.................... 22

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት .................... 22

ምእራፍ አራት .................... 33

የታዋቂ ግለሰቦች ህይወት ታሪክ.................... 33

ምዕራፍ አምስት .................... 47

ውሃና ጠቀሜታው.................... 47

ምእራፍ ስድስት .................... 57

የሰዎች ዝውውር .................... 57

ምእራፍ ሰባት.................... 68

ማህበራዊ ግንኙነት.................... 68

ምእራፍ ስምንት.................... 78

ሱሰኝነት .................... 78

ምእራፍ ዘጠኝ.................... 90

አርበኝነት .................... 90

ምእራፍ አስር.................... 101

ቃላዊ ግጥም .................... 101

ሙዳየ ቃላትና ሀረጋት.................... 115

ዋቢዎች.................... 117

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀውን የተማሪ መፅሐፍ መሠረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች እንዴት ማስተማርና ተግባራቱን እና መልመጃዎቹን እንዴት ማሠራት እንደሚገባ ሁሉአቀፍ የሆነ ጥቆማ ለመምህር ያቀርባል። ከዚህም ሌላ የክፍል አደረጃጀትና አስተዳደሩ ምን መሆን እንደሚገባው አቅጣጫ ያስቀምጣል። በዚህም መምህራን የየክፍላቸውንና የየተማሪዎቻቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መምሪያውን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል።

## የመምሪያው አደረጃጀትና ይዘት

ይህ የመምህር መምሪያ ከላይ እንደተገለፀው የተማሪ መጽሐፍን በመንተራስ የተዘጋጀ በመሆኑ የይዘት አደረጃጀቱም ይህንኑ የተከተለ ነው። ስለሆነም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። በየምዕራፉ ለሚከናወኑ የማዳመጥ ተግባራት የተዘጋጁት ምንባቦችም በመምህር መምሪያው ተካተዋል። አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው በታሰቡ ይዘቶች ላይም ተጨማሪ ማስታወሻዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በየደረጃው ለቀረቡ መልመጃዎችም ናሙና መልሶች እንዲካተቱ ሆኗል። እነዚህ ናሙና መልሶች የቀረቡትም በቋንቋ ትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ መምህርና ተማሪዎቹ እንደየሁኔታው (አውዱ) የሚያቀርቧቸው ተጨማሪ ምላሾችም ከግምት የሚገቡ ናቸው።

## ልዩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች

- ✓ የየትኛውም ክፍለ ጊዜ ትምህርት ሲቀርብ አራቱን የቋንቋ መሠረታዊ ክሂሎች በተመጣጠነና በተቀናጀ መልኩ ያካተተ ሊሆን ይገባል፤
- ✓ የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊ፣ ትብብራዊ እና ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ መርህን የተከተለ ሊሆን ይገባል (ለምሳሌ ተማሪን ማዕከል ያደረገ መሆን)፤
- ✓ የልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ አካሄድ ሁልጊዜም ይተግበር፤ በተለይ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ እና መልመጃ ሲቀርብ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፤
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች ከተመሳሳይ ዳራ ያልመጡ ወይም ተመሳሳይ ልምድ የሌላቸው ስለሚሆን በመማር ወቅት የሚቸገሩ ተማሪዎችን ቀስ በቀስ የማብቃት ስልትን (scaffolding) በመተግበር ማገዝ ያስፈልጋል፤

- ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችና ላቅ ያለ አፈፃፀም የሚያሳዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙንም ችሎታዎቻቸውን ለማዝለቅ ማበረታትና ተጨማሪ ተግባራትን እያዘጋጁን በመምጣት ማትጋት ይገባል፤
- በክፍል ተሳትፎ ወቅት ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን መከተል ይገባል (የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፆታ ወዘተ አካታችነትን ከግምት ማስገባት)
- ተማሪዎቹ በሚማሩበት አካባቢ በሌላ መልኩ የሚተረጎም ቃል ወይም አገላለፅ ወይም ምስል ሲያጋጥም (ታቡ የሆነ) በሌላ መተካት/ማለዘብ
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የአካቶ ትምህርትን መርህ በመከተል ተገቢ እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡

# ምእራፍ አንድ

## ተፈጥሮን ማድነቅ

(ክፍለጊዜ ዘጠኝ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ፡-**

- ምንባቡን በማድመጥ የተገነዘቡትን ቁም ነገር ይናገራሉ፡፡
- የተፈጥሮ ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- የተለያዩ የተፈጥሮ ገጽታዎችን ያደንቃሉ፡፡
- ቋንቋን በተለመዱ ሁኔታዎች ይጠቀማሉ፡፡
- በተለመዱ የቋንቋ አገላለጾች አማካኝነት አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅሮችን ይገልጻሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የማዳመጥ ክንውን ደረጃዎችን ማሰራት
- የሚነበበውን ጽሁፍ ማዳመጥ
- የጓደኞቻቸውን ሀሳብ ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- ተፈጥሮን ለማድነቅ በተገቢው ቋንቋ መጠቀም
- በተሰጠው ርእስ ላይ መወያየት
- ተፈጥሮን በተመለከተ በንግግር ማቅረብ

### 2.3 ማንበብ

- የማንበብ ክንውን ደረጃዎችን ማሰራት

### 2.4 መጻፍ

- አንቀጽ መጻፍ
- ተዘበራርቀው የተቀመጡትን አስተካክሎ አንቀጽ መጻፍ

- የተፈጥሮ መስህብ ላይ በመመስረት አንቀጽ መጻፍ

2.5 ቃላት

- የቃላትን ምንነት
- የተዘውታሪ ቃላት ምንነት
- በቢጋር ሰንጠረዥ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን መሙላት
- በተዘውታሪ ቃላት ዓረፍተነገር መመስረት
- ተዘውታሪ ቃላት ተጠቅሞ የመተዋወቅ ተግባር ማከናወን

2.6 ሰዋስው

- የአፍመፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅሮች
- ዓረፍተነገሮችን እንደገና ማዋቀር
- የዓረፍተነገር ዋናዋና ተዋቃሪ አካላት መለየት

3 ማስተማሪያ ዘዴ

- የቀረበውን ምስል በማየት የቀደመእውቀታቸውን መቀስቀስ
- የጽሁፉን ርእስ በማስተዋወቅ ለተማሪዎች ማንበብ
- የማዳመጥ ክንውን መተግበር
- የቀረበውን ምስል መሰረት በማድረግ የተረዱትን እንዲናገሩ ማድረግ
- ስለብሄራዊ ፓርኮች የቀደመእውቀታቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት
- ምንባቡን እንዲያነቡ በማድረግ የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ
- የአንቀጽን ምንነት በምሳሌ ማቅረብና ተማሪዎችም እንዲጽፉ ማድረግ
- ልምዳቸውን በመጠቀም አንቀጽ እንዲጽፉ ማበረታታት
- ለአንብቦ መረዳት የሚያገለግሉ መልመጃዎችን ምሳሌ በመስጠት እንዲሰሩ ማበረታታት
- በቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ምሳሌ በመስጠት ማበረታት
- የዓረፍተ ነገር ዋና ዋና ተዋቃሪ አካላት እንዲገልጹ ማድረግ
- ዓረፍተ ነገር ሲዋቀር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አስማምተው እንዲጽፉ ማበረታት

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. "የወንጪ ሀይቅ" በሚል ርእስ ምንባቡን ለተማሪዎች ከማንበብዎ በፊት የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ ከ1-2 የቀረቡትን ጥያቄዎች ማቅረብና ምላሽ እንዲሰጡ ማበረታታት፡፡

- የቀረበውን ምስል በማየት የሚያውቁትን መረጃዎች ሲናገሩ መቀበል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል የሚያውቁትን ሀይቆች ስም እንዲዘረዝሩ ማድረግ

ይህንን ተግባር ተማሪዎች ካከናወኑ በኋላ "የወንጪ ሀይቅ" የሚለውን ጽሁፍ ለተማሪዎች ማንበብ፡፡ ተማሪዎች በትኩረት እንዲያዳምጡ ያበረታቷቸው፡፡

## የወንጪ ሀይቅ

ወንጪ በተፈጥሮ ሀብቱ የታደለ ከጎብኝዎች አይን ያልተለየ ነው፡፡ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከሚጎበኙ መስህቦች ተጠቃሽ ሲሆን መስመርዎን ከአዲስ አበባ ወደ አምቦ ሲያደርጉ ከጊንጪ ከተማ በስተግራ በሚገኘው የጠጠር መንገድ ላይ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ከተጓዙ በኋላ ያገኛሉ፡፡ ወንጪ ሀይቅ በእሳተ ገሞራ የተፈጠረና ከባህር ጠለል በላይ በ3386 ሜትር ከፍታ ላይ በደንና በተራሮች ተከቦ ይገኛል፡፡ በአመዛኙ ደጋ የአየር ንብረት ያለው ሲሆን በአገራችን እሳተ ገሞራ ወለድ ከሆኑ ሀይቆች መሀከል እጅግ ማራኪው የወንጪ ሀይቅ አንዱ ነው፡፡ ሀይቁ 560 ሄክታር የሚሸፍን ሲሆን ከ 9 እስከ 68 ሜትር ጥልቀት እንዳለው መረጃዎች ይጠቅሳሉ፡፡

ሀይቁ ከረጋው ሰማያዊ ውበቱ በተጨማሪ በውስጡ የታሪክ ባለቤት የሆኑ ሶስት ደሴቶች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ውስጥ ገዳማትም አሉ፡፡ ዛሬ ላይ በፋብሪካ እየተመረቱና በእሽግ መጠጦች ውስጥ የሚገኘውና ካርበን የተሰኘውን ማእድን በተፈጥሮ የምናጣጥምበት የምንጭ ውሃም በዚሁ በወንጪ ሀይቅ አካባቢ ነው የሚገኘው፡፡ በተጨማሪም ለተለያዩ አካላዊ ህመሞች ፈውስነቱ የሚነገርለት ተፈጥሯዊ ፏፏቴም በወንጪ ሀይቅ አከባቢ የሚገኝ ሀብት ነው፡፡

መምህር ምንባብዎን እዚህ ጋር ቆም በማድረግ ለማዳመጥ ተግባር የሚውሉ የቀረቡትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያቅርቡ፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እስካሁን ሲነበብ ባዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የወንጪ ሀይቅ መገኛ ቦታ የት ነው?
2. የወንጪ ሀይቅ የተፈጠረው እንዴት ነው?
3. የወንጪ ሀይቅ የሚገኝበት ቦታ አየር ንብረት ምን አይነት ነው?
4. ሀይቁ በውስጡ ስንት ደሴቶችን ይዟል?

በደን የተከበበውና በእንሰት ምርት ልማት የተዋበው ይህ የተፈጥሮ ሀብት ያማረ ፏፏቴ፣ ፍል ውሃ፣ የአሳ ሀብትና የቱሪዝም መዳረሻ የሆኑ ተፈጥሯዊ ሀብቶች የያዘ ውብ ስፍራ ነው፡፡

በጣሊያን ሀገር ተመራጭ የሆነው የአካባቢው የማር ምርት፣ በኢኮ ቱሪዝም ዘርፍ የጎላ ድርሻ ያለው ተፈጥሯዊ ሀብትና በስፍራው የሚገኙት አእዋፍት በስፍራው የሚገኘውን የረጋ ሀይቅ የከበቡት መስህቦች ናቸው፡፡ በዚህ ተፈጥሯዊ ሀብቱም ለሀገር ገቢ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

*(ከኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጥር 10/2010 ከቀረበው መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የቀረበ)*

## የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ተማሪዎች ከተራ ቁጥር 1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ እንዲመልሱ ይርዷቸው፡፡ ከተማሪዎች የሚጠበቀው መልስም ለናሙናነት ለጥያቄ ቁጥር አንድ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

“ዛሬ ላይ በፋብሪካ እየተመረቱና በእሽግ መጠጦች ውስጥ የሚገኘውና ካርበን የተሰኘውን ማእድን በተፈጥሮ የያዘ የምንጭ ውሃ ነው፡፡” ተማሪዎች ጽሁፉን በተመለከተ ያገኙትን መረጃ አሳጥረው ሲያቀርቡ ሀሳባቸውን በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ተማሪዎች ከተራ ቁጥር 1-2 በቀረቡት ነጥቦች ላይ በጽሁፍ ዘገባ አዘጋጅተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ጽሁፉን ሲያቀርቡ ከተሰጣቸው ርእሰጉዳይ ውጭ እንዳያቀርቡ መከታተልና ተገቢውን ግብረመልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

*መምህር ከተራ ቁጥር 1-2 ለውይይት የቀረቡትን ነጥቦች በማቅረብ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች በቀረቡት ነጥቦች ላይ ሲወያዩ እየዞሩ በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎች ሲወያዩ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መመሪያ ይስጧቸው፡፡ ለምሳሌ ከተወያዩ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ ይስጧቸው፡፡ ከተማሪዎች የሚቀርበውን መልስ በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በምን ጊዜ ተወያይተው መልስ እንደሚሰጡም መጠቆም አይዘንጉ፡፡*

### ተግባር ሁለት

*በዚህ ስር 1-3 ለቀረቡት መወያያ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቀረበው ቅደም ተከተል መሰረት ከጓደኞቻቸው ጋር በመነጋገር በሚከተለው መልኩ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡*

1. *በአከባቢያቸው የሚገኙ ማራኪ ቦታዎችን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡*
2. *ቦታዎቹ ማራኪ እንዲሆኑ ያደረጓቸውን ምክንያቶች እንዲያስረዱ ይዘዟቸው፡፡*
3. *ማራኪ ስፍራዎችን የመጎብኘት ልምድን ለማዳበር የሚረዱ ሀሳቦችን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ ለተማሪዎች ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡*

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

የቀረበውን ምስል አይተው ከሀገራችን ፓርኮች የትኛው እንደሆነ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ ባሌ ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ የሚለውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት የብሄራዊ ፓርክ ምንነት፣ በአገራችን ከሚገኙ ፓርኮች የሚያውቁትን እንዲናገሩ፣ አንድ ፓርክ በውስጡ ምን ምን ነገሮችን ሊይዝ እንደሚችል እንዲናገሩ በማድረግ የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ምንባቡን እያነበቡ እያለ በመሀል ቆም በማለት እስካሁን ያነበቧቸውን ሀሳቦች ምንያህል እንደተገነዘቡ በምንባቡ መሀል ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ ጥያቄዎቹ የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ መስጠት፡፡

1. የባሌ ብሄራዊ ፓርክ መገኛ ቦታ የት ነው?
2. የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ምን አስገራሚ ነገሮች አሉት?
3. ቀጣዩ የምንባቡ ክፍል ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል?

**ክፍለጊዜ አራት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ከምንባቡ ለወጡ ቃላት በ ሀ ስር ለቀረቡት ቃላት ፍችያቸውን ከ ለ ስር መርጠው እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ሐ. በዚህ ስር ተማሪዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ከ1-3 ለቀረቡት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ ለሚሰጡት መልስም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### ተግባር ሶስት

የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ ስለአንቀጽ ምንነት ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ ማድረግ፤ ተማሪዎቹ በሚወያዩበት ወቅት እየዞሩ ተማሪዎችን መከታተል ያስፈልጋል፡፡ በክትትልዎ ጊዜ የቀደመ እውቀታቸው ጥሩ ለሆነ ተማሪዎች የበለጠ የቀደመ እውቀታቸው እንዲሰፋ ተጨማሪ መወያያ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡

ለምሳሌ፡ በአንቀጽ ውስጥ የሚተላለፈውን ሀሳብ አጠቃሎ የሚይዝ ምን ይባላል?

ስለአንቀጽ የቀደመ እውቀታቸው ደከም ያለ ተማሪዎች ሲያጋጥሙን መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠል ስለአንቀጽ አጻጻፍ የቀረበውን ማስታወሻ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ አንቀጽን በተመለከተ ከቀረበው ማስታወሻ ላይ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ እርስዎም ተጨማሪ አንቀጾችን በማቅረብ ስለአንቀጽ ግንባታ ያለማምዷቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

### መልመጃ ሶስት

ተዘበራርቀው የተቀመጡ ዓረፍተ ነገሮችን እንደገና አስተካክለው አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ ዓረፍተ ነገሮቹን አስተካክለው አንቀጽ በሚጽፉበት ሂደት፣ የአንቀጹን ሀይለቃልና ዝርዝር ዓረፍተነገሮችን መለየታቸውን ይከታተሏቸው፡፡ ከቀረቡት ዓረፍተነገሮች “ፋጡማ ሁልጊዜ ሳይረፍድባት መማሪያ ክፍል ትገኛለች፡፡” የሚለው ዓረፍተ ነገር የአንቀጹ ሀይለቃል መሆኑን መገንዘባቸውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡

### ተግባር አራት

በአከባቢያቸው የሚገኝ ተፈጥሯዊ መስህብ እንዲጎበኙ ይዘዟቸው፡፡ በጉብኝቱም ወቅት ስላዩት ነገር በአስተዋጽኦ መልክ የጉዞ ማስታወሻ ይያዙ፡፡ በመጨረሻም በጥንድ በመተጋገዝ

አስተዋጽኦውን በአንቀጽ አደራጅተው በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻቸው በንባብ እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች ይህን ሲያደርጉ በመከታተል አስፈላጊውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### ተግባር አምስት

ተማሪዎች ስለቃል ምንነት ከማስታወሻው ከመመልከታቸው በፊት የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ስለቃል ምንነት እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ስለቃል ምንነት ውይይት እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

ተዘውታሪ ቃላት የሚባሉት ምን አይነት ቃላት እንደሆኑ እንዲናገሩ በማድረግ የቀረበላቸውን ማስታወሻ በማቅረብ ማወያየት ያስፈልጋል፡፡ከአካባቢ ቁሳቁስ ተዘውታሪ ቃላትን ለማለማመድ የሚያግዝ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀሙ፡፡

### መልመጃ አራት

ሀ. ቃላት የነገሮች ተወካይ በመሆናቸው በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ነገሮችን የሚወክሉ ቃላት፣ ስሜትን የሚወክሉ ቃላት፣ ጽንሰሀሳብ የሚወክሉ ቃላት በሰንጠረዡ ውስጥ እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡

ለ. ከ ሀ - ሠ በቀረቡት ተዘውታሪ ቃላት አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ምሳሌ በመስጠት ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች ሰርተው ሲያቀርቡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡ **ቸር** - መሐመድ ቸር ነው፡፡

ሐ. ተማሪዎች ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው ለእርስ በእርስ ትውውቅ የሚያገለግል ንግግሮችን እንዲያደርጉ ይዘዟቸው፡፡ ሁለት ተማሪዎችን በመምረጥ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ንግግሩን እንዲያደርጉ ያድርጉ፡፡ ተገቢውንም እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ተግባር ስድስት**

ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን ሆነው እንዲወያዩ በማድረግ እንዲናገሩ ይዘዟቸው፡፡ በመቀጠል በሳጥኑ ውስጥ የቀረበላቸውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡

ከአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅሮች የንግግር ድምጾችን፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና የአረፍተነገር አወቃቀር ሂደት በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡ የአፍመፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅሮችን በተመለከተ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

**መልመጃ አምስት**

ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ለተማሪዎች ተገቢውን መልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

የዓረፍተ ነገር መዋቅርን በሚመለከት የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎች የአረፍተነገር መዋቅር በሚለው ሀሳብ ዙሪያ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ አንድ ዓረፍተነገር ሲዋቀር የዓረፍተ ነገሩ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ በጾታ፣ በቁጥርና በመደብ መስማማት እንዳለበት ተጨማሪ መረጃዎችን በማጠናከር ይግለጹላቸው፡፡

**መልመጃ ስድስት**

ሀ. ተማሪዎች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጹ እንዲስማማ በማድረግ እንዲገነቡ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች ዓረፍተነገር በሚመሰርቱበት ጊዜ እየዞሩ በመከታተል ተገቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-5 ላይ በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ለይተው እንዲያመለክቱ ያበረታቷቸው፡፡

3.ግምገማ

- የቀረበውን ምስል በማየት በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- በኦሮሚያ ክልል የሚያውቋትን ሀይቆች ስም እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- የወንጪ ሀይቅ በሚል የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ እንዲሰጡ መጠየቅ፡፡
- በቀረቡት መወያያ ነጥቦች ላይ ከተወያዩ በኋላ ዘገባ እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- ስለብሄራዊ ፓርኮች የቀደመእውቀታቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የቀደመ እውቀታቸውን ለመገምገም ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡
- ምንባቡን እንዲያነቡ በማድረግ የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍችያቸውን በመፈለግ እንዲያዛምዱ ማድረግ
- ለአንብቦ መረዳት የሚያገለግሉ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማበረታታት
- በቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ምሳሌ በመስጠት ማበረታት
- ልምዳቸውን በመጠቀም አንቀጽ እንዲጽፉ ማበረታታት
- የዓረፍተ ነገር ዋና ዋና ተዋቃሪ አካላት እንዲገልጹ ማድረግ
- ዓረፍተ ነገር ሲዋቀር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አስማምተው እንዲጽፉ ማበረታታት

# የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

# መልመጃ ሁለት

**ሀ. የእውነት/ ሀሰት መልሶች**

1. ሀሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሀሰት

5. እውነት

**ለ. አዛምድ ጥያቄ መልስ**

1. ሸ
2. በ
3. ለ
4. ሀ
5. ረ
6. ሐ.
7. መ
8. ቀ
9. ሰ

*መልመጃ ሶስት*

**ሀ. ዓረፍተነገሮችን ቅደም ተከተላቸውን አስተካክሎ አንቀጽ መጻፍ**

ፋጡማ ሁል ጊዜ ሳይረፍድባት መማሪያ ክፍል ትገኛለች፡፡ በጥዋት ተነስታ መጸዳጃ ቤት ትሄዳለች፡፡ ከዚያም እጇንና ፊቷን በሳሙና ትታጠባለች፡፡ ቁርሷን በልታ፣ ጓደኛዋን ጠርታ ወደትምህርት ቤት ትሄዳለች፡፡

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. ምርጫ**

1. ለ
2. ሐ.
3. መ
4. መ
5. ለ

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ. ዓረፍተነገሮችን አስተካክሎ መጻፍ**

ቶላ ወደቤቱ ሄደ፡፡

አሰገደች መጣች፡፡

ሜቲና ማርቆስ ወደሱቃቸው ገቡ፡፡

ለእርሳቸው ጉዳዩን ነገርኳቸው፡፡

መሀመድ እና ሞሚና ወንድምና እህት ናቸው፡፡

ለ. ከቀረቡት አረፍተነገሮች ባለቤት፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ መለየት

| ጥያቄ | ባለቤት | ተሳቢ | ማሰሪያ አንቀጽ |
|---|---|---|---|
| 1 | ፍጹም | በጉን | መታች |
| 2 | ልጁ | | መጣ |
| 3. | ጫላ | ኳሱን | አነጠረ |
| 4. | አባቴ | | ይወደኛል |
| 5. | እሷ | በሬውን | ሸሸች |

# ምዕራፍ ሁለት

# የቤተሰብ ምጣኔ

**(ክፍለጊዜ ዘጠኝ)**

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የሚነበብላቸውን ምንባብ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡
- ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል ይተርካሉ፡፡
- የቀረበላችውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለተለያዩ መልመጃዎችና ተግባራት መልስ ይሰጣሉ፡፡
- አስረጅ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅሮች ጠብቀው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

## 2.የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- የሚነበበውን ጽሁፍ ማዳመጥ
- የአዳምጦ መረዳት መልመጃዎች

### 2.2. መናገር

- ጥንድ ጥንድ በመሆን ጭውውት ማቅረብ
- ስለቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ዘገባ ማቅረብ
- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ጥቅም መናገር

2.3. ንባብ

- ምንባብ ማንበብ
- የንባብ ክንውን ደረጃዎች
- አንብቦ መረዳት መልመጃዎች

2.4. መጻፍ

- አስረጅ ጽሁፍ
- በአስረጅ ጽሁፍ አንቀጽ መጻፍ

2.5. ቃላት

- ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት
- ለቃላት አገባባዊ ፍች መርጦ ማዛመድ

2.6. ሰዋስው

- ዓረፍተ ነገር መገንባት
- ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላትን አስተካክሎ ዓረፍተነገር መጻፍ

## 3. ማስተማሪያ ዘዴ

- ለቅድመ ማዳመጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች አቅርቦ በቃል እንዲመልሱ ማድረግ
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ለአዳምጦ መረዳት የቀረበውን ጽሁፍ ማቅረብ
- የአዳምጦ መረዳትን ተግባራት ማቅረብ
- ጭውውት ማቅረብ
- ከጭውውቱ የተገነዘቡትን በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ
- በቡድን በመሆን መረጃዎችን አደራጅቶ ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ቅድመ ንባብ ተግባራትን ማሰራት
- የቤተሰብ ምጣኔ በሚል የቀረበውን ምንባብ እንዲያነቡ ማድረግ
- እያነበቡ እያለ የንባብ ጊዜ ተግባር ማሰራት
- የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ማሰራት
- አስረጅ ጽሁፍን በተመለከተ ማስታወሻ እንዲወስዱ ማድረግ
- በአስረጅ ጽሁፍ አንቀጽ መጻፍ እንዲለማመዱ ማድረግ
- ለቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ

- ዓረፍተ ነገር እንዲገነቡ ማድረግ
- ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክለው እንዲጽፉ ማድረግ፡፡

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከሁ-ለ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተማሪዎች የሚመልሱትን በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ በመስጠት ለሚቀጥለው ትምህርት ያነሳሷቸው፡፡

# ቤተሰብን ያለመመጠን ጉዳት

የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን በተግባር ላይ ማዋል በጣም ወሳኝ ነው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ በ1984 ዓ.ም የኢትዮጵያ የህዝብ ብዛት 40 ሚልዮን ነበር፡፡ ይህ ቁጥር 2.5 እጅ በማደግ በአገራችን አቆጣጠር በ2009 ወደ 94.3 ሚልዮን ገደማ ደርሷል ተብሎ ይገመታል፡፡ በየአመቱም 2 ሚልዮን ህጻናት ይወለዳሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ፍጥነት የሚቀጥል ከሆነ የአገራችን የህዝብ ብዛት በሚመጡት 30 አመታት አሁን ካለው የህዝብ ብዛት እጥፍ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ምንባቡን እያነበቡላቸው በመሀል ንባቡን ገታ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ከተማሪዎች መልሳቸውን ይቀበሏቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

1. በ1984 የኢትዮያ የህዝብ ብዛት ስንት ነበር?
2. ቤተሰብን አለመመጠን በየትኞቹ ዘርፎች ላይ ተጽእኖ ያመጣል?

ይህ ደግሞ በሰዎች ኑሮ ላይ፣ በተፈጥሮ ሀብት ላይ፣ በኢኮኖሚ እድገት ላይና መሰረታዊ ልማትን በማስፋፋት ረገድ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በምግብ እጥረትና ስራ አጥን ከማብዛት አንጻር የሚያስከትለው ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን በስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው፡፡

የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቅሞ አራርቆ መውለድ በቤተሰቡ ውስጥ ደስታና እድገት እንዲኖር ያግዛል፡፡ በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚኖረው አስተዋጽኦ ትልቅ ነው፡፡ ስለዚህ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን የራሳችንን ድርሻ እንወጣ፡፡

*(ኦሮሚያ ኮሙኒኬሽን ቢሮ፡፡2009፡፡ ድረ ገጽ https://www.facebook.com የቀረበ፡፡)*

## አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

ሀ.ያዳመጡትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ከ1-5 ተራ ቁጥር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በቃል መስጠታቸውን ይከታተሏቸው፡፡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለ ጊዜ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተግባር አንድ**

ሀ. ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው የቀረበላቸውን ጭውውት እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ጭውውቱን በፍላጎት የሚያቀርቡ ተማሪዎችን በማስተባበር ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች ከጭውውቱ ምን እንደተረዱ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

ለ. የቀረበላቸውን ጭውውት መሰረት በማድረግ ሌላ መሰል ጭውውት እንዲያዘጋጁ ይንገሯቸው፡፡ የአዘገጃጀት ሂደቱ እንዴት እንደሆነ ያስረዷቸው፡፡ ከዚያም በቡድን በመወያየት ጭውውቱን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ከጭውውቱም ምን እንደተገነዘቡ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

**ተግባር ሁለት**

በቅድሚያ በአከባቢያቸው ወደሚገኝ ጤና ጣቢያ ሄደው ስለቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የህክምና ባለሙያ በመጠየቅ መረጃዎችን እንዲያሰባስቡ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በቡድን በመሆን መረጃዎችን አደራጅተው ዘገባ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ዘገባውንም ለክፍል ጓደኞቻችው በቃል

ያቅርቡ፡፡ በተጨማሪም ወደፊት ቤተሰብ ሲመሰርቱ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ቢሆኑ የሚያገኙትን ጥቅም ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡በዚህን ጊዜ እርስዎም ቤተሰብን ለመመጠን የሚያገለግሉ የህክምና ዘዴዎችን በምስል ወይም በቁስ እንደመርጃ መሳሪያ በክፍል ውስጥ በማምጣት ይጠቀሙበት፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-3 ለቀረቡት ጥያቄዎች የቀደመእውቀታቸውን በመጠቀም እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

የቤተሰብ ምጣኔ በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ መጀመሪያ ለራሳቸው በአይን እይታ ብቻ እንዲያነቡ በማድረግ በምንባቡ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት በመሰብሰብ እንዲያቀርቡ በመንገር ፍችያቸውን እንዲገነዘቡ ይርዷቸው፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እስካሁን ያነበቡትን ምንባብ ምን ያህል እንደተገነዘቡ የሚያመለክቱ ጥያቄዎችን ማለትም ከ1-2 ያሉትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

# መልመጃ ሁለት

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-10 ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹ ትክክል ከሆኑ እውነት ካልሆኑ ግን ሀሰት በማለት እንዲመልሱ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

አስረጅ ጽሁፍን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲወስዱ በማድረግ ሰፋ ያለ ገለጻ በማድረግ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ይርዷቸው፡፡ ለአንድ ድርሰት የሚያስፈልጉ ሂደቶችን የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

### ተግባር ሶስት

አስረጅ አንቀጽ ለመጻፍ የሚያስችሉ ሶስት ርእሶች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ርእሶች አንዱን በመምረጥ የተሰጡትን መመሪያዎች በመከተል አስረጅ ጽሁፍ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ አስቀድመው በዚህ የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴ የቀረበ ሌላ ምሳሌ በመውሰድ በደንብ እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡ ከዚያም አንድ ርእስ መርጠው በአስረጅ አንቀጽ ድርሰት እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡ በመቀጠል የቢጤ እርማት እንዲያደርጉ ካዘዟቸው በኋላ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## ትምህርት አምስት፡ቃላት

## መልመጃ ሶስት

ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ከ1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ የሰጡትን ትርጉም በማየት ተገቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ከ1-10 ለቀረቡት ቃላት ከለ ስር በመምረጥ አገባባዊ ትርጉማቸውን እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን መልስ በመመልከት ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

***መልመጃ አራት***

*ሀ. በሰንጠረዡ ውስጥ ከቀረቡት ባለቤት፣ ተሳቢ እና ማሰሪያ አንቀጽ በመምረጥ ሙሉ መልእክት የሚያስተላልፉ አስር አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡ አስቀድመው እርሶ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስረዷቸው፡፡ ተማሪዎችም የሰሩትን ጽፈው ሲያቀርቡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡*

*ለ. ከተራ ቁጥር 1-4 ያሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ቃላት ተዘበራርቀው የተቀመጡ ናቸው፡፡ ቃላቱን በማስተካከል አረፍተነገር እንዲገነቡ ይርዷቸው፡፡ ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት አረፍተነገሮችን ይስሩላቸው፡፡ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡*

## 3.ግምገማ

- *የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ መጠየቅ*
- *እያዳመጡት ስላለው ምንባብ የተረዱትን እንዲናገሩ መጠየቅ*
- *ስላዳመጡት ምንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መጠየቅ*
- *ስለቤተሰብ ምጣኔ የሚያመለክት ጭውውት ተመልክተው እነሱም ያንኑ ደግመው እንዲጫወቱ ማድረግና ከጭውውቱ የተገነዘቡትን እንዲናገሩ መጠየቅ*
- *የቤተሰብ ምጣኔ በሚል የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት የቀደመ እውቀታቸውን የሚቀሰቅስ ጥያቄዎችን መጠየቅ*
- *ምንባቡን እያነበቡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን መጠየቅ*
- *ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት እንዲመልሱ ጥያቄ ማቅረብ*
- *አንቀጽ እንዲጽፉ ማዘዝ*
- *ለቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ መጠየቅ*

- ለቃላት አገባባዊ ፍቺ እንዲያዛምዱ መጠየቅ
- አረፍተነገሮችን እንዲገነቡ ማዘዝ
- ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክለው አረፍተነገር እንዲገነቡ መጠየቅ

## የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ግን ሀሰት በማለት መመለስ፡፡**

1. ሀሰት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. ሀሰት
7. ሀሰት
8. እውነት
9. እውነት
10. እውነት

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ. የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት፡፡**

1. ስንጠቅስ
2. አጠናቀቅሁ
3. መከልከል
4. እገዛ
5. እርግዝና እንዳይከሰት የሚያደርግ

**ለ. አገባባዊ ፍች ማዛመድ**

1. መ
2. ሐ
3. ረ
4. ሠ
5. ሀ
6. ለ

**መልመጃ አራት**

**ለ. ተዘበራርቀው የተቀመጡትን አረፍተነገሮች አስተካክሎ መጻፍ**

1. በላይነሽ ውሃ ስለጠማት ጠጣች፡፡
2. ሰይፉ መምህሩ ስለጠራው ደስ አለው፡፡
3. መሰረት መረብ ኳስ መጫወት ትወዳለች፡፡
4. አቡበከር ከትምህርት ቤት ሲወጣ በሩጫ ወደቤቱ ገባ፡፡

# ምእራፍ ሶስት

# የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

**(ክፍለጊዜ ዘጠኝ)**

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ አዳምጠው ስሜታቸውን ይገልጻሉ፡፡
- የበጎ ፈቃደኝነት መተግበሪያ አከባቢዎችን ይለያሉ፡፡
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ ያስታውሳሉ፡፡
- ምንባቡን አንብበው ከምንባቡ ተዘውታሪ ቃላት ለይተው ያወጣሉ፡፡
- አራት አንቀጽ ያሉት የማግባቢያ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- የቃላትን ነጠላና ብዙ ቁጥር ለይተው ያመለክታሉ፡፡

## 2. የትምህርቱ ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የሚነበበውን ምንባብ የየአንቀጾችን ፍሬ ሀሳብ መለየት
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

### 2.2 መናገር

- ምስል በማየት መልእክቱን መናገር
- ተማሪዎች በጎአድራጎት ላይ ያላቸውን ሀሳብ እንዲናገሩ ማድረግ

### 2.3 ማንበብ

- ምንባብ ማንበብ
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት
- ተዘውታሪ ቃላትን መለየት

2.4 መጻፍ

- አስረጅ ድርሰት
- አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽ ማስፋፊያ ስልት
- በአወዳዳሪ አንቀጽ መጻፍ
- በማነጻጸር አንቀጽ መጻፍ

2.5 ቃላት

- ከምንባብ አዳዲስ ቃላትን መለየት
- ጥምር ቃላት
- ጥምር ቃላት መመስረት
- ለቃላት ፍቺ መስጠት

2.6 ሰዋስው

- ነጠላና ብዙ ቁጥር
- ነጠላ ቃላትን ወደብዙ ቁጥር መቀየር
- ብዙ ቃላትን ወደ ነጠላ ቁጥር መቀየር

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቅድመ ማዳመጥ ተግባር በማቅረብ የቀደመ እውቀታቸውን በውይይት መቀስቀስ
- በማዳመጥ ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻቸው እንድይዙ ማድረግ
- ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት ያደረገ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- የቀረበውን ምስል መሰረት በማድረግ ከምስሉ የተገነዘቡትን በንግግር እንዲያቀርቡ በማድረግ የንግግር ክሂላቸውን ማዳበር
- ቅድመ ንባብ ተግባራትን በማቅረብ ማወያየትና የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ
- የንባብ ጊዜ ተግባር ማሰራት
- አንብቦ መረዳት ተግባራትን ማሰራት
- ተዘውታሪ ቃላትን ከምንባቡ እንዲያወጡ ማድረግ

- ድርሰት መጻፍ ማለማመድ
- አስረጅ ድርሰት ምንነት በማቅረብ ማወያየት
- አስረጅ ድርሰት አይነቶችን በማቅረብ ማወያየት
- በአስረጅ ድርሰት አይነቶች ድርሰት እንዲጽፉ ማለማመድ
- ከምንባቡ አዳዲስ ቃላት መለየት
- ጥምር ቃላት እንዴት እንደሚመሰረቱ ማለማመድ
- ለጥምር ቃላት ትርጉም እንዲሰጡ ማድረግ
- ነጠላና ብዙ ቁጥር የሚያመለክቱ ቃላትን ማቅረብ

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ውድ መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሻቸውን ይቀበሉ፡፡ በተጨማሪም በመቀጠል የሚቀርበውን የማዳመጥ ግብአት ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው፡፡ የማዳመጥ ግብአቱን እንደ ተማሪዎችዎ የትምህርት አቀባበል ደረጃ አንዴ ወይም ሁለቴ ያንብቡላቸው፡፡ ተማሪዎችዎ የሚነበብላቸውን ፅሁፍ እያዳመጡ ዋና ዋና ሀሳብ በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲመዘግቡ ያበረታቷቸው፡፡

1. ሰዎችን በተለያዩ ነገሮች መርዳት ምን ተብሎ እንደሚጠራ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
2. ተማሪዎች ከዚህ በፊት ሰዎችን በምን በምን ረድተው እንደሚያውቁ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

## ኦብሴ ሉቦ

ኦብሴ ሉቦ ትባላለች፡፡ ተወልዳ ያደገችው  ኦሮሚያ ክልል ምእራብ ወለጋ ዞን በነጆ ከተማ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷንና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጋማሹን እዛው በነጆ

ከተማ ነው የተማረችው፡፡ ኋላ ላይ ወደአሜሪካ አገር የመጓዝ እድል አግኝታ በሚኒሶታ ክልል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷንና የመጀመሪያ ድግሪዋን በህክምና ዘርፍ በነርስ ሙያ ተምራለች፡፡

የነርስነት ትምህርቷን ስትጨርስ ወደ ካሊፎርኒያ ግዛት በመሄድ ኑሮዋን ጀመረች፡፡ በ2001 ዓ.ም. ወደ ሀገር ቤት ስትመጣ የነጆ ሆስፒታልን ስትጎበኝ በሆስፒታሉ በህክምና ሙያ የሚያገለግሉ ምን እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ተመልሳ ወደ አሜሪካ ሄደች፡፡ በዚያም አብረዋት የሚሰሩትን ነርሶች በማግባባት እንዴት ሆስፒታሉን እንደሚረዱ ተመካከሩ፡፡ በዚህም አብረዋት ከሚሰሩ ነርሶች ጋር ወደሀገር ቤት መጥተው ለሶስት ሳምንት የበጎ ፍቃድ ተግባርን ሰርተው ተመለሱ፡፡

ከዚያን ጊዜ አንስቶ በየአመቱ ወደሀገር ቤት በመምጣት በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ከሚኖሩ ሀኪሞች ጋር በመተባበር በሆስፒታሉ የበጎ ተግባር ስራ ፈጽመዋል፡፡ በ2007 ወደሀገር ቤት በመምጣት የቀዶ ጥገናና ለእናቶችና ለሌሎች ሰዎች የህክምና እርዳታ ሲፈጽሙ ነበር፡፡ እዚህ በቆይታዋም የኦክስጂን መሳሪያ እጥረት ያለ መሆኑን ስለተረዳች መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ሮተሪ ኢንተርናሽናል ግሎባል ግራንት በሚል ድርጅት ውስጥ በአባልነት ስለምትሳተፍ የድርጅቱን ሰራተኞች በማግባባት ወደስራ ገቡ፡፡ የፕሮጀክቱ ስራም አምስት አመት ይፈጃል፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እዚህ ጋር ምንባቡን ገታ በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ

1. ኦብሴ የተወለደችው የት ነው?
2. ኦብሴ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያገኘችው በምን ሙያ ነበር?.
3. የጽሁፍን ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦች መዝግቡ፡፡

ዓላማውም በምዕራቡ የአገራችን አከባቢዎች በተለይ ከአዲስ አበባ ርቀው ያሉ ሆስፒታሎች ረጅም ርቀት በመጓዝ አዲስ አበባ ሂደው ኦክስጅን የሚያስሞሉትን ድካም ያስቀራል፡፡ ይህ የኦክስጅን ምርት ለሳምባ በሽታ፣አስም፣በአተነፋፈስ ላይ የሚደርሱ በሽታዎችና ለኮቪድ-19 በሽተኞች ያግዛል፡፡ ኦብሴ የሚያስደስታትንና የሚያሳዝናትን ስትናገር ከ20-30 ዓመት ያሉ ወጣቶች የአይን ሞራቸው ሲነሳላቸውና በደንብ ሲያዩ እንደሚያስደስታትና የሚያሳዝናት ነገር ደግሞ ሰዎች ህክምና በማጣት ሲቸገሩ ስታይ ነው፡፡ ይህንን ተግባሯን በሌሎች የሀገሪቱ ክፍል

አጠናክራ መስራት እንደምትቀጥልበትና ለዚህም ተግባሯ ቤተሰቦቿና የሙያ አጋሮቿ እንደሚያግዟት ትናገራለች፡፡ ሴቶችም እሷን በመመልከት ጠንክረው መማር እንዳለባቸውና በአላማቸው ጸንተው መማር እንደሚገባቸው ትመክራለች፡፡

ምንጭ (ድረ ገጽ https://www.bbc.com)

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**ተግባር አንድ**

በማዳመጥ ሂደት የያዙትን የጽሁፉን ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች በተራ በመነሳት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

**መልመጃ አንድ**

ሀ. ያዳመጡትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ ከተማሪዎችም ለምሳሌ ጥያቄ ቁጥር አንድ የተለያዩ የህክምና አገልግሎት እና የህክምና ቁሳቁስ ረድተዋል የሚል መልስ ይጠበቃል፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተግባር ሁለት**

የቀረበላቸውን ምስል መሰረት በማድረግ የተገነዘቡትን በክፍል ውስጥ በንግግር እንዲያቀርቡ በማድረግ የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማገዝ፡፡ ከዚህ በመተጨማሪ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በምን በምን ተግባር ላይ ሰዎችን ሲረዱ እንደነበሩ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡በዚህን ጊዜ በጎአገልግሎት የሚያመለክቱ የተለያዩ ምስሎችን እንደመርጃ መሳሪያ በክፍል ውስጥ ይጠቀሙ፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ወደምንባቡ ከመግባታቸው በፊት የቀደመ እውቀታቸውን የሚቀሰቅሱ ጥያቄዎችን መጠየቅና ምንባቡን በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ የሚከተሉት ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የቀረቡ ናቸው፡፡

1. በአከባቢያችሁ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በበጎ ተግባር የሚታወቁ ሰዎችን ጥቀሱ፡፡
2. በተራ ቁጥር አንድ የጠቀሳችኋቸው ሰዎች አበይት ተግባራት ምን ምን ናቸው?
3. ለሚከተሉት ቃላት እና ሀረጋት ፍቺ ስጡ፡፡

   ለትርፍ ያልተቋቋመ ልማት ተኮር ማህበር

   ለትርፍ የተቋቋመ

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ተማሪዎች አንድ ጊዜ ንባባቸውን ገታ በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ሀሳብ እንዲሰጡ ይጠይቋቸው፡፡

1. ከቀረበው ምንባብ የተወሰኑ አንቀጾችን እንዳነበቡ በመሀል ካነበቡት ምንባብ ምን ፍሬ ነገር እንዳገኙ ይጠይቋቸው፡፡
2. ቀጥሎ የሚመጣው ሀሳብ ስለምን የሚያወሳ እንደሆነ እንዲገምቱ መጠየቅና ምንባቡን በትኩረት እንዲያነቡት ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

ሀ. የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከየአንቀጾቹ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ተዘውታሪ ቃላት እንዲያወጡ ያበረታቷቸው፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ተግባር ሶስት**

በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ሰዎች በበጎ ተግባር ሲሳተፉ የሚሰሩትና የተግባሩ ትሩፋት ምን እንደሆነ በምሳሌው መሰረት በጽሁፍ እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

አስረጅ ድርሰት ከሚጻፍባቸው ስልቶች አወዳዳሪና አነጻጻሪ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ስለነዚህ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች በበቂ ሁኔታ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ይርዷቸው፡፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ በማስጨበጥ የቀረቡትንም ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

**ተግባር አራት**

የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ በማወዳደር አንቀጽ እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡ የጻፉትንም አንቀጽ ተገቢ ግብረመልስ በመስጠት ተማሪዎች ከስተታቸው እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ተግባር አምስት**

በማነጻጸር የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴ በመጠቀም የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ከቀረቡት ሶስት ርእሶች በመረጡት ርእስ ላይ ባለሁለት አንቀጽ ድርሰት እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ በዚህን

ጊዜ ተገቢውን ግብረመልስ በመስጠት ተማሪዎች እራሳቸውን በማስተካከል የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ይርዷቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት አምስት ፡ ቃላት

**መልመጃ ሶስት**

ለማነጻጸር አንቀጽ መጻፊያ ስልት ከቀረበላቸው ምሳሌ አምስት አዳዲስ ቃላት መርጠው እንዲያቀርቡ ማድረግ ፡፡ ከዚያም እርስበርስ ተለዋውጠው በሚሰጣቸው ማስተካከያ መሰረት እንዲያርሙ ያድርጓቸው፡፡ ለመርጃ መሳሪያ ፍላሽ ካርዶችን በመጠቀም አዳዲስ ቃላቱን ያለማምዷቸው፡፡

ጥምር ቃላት ማለት ቃላትን በማጣመር ቃላቱ ከዚህ በፊት ከያዙት ፍች ሌላ አዲስ ፍች እንድይዙ ማድረግ ማለት እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡ አንድ ጥምር ቃል ጥምር ቃል ነው ለማለት የሚከተሉትን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡ ይህንንም ለተማሪዎች ማስገንዘብ፡፡

- የጥምር ቃሉ ትርጉም ቃሉን ካስገኙት ተጣማሪ ቃላት የተለየ ከሆነ፣
- ጥምር ቃሉ ሌሎች ቃላትን ለማስገኘት መሰረት ከሆነ፣
- ጥምር ቃሉ ለልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ባህሪያት የርባታ ቅጥያዎችን በመጨመር ሊረባ የሚችል ከሆነ፣
- ጥምር ቃሉ በቋንቋው የቃል ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ሊመደብ የሚችል ከሆነና፣
- በጥምር ቃሉ መካከል ሌላ ባእድ ምእላድ የማያስገባ ከሆነ የሚሉት ናቸው፡፡

**መልመጃ አራት**

ሀ. ለቀረቡት ጥምር ቃላት የቀረበላቸውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ፍች እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎችም ለጥምር ቃላቱ ፍች ሲሰጡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ነጠላና ብዙ ቁጥር የሚያመለክቱ ቃላትን በምሳሌ በማቅረብ በማወያየት ግንዛቤያቸውን ማዳበር፡፡ ስለነጠላና ብዙ ቁጥር ለማመልከት ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ በሚከተለው መልኩ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት አድርገው ግንዛቤያቸውን ለማዳበር ያግዟቸው፡፡

**የቃላት ነጠላና ብዙ ቁጥር**

ነጠላ ቁጥር አንድ ነገር ሲያመለክት፣ ብዙ ቁጥር ግን ከአንድ በላይ የሆኑ ነገሮችን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ፍየል --ፍየሎች

ለ. ቃል--ቃላት

ከላይ ለመመልከት እንደቻልነው ፍየል የሚለው አንድ ፍየል መሆኑን ሲያመለክት ፍየሎች የሚለው ቃል ግን ከአንድ በላይ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት /-ኦች/ አብዥ ቅጥያ ምእላድ ስለተጨመረበት ነው፡፡ የሁለተኛው ምሳሌ፡ ቃል ነጠላ ቁጥርን ሲያመለክት ቃላት ግን ብዙ ቁጥር ያመለክታል፡፡ በቃሉ ላይም /-ኣት/ የሚል አብገር ቅጥያ ምላድ ተጨምሮበታል፡፡ /-ኦች/ የአማርኛ አብገር ቅጥያ ሲሆን /-ኣት/ የግእዙ አብገር ቅጥያ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

**መልመጃ አምስት**

ሀ. የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ነጠላ ቃላትን ወደብዙ ቁጥር እንዲቀይሩ ግንዛቤ በመፍጠር ከተራ ቁጥር1-5 የቀረቡትን ቃላት ወደብዙ ቁጥር እንዲለውጡ ያበረታቷቸው፡፡

ለ. የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ በብዙ ቁጥር የቀረቡትን ቃላትን ወደነጠላ ቁጥር እንዲቀይሩ ግንዛቤ በመፍጠር ከተራ ቁጥር1-5 የቀረቡትን ቃላት ወደነጠላ ቁጥር እንዲለውጡ ያበረታቷቸው፡፡

## 4. ግምገማ

- ለቅድመ ማዳመጥ የሚውሉ የቃል ጥያቄዎችን ማቅረብ
- እያዳመጡ ስላለው ምንያህል እየተከታተሉ እንደሆነ ለማረጋገጥ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የቀረበላቸውን ምስል በመመልከት የተገነዘቡትን በንግግር እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- ቅድመ ንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ
- እያነበቡ ያሉትን ምንባብ ምንያህል የየአንቀጾቹን ፍሬ ሀሳብ መረዳታቸውን ለመለየት ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ያነበቡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ተዘውታሪ ቃላትን ከምንባቡ እንዲያወጡ ማዘዝ
- አስረጅ ጽሁፍ በመጠቀም አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ
- አዳዲስ ቃላት እንዲያወጡ መጠየቅ
- ለጥምር ቃላት ፍች መስጠት
- ነጠላ ቃላትን ወደብዙ ቁጥር እንዲቀይሩ ማዘዝ
- ብዙ ቁጥር ያላቸውን ቃላት ወደነጠላ ቁጥር እንዲቀይሩ ማዘዝ

# የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

### መልመጃ ሁለት

**ለ.ምርጫ**

1. ሐ 2. ሀ 3. መ 4. መ 5. መ

### መልመጃ አራት

**ሀ. ለጥምር ቃላት ፍች መስጠት**

ምሳሌ፡ በጎ ፈቃድ — በጎ — ጥሩ ነገር
ፈቃድ — ይሁንታ

በጎፈቃድ፡ በፍላጎት አንድን ነገር ለመስራት መወሰን

1. ትምህርትቤት

ትምህርት እውቀት

ቤት መጠለያ

ትምርትቤት እውቀት ማግኛ ተቋም

2. ልበሙሉ

ልብ የሰውነት አካል

ሙሉ ጎዶሎ ያልሆነ

ልበሙሉ ደፋር

3. ሰውሰራሽ

ሰው ሰብአዊ ፍጡር

ሰራሽ ተገበርሽ/ፈጸምሽ

ሰውሰራሽ ተፈጥሯዊ ያልሆነ ነገር

4. ደንብልብስ

ደንብ ስርዓት

ልብስ ሰዎች አካላቸውን ለመሸፈን፣ ከብርድ ለመከላከል የሚለብሱት

ደንብልብስ የአንድ ተቋም መለያ ልብስ

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. ነጠላ ቃላትን ወደብዙ ቁጥር መቀየር**

1. ቤት - ቤቶች /-ኦች/
2. ሰው - ሰዎች /-ኦች/
3. ቃል- ቃላት /-ኣት/
4. እንስሳ- እንስሳት /-ኣት/
5. ደብተር - ደብተሮች /-ኦች/

**ለ. ብዙ ቁጥርን ወደ ነጠላ ቁጥር መቀየር**

1. ሴት
2. ወንድ
3. ትእዛዝ
4. ገዳም
5. እርሳስ

# ምእራፍ አራት

# የታዋቂ ግለሰቦች ህይወት ታሪክ

(ክፍለጊዜ አስራ ሁለት)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የቀረበላቸውን ምንባብ በማድመጥ ፍሬ ሀሳብ ይናገራሉ
- በቡድን ሆነው በቀረበ መመሪያ ላይ ይወያያሉ
- ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ይለያሉ
- የመሸጋገሪያ ቃላትን ይለያሉ
- ተዘውታሪ ቃላትን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይጠቀማሉ
- ሀረጋትን ይለያሉ

## 2. የትምህርት ይዘቶት

### 2.1. ማዳመጥ

- ለማዳመጥ የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥ
- የማዳመጥ ተግባራትንና መልመጃዎችን መስራት

### 2.2. መናገር

- የህይወት ታሪክ ምንነት
- የራስን ህይወት ታሪክ መናገር
- የህይወት ታሪክ አጻጻፍ

### 2.3. ማንበብ

- የንባብ ክንውን ደረጃዎች
- ምንባብ
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

2.4. **መጻፍ**

- ከአንቀጾች መሸጋገሪያ ቃላትን ለይቶ ማመልከት
- አንድ አንቀጽ ጽፎ መሸጋገሪያ ቃላትን ማመልከት
- የህይወት ታሪክ መጻፍ

2.5. **ቃላት**

- ተዘውታሪ ቃላት ምንነት
- ከቀረበው ጽሁፍ ተዘውታሪ ቃላት መለየት

2.6. **ሰዋስው**

- ቃልንና ሀረግን መለየት
- የሀረግ አይነቶች
- ሀረግንና ዐረፍተነገርን መለየት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ እውቀታቸውን በተለያዩ ጥያቄዎች መቀስቀስ
- እያዳመጡ ያሉትን ምንባብ ፍሬ ሀሳብ እንዲገልጹ ማበረታታት
- አዳዲስ ቃላትን ከሚያዳምጡት ምንባብ እንዲያወጡ ማገዝ
- ለአዳምጦመረዳት የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማገዝ
- ለቃላት ፍች የሚሆኑትን ምሳሌ ሰጥቶ ማሰራት
- ስለ የህይወት ታሪክ አጻጻፍ ምንነት ማወያየት
- የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ የተለያዩ የንግግር ተግባራትን ማሰራት
- ቅድመንባብ ተግባራትን በማሰራት የቀደመእውቀታቸውን ማጎልበት
- የንባብ ጊዜ ተግባራትን በማሰራት ምንባቡን ምንያህል እየተገነዘቡ እንደሆነ መለየት
- የመሸጋገሪያ ቃላት ምንነት በተመለከተ ማወያየት
- ከቀረበው ምንባብ መሸጋገሪያ ቃላትን መለየት
- ስለተዘውታሪ ቃላት ምንነት ማወያየት
- ቃልንና ሀረግን እንዲለዩ ማገዝ
- ሀረግንና ዓረፍተ ነገርን እንዲለዩ ማገዝ

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ጽሁፍ ከማዳመጣቸው በፊት የሚከተሉትን ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የምታውቋቸውን ስመጥር ድምጻዊያንን ስም ዘርዝሩ?
2. የህይወት ታሪክ በውስጡ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች ዘርዝሩ፡፡
3. ከዚህ በታች የቀረበው ፎቶ የማን እንደሆነ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## የአርቲስት ዓሊ ቢራ የህይወት ታሪክ

ዝነኛው አርቲስት ዓሊ ቢራ ከእናቱ ከወ/ሮ ፋጡማ ዓሊ እና ከአባቱ አቶ መሐመድ ሙሳ፣ በድሬዳዋ ከተማ ገንደ ቆሬ ገንደ ካባ በምትባል አካባቢ ግንቦት 26/1940 ዓ.ም ተወለደ። እድሜው 12 ዓመት እስኪ ሞላው በአረብኛ ቋንቋ የሀይማኖት ትምህርት ተከታተለ። ከዚህ በኋላ መደበኛ ትምህርቱን እየተማረ ጐን ለጐን የሚወዳቸውን ሙዚቃዎች በተለያዩ ቋንቋዎች እያዳመጠ አደገ።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አርቲስት ዓሊ ቢራ የተወለደው የት ነው?
2. አርቲስቱ የሀይማኖት ትምህርቱን የተከታተለው እድሜው ስንት እስኪደርስ ድረስ ነው?
3. ጽሁፉን እያዳመጣችሁ አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ መዝግቡ፡፡

አርቲስት ዓሊ ቢራ በሚያቀነቅነው ዘፈን የአድማጭን ስሜት በመያዙና በማስደሰቱ ከህዝብ ከፍተኛ አድናቆትን አተረፈ። በ1962 ዓ.ም. በድሬዳዋ ከተማ ከሚገኘው «ከአርፈንቀሎ» የሙዚቃ ባንድ ለአርቲስቱ የአብረን እንሥራ ጥሪ ቀረበለት። ዓሊም ጥሪውን በደስታ ተቀብሎ በ1963 የባንዱ አባል በመሆን ከባንዱ ጋር ስራውን ማቅረብ ጀመረ። «ከአርፈንቀሎ» የሙዚቃ ባንድ ጋር በመሆን «ቢራንበሪኤ» የተሰኘውን ሙዚቃ ለአድማጭ አቀረበ።

ይህንን ዘፈን ያዳመጡ ሰዎች ዘፈኑን መሰረት በማድረግ ዓሊ መሐመድን ዓሊ ቢራ ብለው መጥራት ጀመሩ። ከዚህም የተነሳ «ቢራ» የሚለው ስም የዓሊን አባት ስም ተክቶ እስከ አሁን መጠሪያው ሆኗል። አርቲስት ዓሊ ቢራ በ1966 ዓ.ም ክቡር ዘበኛ ተብሎ ወደሚታወቀው ባንድ ተቀላቅሎ በተለያዩ ቦታዎች ህዝቡን የሚያስደስቱ የሙዚቃ ስራዎችን እያቀረበ ያዝናና ነበር።

አርቲስት ዓሊ ቢራ በ1982 ዓ.ም የስዊዘርላንድ ዜግነት ካላት ሴት ጋር የትዳር ህይወት መሠረተ። በ1984 ዓ.ም. ባለቤቱ ወደ አሜሪካ ስለሄደች እሱም ከባለቤቱ ጋር ወደዚያው አመራ።አርቲስት ዓሊ ቢራ ለኢትዮጵያ ኪነጥበብ ማበብና ከፍተኛ ደረጃ መድረስ የላቀ አስተዋፅኦ አድርጓል።በተለይም ዜጎች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ለማሳደግ በማይችሉበት ስርዓት የኦሮሞን ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በተጨማሪም ትውልዱ የትምህርትን ጥቅም አውቆ እራሱን፣ አገሩንና ህዝብን እንዲጠቅም በሙዚቃው ይቀሰቅስ ነበር። ይህን ከግምት ውስጥ ያስገባው የጅማ ዩንቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቶታል። በአጠቃላይ አርቲስት ዓሊ ቢራ ለሙዚቃ ህይወቱን የሰጠ፣ በሙዚቃም የህዝብን ስሜት መያዝ የቻለና ለአዲሱ ትውልድ ጥሩ ተምሳሌት የሆነ በአለም ላይ አድናቆት ያተረፈ የኪነጥበብ ሰው ነው። የሠራቸው ስራዎችም ለዛቸው ሳይጠፉ አሁንም እየተደመጡ ይገኛሉ፡፡

*ምንጭ (የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የኦሮሚያ ትምርት ቢሮ፡፡ 2007፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ከተዘጋጀ መጽሀፍ የተወሰደ)*

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

ሀ. ካዳመጡት ምንባብ የተወሰደ አንቀጽ በቀረቡት ባዶ ቦታዎች ከላይ የቀረቡትን ቃላት በመምረጥ በተገቢው ቦታ እንዲያስገቡ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን መልስ በመከተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ከ1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ትርጉም ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ለተማሪዎችም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

የህይወት ታሪክን በተመለከተ የቀረበላቸውን ማስታወሻ በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲወስዱ ያድርጓቸው፡፡ ስለህይወት ታሪክ ምንነት እንዲወያዩ ይዘዟቸው፡፡ ሲወያዩም ተማሪዎችን ይከታተሏቸው፡፡ ተገቢውንም ገለጻና እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

**ተግባር አንድ**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-2 ላሉት የተግባር ጥያቄዎች በተግባር እንዲያመለክቱ ያበረታቷቸው፡፡ ተገቢውንም እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ወይም የመወያያ ነጥቦች ሲሰጣቸው ተሳትፏቸውን በማየት መታገዝ ያለባቸውን በማገዝ ፈጣን ተማሪዎችንም የእውቀት አድማሳቸውንና የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ሌሎች ተግባራትን በመስጠት ይርዷቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

**ተግባር ሁለት**

በህይወት ወይም ከህልፈተ ህይወት በኋላ የተጻፉ የህይወት ታሪኮችን ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ ወደክፍል አምጥተው ለተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-3 ለቀረቡት ቅድመንባብ ጥያቄዎች ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ ይህ ተግባር የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ስለሚያደርጋቸው ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ከተራ ቁጥር 1-3 ለቀረቡት የንባብ ጊዜ ተግባራት የቀረበላቸውን ምንባብ በማንበብ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ በዚህም ተማሪዎች እያነበቡት ያለውን ምንያህል እየተረዱት እንደሆነ ለመረዳት ያግዛል፡፡ እርስዎም የተማሪዎችን መልስ በመከታተል ምንያህል ምንባቡን ተረድተው እያነበቡ እንደሆነ ይከታተሏቸው፡፡ ቀጥሎ የሚመጣው ምንባብ ስለምን እንደሚያወራ እንዲተነብዩ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልስ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች ለሚመልሱት መልስ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-5 የቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹም እውነት ወይም ሀሰት በማለት እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

ሐ. ከተራ ቁጥር 1-4 በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት በዓረፍተነገሩ ውስጥ የያዙትን ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ የተማሪዎችንም መልስ ተከትለው ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

መ. በ'ሀ' ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች ከ 'ለ' ስር ፍችያቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ለተማሪዎችም ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

**ተግባር ሶስት**

ከተራ ቁጥር 1-3 የቀረቡ ጥያቄዎችን በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ በቃል ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**ተግባር አራት**

ተማሪዎች መሸጋገሪያ ቃላትን አውጥተው እንዲያመለክቱ የሚያግዝ አንድ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ መሸጋገሪያ ቃላት ለይተው እንዲያመለክቱ ያድርጓቸው፡፡ በሚከተለው መልኩ እንዲያመለክቱ ይጠበቃል፡፡

ምሳሌ፡ ይሂውም

ስለስነጽሁፍ መነጋገር ሲጀመር ገና ከመነሻው ተዘውትሮ የሚጠየቅ አንድ ጥያቄ አለ፡፡**ይኸውም** ማንኛውም የተጻፈ ነገር ስነጽሁፍ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡ ለጥያቄው የሚሰጠው መልስ በሁለት አቅጣጫዎች ነውም አይደለምም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የመጀመሪያው አቅጣጫ ማንኛውም የተጻፈ ነገር ማለትም በወረቀት፣ በእንጨት፣ በድንጋይ በጨርቅ እንዲሁም በመሰል ነገሮች በጽሁፍ ተቀርጾ የተገኘ ሁሉ ስነጽሁፍ ነው

ይላሉ፡፡ሁለተኛው አቅጣጫ ተጽፎ የተገኘ ሁሉ ስነጽሁፍ አይደለም የሚለው ሲሆን ከላይ የተጠቀሱትንና እነሱን የመሰሉትን ከስነጽሁፍ አይቆጥራቸውም፡፡

ስለ ስነጽሁፍ የተሰጡትን ሁለት የብያኔ አቅጣጫዎች ባጭሩ ተመልክተናል፡፡ **ከነዚህ** አቅጣጫዎች የእኛን ትኩረት የሚስበው ሁለተኛው ማለትም ስነጽሁፍን ለተወሰኑ የፈጠራ ስራዎች ብቻ የሚሰጠው በመሆኑ እሱን ዘርዘር አድርጎ መመልከት ይገባል፡፡ **እዚህ** ስነጽሁፍ ስንል "ከሁሉ አስቀድሞ በከያኒው የተፈጠረ ከያኒው የሚያበጀው የክነጥበብ ስራ" መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ **ይህ** የፈጠራ ስራ የሰውን የተለያዩ ገጠመኞችና የኑሮ መልኮች ሊያሳይ የሚችል የሰዎች ሀሳብ መግለጫ ነው፡፡

(ዘሪሁን አስፋው (1992) የስነጽሁፍ መሰረታውያን መጽሀፍ የተወሰደ፡፡)

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ተግባር አምስት**

ከአንድ ምንባብ አንድ አንቀጽ እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ከመረጡት አንቀጽ መሸጋገሪያ ቃላትን ለይተው እንዲያመለክቱ ይዘዟቸው፡፡ የራሳቸውን ገጠመኝ በተመለከተ አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ይዘዟቸው ከጻፉት አንቀጽ መሸጋገሪያ ቃላትን እንዲያመለክቱና ለጓደኞቻቸው እንድያሳዩ ያድርጉ፡፡

ከዚህ በታች በቀረበላቸው ቅደም ተከተል መሰረት መረጃ በማሰባሰብ የህይወት ታሪክ እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡ ቅደምተከተሎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በመጀመሪያ በህይወት ታሪክ ሊካተቱ የሚችሉ ጭብጦችን መሰረት በማድረግ ከአምስት የማያንሱ ጥያቄዎች አዘጋጁ፡፡
- በመቀጠል ጥያቄዎቹን በአቅራቢያችሁ ለምታገኙት ጓደኛችሁ አቅርባችሁ መረጃ ሰብስቡ፡፡
- በመጨረሻም መረጃዎቹን በአንቀጽ አደራጅታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት አምስት፡ቃላት

### ተግባር ስድስት

### ተዘውታሪ ቃላት

ተዘውታሪ ቃላት የሚባሉት በእለት ተእለት የቋንቋ አጠቃቀማችን ለተለያዩ አላማዎች የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አስተማሪ፣ትምህርት ቤት፣መጽሃፍ፣ ለሰላምታ የምንጠቀማቸው ቃላት ...ወዘተ

የተዘውታሪ ቃላት ምንነት በማወያየት ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም በየቀኑ ከሚጠቀሟቸው ቃላት አስሩን ጽፈው እንዲያቀርቡ በማድረግ ከጓደኞቻቸው ጋር በመለዋወጥ እንዲገማገሙ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አስር**

### መልመጃ አራት

ከዚህ በታች ከቀረበው አንቀጽ አስር ተዘውታሪ ቃላትን ለይተው እንዲያመለክቱ ያበረታቷቸው፡፡ ከዘረዘሩት ተዘውታሪ ቃላት ለአምስቱ ቀጥተኛ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግና ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ አንቀጹም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

## ብልጧ ወፍ

አንዲት ወፍ በበረሃ ሰማይ ላይ ስትበር ብዙ ጊዜ ከመቆየቷ የተነሳ ውሃ ጠማት፡፡ ወሃ ለመጠጣት ስትፈልግ አንድ የውሃ እንስራ አየች፡፡ ወደ ውሃው እንስራ ተጠግታ ስትመለከት ውሃው ጎድሎ ስለነበር ለመጠጣት እንደምትቸገር ተገነዘበች፡፡ ከዚያም ውሃ የያዘውን እንስራ በድንጋይ ለመስበር ብትሞክር አልተሳካላትም፡፡ ጥቂት ካሰበች በኃላ ትናንሽ ጠጠሮችን እየለቀመች ወደ ውሃው እንስራ ውስጥ መጨመር ጀመረች፡፡ ቀስ በቀስ ውሃው ወደ እንስራው አፍ እየተጠጋ መጣ፡፡ከዚያም ጠጥታ ጥሟን አረካች፡፡

ክፍለጊዜ አስራ አንድ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## ተግባር ሰባት

ከተራ ቁጥር 1-2 ለቀረቡት ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ በማድረግ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የቀረበላቸውን ማስታወሻ በደብተራቸው ላይ እንዲወስዱ ይዘዟቸው፡፡ ማስታወሻውም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

## ሀረግ

ድምጾች ስርዓት ባለው መልኩ ተቀናጅተው ቃልን እንደሚፈጥሩ ሁሉ፣ ቃላትም ስርዓታዊ ቅንጅት በማድረግ ሀረግን ይመሰርታሉ፡፡ በመሆኑም ሀረግ ከቃል ከፍ ያለ ከዓረፍተነገር አነስ ያለ የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡

በአማርኛ ቋንቋ አምስት አይነት የሀረግ ክፍሎች አሉ፡፡ እነሱም፡

1. ስማዊ ሀረግ
2. ግሳዊ ሀረግ
3. ቅጽላዊ ሀረግ
4. ተውሳከግሳዊ ሀረግ
5. መስተዋድዳዊ ሀረግ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡

| ቃል | ሀረግ |
|---|---|
| ሀ. ቤት | ትልቅ ቤት |
| ለ. ሰበረ | ብርጭቆ ሰበረ |
| ሐ. አክባሪ | ሰው አክባሪ |
| መ. ገና | አሁን ገና |
| ሠ. እንደ | እንደ እህቱ |

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

***መልመጃ አምስት***

*ሀ. በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩ የሀረግ አይነቶች በ "ለ" ስር ከቀረቡት ምሳሌዎቻቸው ጋር ያዛምዱ፡፡ በዚህን ጊዜ ለተማሪዎች ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡*

*ለ. የተዘረዘሩትን ቃላትና ሀረጋት የተሰጣቸውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በተዘጋጀው ሰንጠረዥ ውስጥ በየወገናቸው ለይተው እንዲያስገቡ ይዘዟቸው፡፡*

***መልመጃ ስድት***

*ሀ.ከተራ ቁጥር 1-7 ለቀረቡት ሀረጋትና ዓረፍተነገሮች የተሰጠውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በየወገናቸው ሰንጠረዥ ውስጥ እንዲያስገቡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡*

## 4. ግምገማ

- *የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት የሚቀሰቅስ ቅድመ ማዳመጥ ተግባራት እንዲሰሩ ማድረግ*
- *የማዳመጥ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማዘዝ*
- *ምንባቡን ባዳመጡት መሰረት ጥያቄዎችን በማቅረብ እንዲመልሱ ማድረግ*
- *ለቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ማዘዝ*
- *ለቃላት ፍች በመፈለግ እንዲያዛምዱ ማዘዝ*
- *የመናገር ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያግዝ ተግባራት እንዲሰሩ ማዘዝ፡፡*
- *የቅድመንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ማዘዝ*
- *የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ መጠየቅ*
- *የድህረንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ*
- *ለቃላት ትክክለኛውን ፍቺ እንዲያዛምዱ ማድረግ*
- *የመጻፍ ክሂላቸውን የሚያዳብሩ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ*
- *የቃላት እውቀታቸውን የሚያሰፉ ተግባራትን እንዲሰሩ መጠየቅ*
- *ለተማሪዎች ከቀረበላቸው ምንባብ ተዘውታሪ ቃላትን እንዲለዩ መልመጃዎችን መስጠት*

- ቃላትንና ሀረጋትን እንዲለዩ መልመጃዎችን እንዲሰሩ መጠየቅ
- ሀረጋትንና አረፍተነገሮችን እንዲለዩ መልመጃዎችን እንዲሰሩ መጠየቅ

# የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. ቃላትን በተገቢው ቦታቸው ማስገባት**

የሙዚቃ ባንድ

ጥሪውን

"ከአርፈንቀሎ"

"ቢራንበሪኤ"

**ለ. ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ ከተሰጡት አማራጮች ትክለኛውን መልስ መምረጥ**

1. ሐ
2. ለ
3. መ
4. ሀ
5. ለ

**መልመጃ ሁለት**

**ለ. እውነት/ሀሰት**

1. ሀሰት
2. ሀሰት
3. ሀሰት
4. እውነት
5. እውነት

**መ. ትክክለኛውን መልስ መምረጥ**

1. በ
2. ሐ
3. ሀ
4. ሰ
5. ረ
6. ሠ
7. ሸ
8. መ
9. ለ

**መልመጃ አራት**

**ሀ. አስር ተዘውታሪ ቃላት ማመልከት**

1. መጠጣት
2. ውሃ
3. ጠማት
4. ወፍ
5. አየች
6. ተነሳ
7. መቆየት
8. መስበር
9 . አልተሳካም
10. ድንጋይ

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. አዛምዱ**

1. መ
2. ሠ
3. ሀ
4. ሐ
5. ለ

ለ.የተዘረዘሩትን ቃል/ሀረግ በሚለው ስር ለይቶ ሰንጠረዥ ውስጥ ማስገባት

| ቃል | ሀረግ |
|---|---|
| አእዋፍ | ከእህቱ ጋር |
| ደብተር | ከሸክላ የተሰራ ቤት |
| ልበሙሉ | ሁለት በግ |
| ሰዎች | መቼ ተከፈተ |
| | የጠይም ቆንጆ |
| | እንደወንድሙ ከፉኛ |

መልመጃ ስድስት

ሀ. ሀረጋትና አረፍተነገር መለየት

1. ረጅም እንጨት
2. ሂካ በሬውን ሸጠው
3. ቀይ ሱሪ
4. አለማየሁ ከቤቱ ወጣ
5. እሱ ፎጭ ነው
6. ጥሩ ልጅ
7. እንደ እህቱ ታታሪ

| ሀረግ | ዓረፍተ ነገር |
|---|---|
| ረጅም እንጨት | ሂካ በሬውን ሸጠው |
| ቀይ ሱሪ | አለማየሁ ከቤቱ ወጣ |
| ጥሩ ልጅ | አፊያ ፎጭ ነች |
| የልጅ አዋቂ | |

# ምዕራፍ አምስት

## ውሃና ጠቀሜታው

(ክፍለጊዜ ዘጠኝ)

### 1. የሚጠበቅ ውጤት

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ከቀረበላቸው ምንባብ አዳምጠው መልእክቱን ይናገራሉ፡፡
- ስለውሃ ጥቅም ይገልጻሉ፡፡
- ምንባብን በማድመጥ የምክንያትና ውጤትን ሀሳብ ይለያሉ፡፡
- ተራኪ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- የቃላትን እማሬያዊ ፍች ይለያሉ፡፡
- ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተነገሮችን ይለያሉ፡፡

### 2. የትምህርት ይዘቶች

2.1. **ማዳመጥ**

- የማዳመጥ ክንውን ተግባራትን ማሰራት
- ለቃላትና ሀረጋት ፍች መስጠት

2.2. **መናገር**

- በውሃ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት መዘርዘር
- የውሃ አጠቃም በንግግር መዘገብ
- የውሃ ጥቅም ዙሪያ መወያየት

2.3. **ማንበብ**

- ቅድመንባብ ተግባራት
- የንባብ ጊዜ ተግባራት
- በምንባቡ መሰረት ጥያቄዎችን መመለስ
- ቅደም ተከተል አስተካክሎ መናገር

### 2.4. መጻፍ

- ተራኪ ድርሰት
- በተራኪ ድርሰት አንቀጽ መጻፍ

### 2.5. ቃላት

- ለቃላት በተዘዋዋሪ ፍች መስጠት
- እማሬያዊ ፍች
- ለቃላት እማሬያዊ ፍች መስጠት

### 2.6. ሰዋስው

- ገቢር አረፍተነገር
- ገቢር አረፍተነገር መጻፍ
- ተገብሮ አረፍተነገር
- ተገብሮ አረፍተነገር መጻፍ

## 3.የማስተማሪያ ዘዴ

- ቅድመ ማዳመጥ ተግባራትን እንዲሰሩ ማበረታታት
- የማዳመጥ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማገዝ
- ካዳመጡት ምንባብ ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ማዘዝ
- ለቃላትና ሀረጋት ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- የውሃን ጥቅም እንዲዘረዝሩ ማነሳሳት
- ቅድመ ንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ማገዝ
- የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማነሳሳት
- ምንባቡን በማንበብ ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ማድረግ
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- ሀሳቦችን በቅደም  ተከተል እንዲናገሩ ማድረግ
- በተራኪ ድርሰት አንቀጾችን እንዲጽፉ ማመቻቸት
- ለቃላት እማሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ
- ገቢርና ተገብሮ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማበረታታት

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-3 ለቀረቡት የተግባር ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## የውሃ ብክለት

እንደሚታወቀው ውሃ ለሰው ልጅ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ ብዙዎች "ውሃ ሕይወት ነው" ይላሉ። ወደ 70% የሚሆነው የመሬት ክፍል በውሃ የተሸፈነ ነው። ዋናው የውሃ ምንጭ የከርሰምድር እና የወራጅ ውሃ ናቸው። እነዚህ ሁለት የውሃ ምንጮች በተለያዩ ምክንያቶች ሊበከሉ ይችላሉ።

የውሃ ብክለት ምክንያት የሰው ልጅ ለእለት ተእለት ህይወቱ የሚያደርጋቸው የተለያዩ ክንውኖች ናቸው። ለምሳሌ የፋብሪካ ፍሳሽ ከውሃ መውረጃ ቱቦ ጋር ሲገናኝ፣ የመኪና ዘይት ወደ ውሃ መውረጃ ቦይ ሲለቀቅ የሚከሰት የውሃ መነሻ ብክለት ይጠቀሳል፡፡ ሌላው ደግሞ ከውሃ ምንጭ መነሻ ውጪ የሚከሰት የውሃ ብክለት ነው፡፡ይህም አብዛኛው የሚነሳው ከራሱ ከውሃው ሳይሆን ለምሳሌ ወደ 80% የሚጠጋው የውቅያኖስ ውሃ ብክለት ወደ ባህሮች በመቀላቀል ለእለት ጥቅም ከሚውል ውሃ ጋር ሲቀላቀል የሚከሰት ብክለት ነው፡፡

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እዚህ ጋር እያነበቡት ያለውን ገታ በማድረግ ተማሪዎች የሚከተለውን ተግባር እንዲፈጽሙ ያድርጉ

1. በውሃ የተሸፈነው የመሬት ክፍል ምን ያህል ነው?
2. ቀጥሎ ያለው የጽሁፉ ታሪክ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ፡፡

አብዛኞቹ የሰው ልጅ ክንውኖች የአከባቢያችን ውሃ ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያመጣሉ። ለአብነት ያህል የእርሻ ማዳበሪያ ኬሚካል በጎርፍ ተጠርጎ የወራጅና የከርሰምድር ውሃን

ይበክላል። እንዲሁም በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ኬሚካሎች ከዝናብ ውሃ ጋር ተዋህደው የምድር ውሃን ሊበክሉ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የውሃ ብክለት ምክንያቶች ውስብስብ በመሆናቸው በቀላሉ መፍትሔ ለማግኘት አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል። በአብዛኛው ጊዜ የውሃ ብክለት ታዳሽ ነው፡፡ይሁን እንጂ የተበከለ ውሃን መልሶ ለመጠቀም ከፍተኛ የሆነ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ጉልበት የሚጠይቅ ስለሆነ ውሃ እንዳይበከል ሁላችንም ሀላፊነታችንን መወጣት አለብን፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

*ሀ. ለአዳምጦ መረዳት የቀረበውን ጽሁፍ አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡ተማሪዎችም ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከተራ ቁጥር 1-6 ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ምንባቡን መሰረት በማድረግ ይከታተሏቸው፡፡*

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

*ሀ. ከተራ ቁጥር 1-4 በቀረቡት ሀሳቦች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ የየቡድናቸውን ሀሳብ በተወካያቸው አማካይነት እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡*

**ክፍለጊዜ አራት**

### ተግባር ሶስት

*ከተራ ቁጥር 1-5 ላሉት ጥያቄዎች በውሃ ጥቅም ዙሪያ በቡድን በመወያየት በተሰጡት ምሳሌዎች መሰረት በእያንዳንዱ ርእስ ስር እንዲዘረዝሩ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችንም መልስ በመከታተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡*

**ክፍለጊዜ አምስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ሀ.ተማሪዎች ከተራ ቁጥር 1-3 ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች ውሃን በተመለከተ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ከተራ ቁጥር 1-2 ለቀረቡት ጥያቄዎች እስካሁን ካነበቡት የተረዱትን እንዲገልጹ በማድረግ ምን ያህል ምንባቡን በትኩረት እያነበቡ እንደሆነ ይከታተሉ፡፡ ቀጥለው የሚመጡ አንቀጾች ስለምን ሊያወሩ እንደሚችሉ እንዲተነብዩም ያድርጉ፡፡

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-4 ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-5 ለቀረቡት አረፍተነገሮች ቅደም ተከተል አስተካክለው እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡ ለመነሻ እንዲሆናቸው መጀመሪያ ላይ ቀድሞ የሚጻፈውን ምንባቡን መሰረት በማድረግ ያሳዩዋቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

# ትምህርት አራት ፡ መጻፍ

ስለተራኪ ድርሰት የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ላይ እንዲወስዱ በማድረግ ተጨማሪ ገለጻም ያድርጉላቸው፡፡

## ተራኪ ድርሰት

ስላለፈ ድርጊት የሚተርክ ወይንም የሚያትት ጽሁፍ ተራኪ ድርሰት ይባላል፡፡ለዚህ ምሳሌ ሊሆን የሚችል በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

ምሳሌ፡- በምስራቅ ወለጋ ዞን በአርጆ ወረዳ በ1932 ዓ.ም የተወለደው ሃይሌ ፊዳ የማያልቅ ትዕግስት ያለው አድማጭ ሰው ነው፡፡ ሊያስቆጣ ወይም ስሜትን ሊነካ የሚችል የግል ጉዳይን እንኳ በበጎ የሚያይ ሰው ነበር፡፡ ሃይሌ ቃልና ቁጣ የራቁት ሰው ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ሃይሌ ሁልጊዜ ጠያቂ ሠው ነው፤ በትምህርት ከልጅነቱ ጀምሮ ጎበዝ ነበር፡፡ 8ኛ ክፍል ሚኒስትሪ ወስዶ፣ በአገር ደረጃ አንደኛ ወጥቶ ነው በማዕረግ፣ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተሸጋገረው። ሰብዕናው ሙሉ የነበረ ሰው ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ጀነራል ዊንጌት ት/ቤት ተምሯል፡፡ አብረውት የተማሩና የቅርብ ጓደኞቹ እንደሚናገሩት ከሆነ፤ ሁሉም ሠው ሊወዳጀው የሚጓጓለት፣ ጨዋና አስተዋይ ነበር ይላሉ፡፡ በዚህ ላይ በኢትዮጵያ ጉዳይ ገና በለጋነቱ ማሰብ የጀመረ ሰው ነው፡፡ የአለም የፖለቲካ ሃሣቦችን መመርመር የጀመረው፣ ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ ነው፡፡ 12ኛ ክፍልን የጨረሰው በከፍተኛ ነጥብና ማዕረግ ነበር፡፡ ዩኒቨርሲቲም ገብቶ፣ በልዩ ማዕረግ ነበር የጨረሰው፡፡

*ምንጭ (አዲስ አድማስ ጋዜጣ፡፡2010፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ለክፍል ደረጃው እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ )*

### ተግባር አራት

1. የቀረበላቸውን ተራኪ ድርሰት ምሳሌ መሰረት በማድረግ ከታዋቂ አትሌቶቻችን የአንዳቸውን ታሪክ ከተለያዩ መረጃ ምንጮች በማሰባሰብ ባለሁለት አንቀጽ ተራኪ ድርሰት ጽፈው እርስበር በመለዋወጥ እንዲያርሙ ያድረጉ፡፡
2. ቤተመጽሃፍት በመሄድ በተራኪ ድርሰት አጻጻፍ የተጻፉ ድርሰቶችን በመለየት ወደክፍል በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ለሁለቱም ተግባራት ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ በመከታተል ተገቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### ተግባር አምስት

አብዛኛውን ጊዜ ለቃላት ቀጥተኛ ፍች እንደሚሰጥ ይንገሯቸው፡፡ ለቃላት ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ትርጉም ቀጥተኛ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ሰዎች የቃላትን ተደራቢ ፍቺ ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ አንበሳ የሚለውን ቃል ሀይለኛ፣ ጀግና፣ ጎበዝ ሰው ለማለት ይጠቀሙበታል፡፡ እንዲህ አይነቱ ተግባር አጋጥሟቸው ከሆነ በምሳሌ በማስደገፍ ለመምህራቸው እንደዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡በሚከተለው መልኩ የቀረበውንም ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡

## እማሬያዊ ፍቺ

ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የቃላት እማሬያዊ ፍች የሚባለው

ቃላቱ የሚኖራቸውን ቀጥተኛ ትርጉም የሚያመለክት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ቤት ለሚለው እማሬያዊ ፍችው ለሰውልጅ መኖሪያ የሚያገለግል ከእንጨት፣ከሸክላ ድንጋይ፣ ከብሎኬት…ወዘተ ሊሰራ የሚችል በማለት ፍችውን መስጠት ይቻላል፡፡

### መልመጃ ሶስት

ሀ. ተማሪዎች ከተራ ቁጥር 1-10 ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ተግባር ስድስት

የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ግሶች በመጠቀም አምስት ገቢር ዓረፍተ ነገር ጽፈው ለመምህራቸው እንዲያሳዩ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ተገቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ገቢር ዓረፍተ ነገር

ገቢር ዓረፍተ ነገር የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ድርጊት ፈጻሚ የሚሆንበት የዓረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡ ጫልቱ ቤቱን ጠረገች፡፡

**መልመጃ አራት**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-4 ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ቃላት አስተካክሎ ገቢር አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

ከዚህ በታች የቀረበውን ማስታወሻ ተማሪዎች እንዲወስዱ በማድረግ የቀረቡትን ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ማስታወሻ

**ተገብሮ ዓረፍተ ነገር**

ተገብሮ ዓረፍተ ነገር የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ድርጊት ሲፈጸምበት የሚያመለክት የዓረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. በሬው ተሸጠ፡፡

ለ. መስታወቱ ተሰበረ፡፡

**ተግባር ሰባት**

በቀረበው ምሳሌ መሰረት በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ግሶች በመጠቀም አምስት ተገብሮ ዓረፍተ ነገር ጽፈው ለመምህራቸው እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

**መልመጃ አምስት**

ለተግብሮ አረፍተነገር ምሳሌዎች ለተማሪዎች ቀርቧል፡፡ ያንን መሰረት በማድረግ ተገብሮ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያግዟቸው፡፡ ተማሪዎች አረፍተነገሩን በሚመሰርቱበት ጊዜ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## 4.ግምገማ

- ቅድመ ማዳመጥ ተግባራትን እንዲሰሩ ማዘዝ
- የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማዘዝ
- ካዳመጡት ምንባብ እንዲመልሱ ድህረንባብ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ለቃላትና ሀረጋት ፍች እንዲሰጡ መጠየቅ
- የውሃን ጥቅም እንዲዘረዝሩ ማዘዝ
- ቅድመ ንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ ማዘዝ
- የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማዘዝ
- ምንባቡን በማንበብ ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ማዘዝ
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- ከምንባቡ ለወጡ ሀረጋት ትርጉም ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- በምክንያትነት ለቀረቡ ሀሳቦች ውጤት እንዲያቀርቡ ማዘዝ
- በተራኪ ድርሰት አንቀጾችን እንዲጽፉ መጠየቅ
- ለቃላት አማሬያዊ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- ገቢርና ተገብሮ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማዘዝ
- የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

# የተመረጡ መልመጃ መልሶች

**መልመጃ ሁለት**

**ለ. ወይዘሮ አልማዝ የተጠቀመችውን በሻሽ ውሃ የማጣራት ሂደት ቅደም ተከተል አስተካክለው በዚህ መልኩ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡**

1. ከወንዝ የቀዳችውን ውሃ በሻሽ ታጠላለች፡፡
2. ውሃውን እየተንተከተከ እንፋሎት እስኪወጣው ድረስ ታፈላዋለች።
3. ሲቀዘቅዝ በእንሥራ ትገለብጥና መልሶ እንዳይበከል ትከድነዋለች።
4. ለመጠጣት ሲፈለግ በንፁህ ጣሳ ወይም ብርጭቆ በመቅዳት ቤተሰቦቿ ለመጠጥ እንዲጠቀሙበት ታደርጋለች።
5. ይህን ተግባር ለተከታታይ ሳምንታት ተጠቀመች።

**መልመጃ አራት**

**ሀ. ገቢር አረፍተነገር መመስረት**

1. ሲፈን ለበሬው ጭድ ሰጠች፡፡
2. ደስታ መኪናውን በፍጥነት ነዳ
3. ቶለሳ ቡና ወቀጠ፡፡
4. ሰውነት ኳሱን ለጋው፡፡

**መልመጃ አምስት**

**ሀ. ተገብሮ አረፍተነገሮችን መመስረት**

1. አልጋው ተሰበረ
2. ቆሎው ተደፋ
3. መኪናው ተበላሸ፡፡

# ምእራፍ ስድስት

# የሰዎች ዝውውር

**(ክፍለጊዜ ዘጠኝ)**

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ምንባቦችን በማዳመጥ ዋና ዋና ነጥቦችን ይለያሉ፡፡
- የሰዎች ዝውውር ጽንሰሀሳብ ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- በራሳቸው ተማምነው ንግግር እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡
- የገላጭ ድርሰትን መዋቅር ይመረምራሉ፡፡
- ለቃላት ፍካሬያዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎት አንጻር ይለያሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- የቅድመና የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች
- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### 2.2. መናገር

- ተግባራትን በንግግር ማቅረብ

### 2.3. ማንበብ

- የንባብ ክንውን ተግባራት
- ለቃላት ፍች መስጠት

### 2.4. መጻፍ

- ገላጭ ድርሰት
- ሁለት አንቀጽ ገላጭ ድርሰት መጻፍ

### 2.5. ቃላት

- የቃላት ፍካሬያዊ ፍች ምንነት
- ለቃላት ፍካሬያዊ ፍችና እማሬያዊ ፍች መስጠት

### 2.6. ሰዋስው

- የአረፍተነገር አገልግሎት ምንነት
- የአረፍተነገር አገልግሎት አይነቶች
- ሀተታዊ አረፍተነገር
- አሉታዊ አረፍተነገር
- ጥያቄያዊ አረፍተነገር
- ትእዛዛዊ አረፍተነገር

## 3.የማስተማሪያ ዘዴ

- ለማዳመጥ የተዘጋጀ ምንባብ ከመቅረቡ በፊት የቀደመእውቀታቸውን ለመቀስቀስ ተግባራትን አቅርቦ ማወያየት
- የአዳምጦ መረዳት ምንባብ ሲቀርብ እያዳመጡ ስላለው ምንባብ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ
- ቀጣይ አንቀጽ ስለምን እንደሚገልጽ እንዲገምቱ ማበረታታት
- ስላዳመጡት ምንባብ ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ ማድረግ
- በተለያዩ ርእሰጉዳዮችላይ መረጃ በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ እንዲወያዩና እንዲናገሩ ማበረታታት
- ቅድመንባብ ተግባራትን በማሰራት የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ
- ንባቡን ቆም በማድረግ እያነበቡ ያሉትን ምንያህል እየተገነዘቡ እንደሚያነቡ መከታተል
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ትርጉም እንዲሰጡ ማድረግ
- ስለገላጭ ድርሰት ማስታወሻ መስጠትና ማወያየት
- በገላጭ ድርሰት አንቀጽ እንዲጽፉ ምሳሌ በመስጠት ማሳየት
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ማስታወሻ መስጠትና ማወያት
- ለአረፍተነገር አገልግሎት ማስታወሻ መስጠትና ማወያየት

- የአረፍተነገር አገልግሎት አይነቶችን በመዘርዘር ማወያትና ማጠናከሪያ መስጠት

**ክፍለ ጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ተማሪዎችን ከተራ ቁጥር 1-3 ለቀረቡት የሰዎች ዝውውርን በተመለከተ ተግባራት እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## ሰሚራ

ጣሰው የነሰሚራ ጎረቤት ነው፡፡ ሁልጊዜ እያገኛት ውጭ ሀገር ብትሄድ የተሻለ ህይወት እንደሚኖራትና ጥሩ ኑሮ መኖር እንደምትችል ነገራት፡፡ እንዲሁም በትምህርቷም ጎበዝ ስለሆነች የተሻለ ትምህርት መማር እና ቤተሰቦቿን በተሻለ መልኩ ማኖር እንደምትችል ወትውቶ ልቧን አሸፈተ፡፡ እሷም ቤተሰቦቿን ጥዋትና ማታ ወደውጭ ሀገር እንዲልኳት መነዝነዝ ጀመረች፡፡ ቤተሰቦቿም ጥላቸው እንዳትጠፋ በማሰብ በሀሳቧ ተስማሙ፡፡

ሰሚራም ቤተሰቦቿ በሀሰቧ እንደተስማሙ ለጣሰው ነገረችው፡፡ እሱም ለሰሚራ የነገራትን ለቤተሰቦቿ ተናግሮ እነሱም አመኑት፡፡ ሰሚራም የስምንተኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ በመተማ በኩል ወደሱዳን ከዚያም ወደሳውዲ አረቢያ ሀገር ለመሄድ ተስማምታ የመሄጃ ቀን ተቆርጦ ወደመተማ አቀኑ፡፡ መተማ ሲደርሱም ጣሰው ለደላላ ሰሚራን ሰጥቶ ወደቀዬው ተመለሰ፡፡

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ከመጀመሪያው አንቀጽ ምን እንደተገነዘቡ ይጠይቋቸው፡፡አንቀጹንም እንደገና ያንብቡላቸው፡፡የሚሰጡት መልስ ከአንቀጹ ውጭ እንዳይሆን ይከታተሉና ያርሟቸው፡፡
2. ከመጀመሪያው አንቀጽ ቀጥለው ያሉ ምን መልእክት እንደሚያስተላልፉ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
3. በቀጣይ በሚያነቡት አንቀጽ ውስጥ ሰሚራን ምን ያጋጥማታል ብለው እንደሚያስቡ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

የሰሚራ ቤተሰቦች ልጃቸው ከምን እንደደረሰች ጣሰውን ሲጠይቁት እንደሷ ወደውጭ ሀገር የሚሄዱ ብዙ ወጣቶች እንዳሉና እሷም በደስታ ወደሱዳን እንደተጓዘች ነገራቸው፡፡ ምንም ልባቸው ቢጨነቅ ልጃቸው እንደሷ ወደባእድ ሀገር ብቻዋን እንዳልሄደች ስለተነገራቸው እፎይታን አግኝተዋል፡፡ ሰሚራ ከቤተሰቦቿ ከተለየች ቀናቶች አለፉ፡፡ የሰሚራ ቤተሰቦች የልጃቸው ትንፋሽ መኖር አለመኖር ለማረጋገጥ አልቻሉም፡፡ጣሰውን ቢጠይቁትም ገና ስላልተረጋጋች እንጂ ትደውላለች እያለ ያሞኛቸዋል፡፡እነሰሚራን ይዞ ከመተማ በለሊት ይዟቸው በረሃ ውስጥ ሲያንከራትታቸው የነበረ ደላላ ህግ አስከባሪዎች ተከታትለው ስለደረሱባቸው እነሱን እዛው ጥሎ ጠፋ፡፡ እነሰሚራም ተይዘው መተማ ፖሊስ ጣቢያ ታሰሩ፡፡ ሰሚራም ብዙ ተንገላታች፣ ተራበች፣ ተጠማች፣ ታመመች፡፡ ከብዙ ስቃይ በኋላ ለቤተሰቦቿ ተደውሎ አባቷ ሄደው ልጃቸው በደላላ ተታላ ለዚህ ሁሉ ችግር የተጋለጠች መሆኑን ህግ አስከባሪዎች አስረዷቸው፡፡ ሰሚራም ከስህተቷ ተምራ ለአከባቢው ሰው ጥሩ ግንዛቤ እንድትፈጥር ተመክራ ወደሀገሯ ተመለሰች፡፡

ጣሰው በፈጸመው ወንጀል ተከሶ ተፈረደበትና ማረሚያ ቤት ገባ፡፡ እሷም ቤተሰቦቿን ይቅርታ ጠይቃ ወደትምህርቷ ተመልሳ ጥሩ ውጤት አምጥታ ያዘኑባትን ቤተሰቦቿን ለመካስ ቃል ገባች፡፡

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከተራቁጥር 1-5 የቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎችም ተገቢውን መልስ እንዲመልሱ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

# ትምርት ሁለት፡ መናገር

1. ወጣቶች በህገወጥ ደላሎች በመታለል ትምህርታቸውን አቋርጠው ከመሰደድ እንዲቆጠቡ መፍትሄ ይሆናል ብለው የሚያስቡትን በቡድን በመሆን ከተወያዩ በኋላ ሀሳባቸውን በተወካያቸው አማካይነት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

2. ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸው በህገወጥ መንገድ እንዳይሰደዱ ማድረግ ያለባቸዉን መፍትሄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያዩ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ንባብ

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከተራቁጥር 1-3 የቀረቡት ጥያቄዎች በህገወጥ ሰዎች ዝውውር ዙሪያ የተማሪዎችን የቀደመእውቀት የሚቀሰቅሱ ናቸው፡፡ ተማሪዎችም የቀደመእውቀታቸውን ተጠቅመው ተግባራቱን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ እያነበቡ በመሀል ቆም እንዲሉ በማድረግ እስካሁን ካነበቡት ምንባብ ቁልፍ ቃላትን እንዲመዘግቡ፣ ከመጀመሪያው አንቀጽ ምን ፍሬ ነገር እንዳገኙ በመጠየቅ እንዲመልሱ ይዘዟቸው፡፡ ቀጥሎ የሚመጣው ምንባብ ስለምን እንደሚያወሳ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

# አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

ሀ. ተማሪዎች ከተራቁጥር 1-5 ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎቹ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን መልስ በመከተልም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ተማሪዎች ከተራቁጥር 1-5 ለቀረቡት ቃላት ፍች እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችንም መልስ በመከተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ስለገላጭ ድርሰት የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ በማድረግ ስለገላጭ ድርሰት እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎቹም ሲወያዩ በመከታተል የሚታገዙ ተማሪዎችን በማገዝ ጥሩ ተሳትፎ የሚያደርጉትን የበለጠ እንዲጠነክሩ ያበረታቷቸው፡፡ ስለገላጭ ድርሰት በሚከተለው መልኩ የቀረበውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

## ገላጭ ድርሰት

አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ ወይንም እንደሚፈጸም የሚያመላክት ወይንም የሚመራ ድርሰት ገላጭ ድርሰት በመባል ይታወቃል፡፡

ምሳሌ፡- ነፋስ በአይን የማይታይ፣በእጅ የማይዳሰስ ሲነፍስ ስሜቱ ለፍጥረት ሁሉ የሚስማማ ነው፡፡ ይህ በራሪ አየር ተለይተው ከታወቁት አየሮች ከኩሬና ከሀይቅ፣ከባህርና ፈሳሾች፣ በጸሀይ ሀይል ተነስቶ ባየር ውስጥ ከሚዛወረው እንፋሎት፣ ካትክልት ርግፍጋፊ፣ ካቧራ ባየር ውስጥ ከሚገኙት ከጥቃቅን ነገሮችና ተባዮች ይመሰረታል፡፡

*(ብርሃኑ ገ/ጻዲቅ፡፡1997፡፡ አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መመሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡)*

**ተግባር ሁለት**

ሀ.የቀረበውን ገላጭ ድርሰት ማስታወሻ ከወሰዱና ስለገላጭ ከተወያዩ በኋላ ከቀረበላቸው ርእስ አንድ ርእስ በመምረጥ በገላጭ ድርሰት ሁለት አንቀጽ ድርሰት እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ለቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲወስዱ በማድረግ በርእሰ ጉዳዩ ላይ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ ማስታወሻውም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

**የቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ**

ቃላት በቀጥታ ከሚታየው ፍች በተዘዋዋሪ ሌላ ትርጉም በሚይዙበት ጊዜ የቃላት ፍካሬያዊ ፍች ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ወንበር

1. የተቀመጥኩበት **ወንበር** አዲስ ነው፡፡

ለመቀመጫነት የሚያገለግል (እማሬያዊ ፍች)

2. ወይዘሮ ማዘንጊያ የፖለቲካ **ወንበር** ያዙ፡፡

ወንበር- ስልጣን አገኙ

**መልመጃ ሶስት**

ሀ. ተማሪዎች ከተራቁጥር 1-10 ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**መልመጃ አራት**

ሀ. ከተራቁጥር 1-10 ለቀረቡ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች ለሚመልሱት መልስ ተገቢውን ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

**ተግባር አራት**

ሀ. ተማሪዎች ለእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አስር ቃላትን ከራሳቸው አእምሮ በማመንጨት ለመምህራቸው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

ለ. በ ሀ ስር የጻፏቸውን ቃላት ፍካሬያዊ ፍች እንዲሰጡ እና ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱባቸው ያድርጉ፡፡ የተማሪዎችን መልስ በመከተል ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

የአረፍተነገር አገልግሎት የሚለውን ርእስ በማቅረብ ተማሪዎች በዚህ ርእስ ዙሪያ ከዚህ በፊት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ካወያዩዋቸው በኋላ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡ማስታወሻውም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

## የአረፍተነገር አገልግሎት

ዓረፍተነገሮች ከአገልግሎታቸው አንጻር በአራት ይከፈላሉ። እነሱም፡-

ሀ. ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር

ለ. ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር

ሐ. አጋኗዊ ዓረፍተ ነገር

መ. ትእዛዛዊ ዓረፍተ ነገር

1. **ሀተታዊ ዓረፍተነገር፡** እውናዊ መረጃ ወይም ሃሳብ የሚገለጽባቸው ዓረፍተነገሮች ናቸው። ሀተታዊ ዓረፍተነገር በአዎንታዊና አሉታዊ መልኩ ሊቀርብ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡ ሀ. ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር 1. ዛሬ በጣም ደክሞኛል።
2. ታደሰ ወደቤቱ ሂደ፡፡
ለ. አሉታዊ ዓረፍተ ነገር 1. ሳምራዊት ወደትምህርት ቤት አልሄደችም።
2. አህመድ ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ አልመጣም፡፡

2. **ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር፡** ሁልጊዜ ጥያቄ ይጠይቃል። በአረፍተነገሩ መጨረሻም ጥያቄ ምልክት ይኖረዋል። ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር ምን ጊዜም መልስ ይሻል፡፡ መልሱ አጭር ወይም ረጅም ሊሆን ይችላል፡፡

ምሳሌ፡ ሀ. ቁርስህን በልተሃል?

ለ. የቡድን ሥራችሁን አጠናቀቃችሁ?

**መልመጃ አምስት**

ሀ. ተማሪዎች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ሶስት ሶስት አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተነገሮችን እንዲገነቡ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስም ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

በዚህ ክፍለጊዜ ባለፈው ክፍለጊዜ የቀረበላቸውን አገልግሎታዊ አረፍተነገር በማስታወስ የቀሩትን የአረፍተነገር አገልግሎት አይነቶችን በሚከተለው መልኩ አቅርቦ ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ መልመጃዎችንም እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

## የዓረፍተ ነገር አገልግሎት

3. **ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር፡-** ትዕዛዝን ለማስተላለፍ የሚያገለግሉ ዓረፍተነገሮች ናቸው። ፍላጎታዊ መልዕክት ይተላለፍባቸዋል፡፡

   ምሳሌ፡ እባክህ፤ መስኮቱን ዝጋው!

4. **አጋኖአዊ ዓረፍተነገር፡** አጋኖአዊ ዓረፍተ ነገር ከውስጥ ፈንቅለው የሚወጡ ድንገተኛና ስሜታዊ ጉዳዮችን መግለጫ ነው። ድንጋጤን፣ አድናቆትን፣ ግርምትን ወይም ቁርጠኛነትን ለመግለፅ የሚዋቀር ዓረፍተነገር ሁሉ አጋኖአዊ ዓረፍተነገር ይባላል።

   ምሳሌ፡ እንደሌንሳ የሚያምር አይቼ አላውቅም!

**መልመጃ ስድስት**

ሀ. ተማሪዎች የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ አጋኖአዊና ለትእዛዛዊ አረፍተነገር ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ስድስት ስድስት አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች በቢጤ እርማት እንዲገማገሙ ካደረጉ በኋላ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## 4. ግምገማ

- ለማዳመጥ የተዘጋጀ ምንባብ ከመቅረቡ በፊት የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ ተግባራትን አቅርቦ እንዲሰሩ ማዘዝ
- የአዳምጦ መረዳት ምንባብ ሲቀርብ እያዳመጡ ስላለው ምንባብ ማስታወሻ እንዲይዙ ማዘዝና ምንያህል እንደተረዱ የቃል ጥያቄ ማቅረብ
- ቀጣይ አንቀጽ ስለምን እንደሚገልጽ እንዲገምቱ የቃል ጥያቄ ማቅረብ
- ስላዳመጡት ምንባብ ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ መጠየቅ
- በተለያዩ ርእሰጉዳዮች ላይ መረጃ በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ እንዲወያዩና እንዲናገሩ መጠየቅ
- ቅድመንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ መጠየቅ
- ንባቡን ቆም በማድረግ እያነበቡ ያሉትን ምን ያህል እየተገነዘቡ እንደሚያነቡ የቃል ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም እንዲሰጡ መጠየቅ
- ገላጭ ድርሰት እንዲጽፉ መጠየቅ
- ለቃላት አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እንዲሰጡ መጠየቅ
- የአረፍተነገር አገልግሎት ምንነት እንዲገልጹ መጠየቅ
- የአረፍተነገር አገልግሎት አይነቶችን በመዘርዘር ምሳሌ እንዲያቀርቡ ማዘዝ

# የተመረጡ የመልመጃ መልሶች

**መልመጃ ሁለት**

**ለ. ለቃላት ፍች መስጠት**

1. ህገወጥ - ህግን ያልተከተለ
2. ሙስና - ከሰዎች ባልተገባ መንገድ ጥቅም ለማግኘት መሞከር
3. ንቅዘት - ችግር
4. መመልመል - መምረጥ
5. ወንጀል - በደል
6. ምህዳር - አቅጣጫ/እይታ

7. ተበዳይ - ተጎጂ
8. መዳረሻ - ማብቂያ
9. መገለል - መራቅ
10. ማዛባት - ማዘበራረቅ

**መልመጃ አራት**

ሀ. በአረፍተነገር ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ስጡ፡፡

| | እማሬያዊ | ፍካሬያዊ |
|---|---|---|
| 1. ምስጥ | የጉንዳን ዘር | መሰሪ/ተንኮለኛ |
| 2. ቋንጣ | ደረቅ ስጋ | ቀጭን |
| 3. ኤሊ | የዱር እንስሳ | ዘገምተኛ |
| 4. ጅብ | የዱር እንስሳ | ጉልበተኛ/ገብጋባ |
| 5. ድንጋይ | ለቤትና ለተለያዩ ግንባታ የሚውል | ጠንካራ/የማይገባው |
| 6. ንብ | በራሪ ነፍሳት | ታታሪ |
| 7. ተርብ | በራሪ ነፍሳት | ምላሰኛ/ተናዳፊ |
| 8. በግ | የቤት እንስሳ | የዋህ |
| 9. እባብ | ተናዳፊ የዱር እንስሳ | ተንኮለኛ/መሰሪ |
| 10.እርግብ | በራሪ ወፍ | የሰላም ተምሳሌት/የዋህ |

# ምእራፍ ሰባት

# ማህበራዊ ግንኙነት

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት)**

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የሚቀርብላቸውን ምንባብ ፍሬ ሀሳብ በማዳመጥ ይናገራሉ፡፡
- ስለማህበራዊ ጉዳይ ይገልጻሉ፡፡
- ተዘውታሪና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለተግባቦት ይጠቀማሉ፡፡
- በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው ጽሁፎችን ያዘጋጃሉ፡፡
- ተመሳሳይ ፍች ያላቸውን ቃላት ያዛምዳሉ፡፡
- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- ምንባብ ማዳመጥ
- የማዳመጥ ተግባራትን መስራት

### 2.2. መናገር

- ክርክር
- በተሰጠው ርእሰጉዳይ ላይ መከራከር
- የተሰበሰበውን መረጃ በንግግር ማቅረብ

### 2.3. ማንበብ

- የቅድመና የንባብ ጊዜ ተግባራት
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች
- ፈሊጣዊ አነጋገር
- ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች መስጠት

### 2.4. መጻፍ

- ማህበራዊ ኑሮን የሚያጠናክሩ ጽሁፎችን መጻፍ

### 2.5. ቃላት

- ለቃላት ፍች መስጠት
- የቃላት አንድነትና ልዩነት
- ሰዎች ተገናኝተው ስለኑሮዋቸው የሚነጋገሩበትን አጋጣሚዎች የሚገልጹ ቃላትና ሀረጋት መግለጽ

### 2.6. ሰዋስው

- የአረፍተነገሮችን አገልግሎት አይነቶች ዓረፍተነገር መገንባት
- ለአረፍተነገር አገልግሎት ምሳሌ መስጠት

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ስለሚያዳምጡት ምንባብ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲገምቱ ማድረግ
- ያዳመጡትን ምንባብ ፍሬ ሀሳብ እንዲገልጹ ማድረግ
- የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም ስለሚያነቡት ነገር እንዲተነብዩ ማድረግ
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲገልጹ ማድረግ
- እያነበቡ እያለ ቆም ብለው ያነበቡትን ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ ማድረግ
- ከምንባቡ ለወጡ መልመጃዎች ምሳሌ በመስጠት በምሳሌው መሰረት እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ለቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- በቡድን ተከፋፍለው በቀረቡት ርእሰጉዳዮች ላይ እንዲከራከሩ ማድረግ
- ለሚቀርበው ምንባብ የቀደመእውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲተነብዩ ማድረግ
- ምንባቡን እንዲያነቡ ማዘዝ
- ስለምንባቡ የተረዱትን እንዲናገሩ ማድረግ
- ከምንባቡ የወጡትን መልመጃዎቹ እንዲመልሱ ማዘዝ
- በየምእራፉ የቀረቡ ተግባራት ላይ ተወያይተው መልስ እንዲሰጡ ማዘዝ
- አንቀጽ ጽፈው እንዲያቀርቡ ማዘዝ

- ለአረፍተነገር አገልግሎት ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከተራ ቁጥር 1-2 ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት በማድረግ መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

## ዕድር

ዕድር አባላቱ በፈቃደኝነት የሚመሰርቱት፣ በመተሳሰብ የሚረዳዱበት፣ የሚተጋገዙበት፣ የሚማማሩበት፣ አንዱ የሌላውን ችግር የሚካፈልበት እና ለቀጣዩ ትውልድ አውርሰው የሚያልፉት ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ ዕድርተኞች ዕድርን ከሀዘን ጋር አያይዘው ይገልጹታል፡፡ ዕድር ማለት ቀባሪ ደግ ጎረቤት ነው፣ በችግር ቀን ከዘመድ ቀድሞ ደራሽ ነው፡፡

ዕድር መግባት አለመግባት ማኅበራዊና ስነልቦናዊ ጫና አለው። ዕድር በገባና ባልገባ ሰው የሚሰጠው አገልግሎት ይለያያል። ዕድር አለመግባት ለነገ አለማሰብ፣ ኃላፊነትን አለመወጣት፣ ራስን ከማህበረሰቡ እንደማግለል ይቆጠራል።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እዚህ ጋር ምንባብዎን ቆም በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

1. መምህራችሁ ጽሁፉን ሲያነቡላችሁ አዳዲስ ቃላትን በመለየት በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. የሚቀጥለው ጽሁፍ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

ዕድሮች በቃል የሚተላለፉ ተግባራትና ደንቦች ነበሩዋቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ዓላማና ደንቦችን በፅሑፍ ማስፈር የተለመደ አሠራር እየሆነ መጥቷል፡፡ የየዕድሮቹ መተዳደሪያ ደንቦችና ዓላማዎች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ቢሆንም በአደረጃጀት ወይም በአወቃቀርና በአባላት ብዛት አንዱ ከሌላው ይለያያሉ፡፡ ደንቦቹም ስለ ዕድርተኞች አባልነት መሥፈርቶች፣ የአባላት መብቶችና ግዴታዎች፣ ስለ ዕድር ዓይነቶች፣ ተግባርና አገልግሎት፣ ስለ መሪዎች ወይም ስለ አስተባባሪዎች በዝርዝር የሚገልፁ ሆነው ይገኛሉ።

ዕድር የሚተዋወቁ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠርቱት ባህላዊ-ማህበራዊ ተቋም በመሆኑ መሥራቾቹ ከመተዋወቅ አልፎ የጋራ ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡ ፍላጎቱ የሚመጣው በመቀራረብና አንዱ ሌላውን በማክበር፣ በመተሳሰብ እና አንዱ ለሌላው መኖር እውቅና በመስጠት ነው፡፡

*ምንጭ (ዜና ልሳን Zena-Lissan Volume XXVI Number 2 December 2017(http://ejol.ethernet.et)*

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-6 ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት አድርገው እንዲመልሱ ይዘዟቸው፡፡ ለምሳሌ ለአንደኛ ጥያቄ በሚከተለው መልኩ መልስ መስጠታቸውን ይከታተሉ፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-10 ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍችያቸውን ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ. ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ሁለት ተመጣጣኝ የሆኑ ሀሳቦችን በመምረጥ በእጣ እንዲደርሳቸው በማድረግ እንዲከራከሩ ያድርጉ፡፡ ክርክሩን የሚቆጣጠሩ ሶስት ተማሪዎችን በመምረጥ አንደኛውን ዳኛ ሌለኛውን ጸሀፊ ሶስተኛውን ሰዓት ያዥ በማድረግ የስራ ድርሻቸውን ይስጧቸው፡፡ ለተከራካሪዎች ጊዜ በመስጠት በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ሀሳባቸውን እንዲያጠቃልሉ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በዳኝነት የተመረጡ ተማሪዎች በምክንያት የአሸናፊውን ቡድን ነጥብ በመግለጽ ክርክሩ እንዲያበቃ ያድርጉ፡፡

ለ. ከክርክሩ የተገነዘቡትን ተማሪዎችን ተራ በተራ እንዲገልጹ በማድረግ መጨረሻ ላይ ማጠቃለያ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

### ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ስር ተማሪዎች በሚኖሩበት አከባቢ ሰዎች የሚረዳዱበትን ማህበራዊ አጋጣሚ በተመለከተ መረጃ በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በንግግር ሲያቀርቡ ማን በጥሩ ሁኔታ እንዳቀረበ በምክንያት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ስለእቁብ ከዚህ በፊት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ እቁብ በማህበራዊ ግንኙነት የሚኖረውን አስተዋጽኦ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

# እቁብ

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ምንባቡን እያነበቡ ቆም እንዲሉ በማድረግ እስካሁን ያነበቡትን ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
2. በቀጣይ ከምንባቡ ምን ምን ሀሳቦችን ማግኘት እንደሚችሉ እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-7 የቀረቡት ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ግን ሀሰት በማለት እንዲመልሱ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ከቀረቡት ጥያቄዎች ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት ከተሰጡት አማራጮች ፍች ሊሆኑ የሚችሉትን እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ተገቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

በዚህ ክፍለጊዜ ፈሊጣዊ አነጋገርን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ ከመውሰዳቸው በፊት ስለፈሊጣዊ ምንነት ያወያዩዋቸው፡፡ማጠናከሪያ ሀሳብ ከሰጧቸው በኋላ ማስተወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡

**ፈሊጣዊ አነጋገር**

በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እየቀላቀሉ መጠቀሙ ጥልቅና ምጥቀት ያላቸው ሀሳቦችን ለማስተላለፍ ከማስቻሉም በላይ የቋንቋ ችሎታንም ለማስገንዘብ አይነተኛ ማስረጃ ይሆናል፡፡

ምሳሌ፡- እንድ ሰው የተስማሙበትን ሀሳብ መልሶ የሚያፈርስ ሰው ቢያጋጥመው በአጭር አገላለጽ፣ አንተ! ሁለት ምላስ አለህ፡፡ በማለት ሊገልጽ ይችላል፡፡

የቀረበላቸውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ከተራ ቁጥር 1-4 ለቀረቡት ፈሊጣዊ አባባሎች ትርጉም እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውን ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ተግባር ሶስት**

በቡድን በመሆን ሰዎች ለተለያዩ ጉዳዮች የሚጠቀሙባቸውን አስር ፈሊጣዊ አባባሎችን ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በማሰባሰብ አገልግሎታቸውን በዓረፍተነገር ውስጥ በማስገባት ለክፍል ጓደኞቻቸው በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡ ሰውየው ብሩን ቶሎ ስላልተመለሰለት ደሙ ፈላ፡፡ **ተናደደ**

**መልመጃ ሶስት**

ከተራ ቁጥር 1-9 ለቀረቡት ፈሊጣዊ አባባሎች ተቃራኒ ፍች እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውን ግብረመልስም ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**ተግባር አራት**

1. ማህበረሰቡ አብሮ ሲኖር አብሮ እንዲኖር ከሚያጠናክሩት አንድ ምሳሌ ቀርቧል፡፡ ሌሎችን በምሳሌው መሰረት በተዘጋጀው ቦታ እንዲሞሉ ይዘዟቸው፡፡
2. በምንባቡ መግቢያ "ለሰው መድሃኒቱ ሰው ነው" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የያዘውን መልእክት አስፋፍተው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡
3. ሌሎች ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ቤተሰብ በመጠየቅ መዝግባችሁ የሚያስተላልፉትን መልእክት በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ አስር**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

***መልመጃ አራት***

በ ሀ ስር ለቀረቡት ቃላት ከለ ስር ፍችያቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ ሊሆን የሚችል አንድ ጥያቄ ይስሩላቸው፡፡

**ተግባር አምስት**

በሚከተሉት ቃላት መካከል ያለውን እንድነትና ልዩነት በቡድን ሆነው ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን ሀሳብ ለመምህራቸው በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

እድር እና እቁብ

ደቦ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

***መልመጃ አምስት***

*ተማሪዎች ከዚህ በታች ሰዎች ተገናኝተው ስለኑሮዋቸው የሚነጋገሩበትን አጋጣሚዎች የሚገልጹ ቃላትና ሀረጋት ተዘርዝረዋል በምሳሌው መሰረት በተጠቀሱት መገናኛ ቦታዎች የሚያነሱትን ሀሳብ በጽሁፍ እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡*

ምሳሌ፡ የቀበሌ ስብሰባ

በቀበሌያቸው ስለሚደረጉ ልማቶች ይነጋገራሉ፡፡

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

***መልመጃ ስድስት***

ሀ. በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ምሳሌ በማድረግ ለዓረፍተነገር አገልግሎት አይነቶች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ዓረፍተነገሮችን በመመስረት በትክክለኛው ቦታቸው አስገቡ፡፡

ለ. ከዚህ ቀደም አረፍተ ነገሮች ከአገልግሎታቸው አንጻር በአራት እንደሚመደቡ የተማሩትን በማስታወስ በአራቱ የአረፍተነገር አገልግሎት አይነቶች ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ የሚሆኑ ሶስት ሶስት አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

## 4. ግምገማ

- ለማዳመጥ የተዘጋጀ ምንባብ ከመቅረቡ በፊት የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ ተግባራትን አቅርቦ እንዲሰሩ ማዘዝ
- የአዳምጦ መረዳት ምንባብ ሲቀርብ እያዳመጡ ስላለው ምንባብ ማስታወሻ እንዲይዙ ማዘዝና ምንያህል እንደተረዱ የቃል ጥያቄ ማቅረብ
- ቀጣይ አንቀጽ ስለምን እንደሚገልጽ እንዲገምቱ የቃል ጥያቄ ማቅረብ
- ስላዳመጡት ምንባብ ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ መጠየቅ
- በተለያዩ ርእሰጉዳዮች ላይ መረጃ በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ እንዲወያዩና እንዲናገሩ መጠየቅ
- ቅድመንባብ ተግባራትን እንዲሰሩ መጠየቅ
- ንባቡን ቆም በማድረግ እያነበቡ ያሉትን ምን ያህል እየተገነዘቡ እንደሚያነቡ የቃል ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ቃላትን በተመሳሳይ ፍቺ እንዲያዛምዱ መጠየቅ
- ስለማህበራዊ ግንኙነት ጠቀሜታ ድርሰት እንዲጽፉ መጠየቅ
- ስለማህበራዊ ግንኙነት ጠቀሜታ በተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በመጠቀም አሳጥረው እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- የአገልግሎታዊ አረፍተነገር ክፍሎችን መጠየቅ

# የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

**መልመጃ አንድ**

| | |
|---|---|
| 1. ለ | 6. መ |
| 2. መ | 7. ለ |
| 3. መ | 8. ሀ |
| 4. ሐ | 9. ሐ |
| 5. ሀ | 10. መ |

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. እውነት/ሀሰት**

1. ሀሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. እውነት
7. ሀሰት

**ለ.ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. ለ
5. መ

**መልመጃ ሶስት**

**ፈሊጣዊ አባባሎች/አነጋገሮች ፍች መስጠት**

1. መላቢስ - መላ ያጣ
2. አይን አውጣ - እፍረት የሌለው
3. ጆሮጠቢ - ወሬ የሚለቃቅም
4. ሆደባሻ - ቶሎ የሚከፋ
5. እጁ አጠረ - ተቸገረ፣ ደኸየ
6. እግረደረቅ - እድል የሌለው
7. ጥላቢስ - ቀዥቃዣ
8. የአዞ እምባ - የውሸት ሀዘን
9. ጥርሰ ፍንጭት- ምስጢር የማይዝ

**መልመጃ አራት**

**ሀ. አዛምዱ**

1. ቀ
2. በ
3. ረ
4. ሀ
5. ሰ
6. ሸ
7. ሠ
8. መ
9. ለ
10. ሐ

# ምእራፍ ስምንት

## ሱሰኝነት

**(ዘጠኝ ክፍለጊዜ)**

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለሱሰኝነት ተጽእኖ ይገልጻሉ፡፡
- ያዳመጡትን ጽሁፍ ፍሬ ሀሳብ ይገልጻሉ፡፡
- ሀሳብን እንደገና በማቀናጀት በንግግር ያቀርባሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ፡፡
- ለተዘውታሪ ቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- የቅድመ እና የማዳመጥ ተግባራት
- የምንባብ ፍሬ ሀሳብ መግለጽ
- ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት

### 2.2. መናገር

- የጽሁፍ ፍሬ ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ በቃል ማቅረብ
- የአልኮል መጠጥ በተመለከተ ዘገባ ማቅረብ

### 2.3. ንባብ

- የቅድመ እና ድህረ ንባብ ተግባራት
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

### 2.4. መጻፍ

- ስርዓተ ነጥብ
- አንድ ነጥብ ተጠቅሞ ቃላትን/ሀረጋትን አሳጥሮ መጻፍ

- ሁለት ነጥብ ተጠቅሞ ሰዓትንና ደቂቃን ለይቶ መጻፍ
- ሁለት ነጥብ ከሰረዝ አገልግሎት
- ነጠላ ሰረዝ አገልግሎት
- አራት ነጥብ
- ለአረፍተነገሮች ተገቢውን ስርዓተነጥብ መጠቀም

2.5. **ቃላት**

- ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት

2.6. **ሰዋስው**

- ድርብ አረፍተነገር

## 3.የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ እውቀታቸውን የቀረቡትን ተግባራት በማሰራት መቀስቀስ
- የማዳመጥ ምንባብ በማቅረብ መልመጃዎችንና ተግባራትን ማሰራት
- ምሳሌዎችን በማቅረብ ለቃላት አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- ያዳመጡትን ምንባብ ፍሬ ሀሳብ በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ
- የአልኮል መጠጥ በጤና ላይ ያለውን ጉዳት ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ቅድመ ንባብ ተግባራትን ማሰራት
- የንባብ ጊዜ ተግባራትን ማሰራት
- ሀሳባቸውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ማበረታታት
- ከስርአተነጥቦች የተወሰኑትን በማቅረብ የቀረቡት ስርዓተ ነጥቦች አገልግሎታቸውን በዓረፍተነር ውስጥ እንዲያመለክቱ ማድረግ
- የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የስርአተነጥቦችን አገልግሎት እንዲዘረዝሩ ማበረታታት
- ተገቢውን ስርዓተነጥብ እንዲጠቀሙ ምሳሌዎችን በማቅረብ ምሳሌውን ተከትለው አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ
- ለቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ማበረታታት
- ድርብ አረፍተነገሮችን ምንነት እንዲገልጹ መነሻ ሀሳብ በመስጠት ማወያየት

- አረፍተነገሮችንና አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ድርብ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

*ሀ. ከተራ ቁጥር 1- 2 ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ ሀሳባቸውን በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡*

## የሱሰኝነት ተጽዕኖ

ሱስ አንዴ ከተለመደ በኋላ በየጊዜው ውል የሚል አምሮት ወይም አምጡ አምጡ የሚያሰኝ ልማድ ነው። ሱስ ከሚያስይዙ ነገሮች ዋና ዋናዎቹ ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃም፣ አልኮል መጠጣት ይጠቀሳሉ።

ከሱስ አስያዥ ነገሮች አንዱ የሆነው ሲጋራ በውስጡ ኒኮቲን የሚባል ንጥረነገር እና ልዩ ልዩ ኬሚካሎች ስለያዘ፣ የማነቃቃትና ሱስ የማስያዝ ኃይል አለው። በዚህ ምክንያት ሲጋራ ማጨስ ለሳንባ ካንሰርና ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል። ጥናቶች እንዳረጋገጡት ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች ከማያጨሱት ሰዎች ጋር ሲነጻፀሩ በሳንባ ካንሰር የመጠቃት ዕድላቸው አሥር እጥፍ ይሆናል። የሲጋራ ሱስ ከጤና ችግር በተጨማሪ ለምጣኔ ሀብታዊ ችግር ያጋልጣል። በተጨማሪም በሲጋራ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ካላጨሱ የመበሳጨትና የመነጫነጭ ስሜት ስለሚፈጥርባቸው ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወን ይሳናቸዋል።

እንደሲጋራ ማጨስ ሁሉ ጫት መቃም ሱስ ያስይዛል። ጫት የአደንዛዥነትና ለሱስ ተገዢ የማድረግ ኃይል አለው። በዚህ ምክንያት በሱሰኞች ላይ የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል። በጫት ሱስ መጠመድ የሥራ ባህልን ስለሚጎዳ ለግለሰብም ሆነ ለሀገር እድገት ፀር ይሆናል። በተለይ ወጣቶች አፍላ ዕድሜያቸውን በትምህርትና በሥራ እንዳያሳልፉ እንቅፋት በመሆን ለቦዘኔነት፣ ለድብርትና ለብስጭት ይዳርጋቸዋል።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እያነበቡ ያሉትን ጽሁፍ እዚህ ጋር ቆም በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቅርቡላቸው፡፡

1. ጽሁፉ ሲነበብላችሁ አዳዲስ ቃላት ናቸው የምትሉትን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡

2. ጽሁፉን እያዳመጣችሁ በምክንያትና ውጤት የተሳሰሩ ዓረፍተነገሮችን መዝግቡ፡፡

የአልኮል መጠጥ ከጫትና ከሲጋራ ባልተናነሰ ሁኔታ ለሱሰኝነት ያጋልጣል። የአልኮል ሱስ ለጤና ችግሮችና ለጉስቁልና ይዳርጋል። መጠጥ ስካርን ስለሚያስከትል ለጠብና ለሌሎች አደገኛ ወንጀሎች ያጋልጣል። በስካር መንፈስ ጥፋት የሚሠሩ ሰዎች ስካሩ ካለፈላቸው በኋላ በሠሩት ሥራ ይፀፀታሉ። ይህ ደግሞ ተደጋጋሚ ብስጭት ስለሚፈጥር የጤና ችግር ያስከትላል።

በአጠቃላይ ሱሰኝነት ማህበራዊ ተቀባይነትን ስለሚያሳጣ ለማህበራዊ ሕይወት እንቅፋት ይሆናል። ሱሰኞች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን የቆየ ግንኙነት በማቋረጥ ለብቸኝነት ይጋለጣሉ። በዚህም ምክንያት ሱሰኞች ራሳቸውን እስከማጥፋት ሊደርሱ ይችላሉ። ስለዚህ ሱሰኝነት ለተለያዩ ችግሮች የሚያጋልጥ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከተራቁጥር 1-9 ላሉት ጥያቄዎች ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚመልሱት ነው፡፡ ምንባቡን በድጋሚ አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ካዳመጡት ምንባብ መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ለሱስ የሚያጋልጡ ነገሮች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ እና በጤና ላይ የሚያስከትሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በቢጋር ሰንጠረዥ ውስጥ እንዲያመለክቱ

ያድርጉ፡፡ እንደመርጃ መሳሪያም የሚያገለግሉ ሰንጠረዦችን በቻርት ላይ በማዘጋጀት ለታማሪዎች ያቅርቡ፡፡ ተማሪዎችም ሰርተው እንዲመጡ ያበረታቷቸው፡፡

**መልመጃ ሁለት**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-9 የቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን ፍች የያዘውን ቃል እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመከተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለምሳሌ፡. ሱስ አንዴ ከተለመደ በየጊዜው <u>አምጡ አምጡ</u> የሚያሰኝ ልማድ ነው፡፡

ሀ. አድርጉ ሐ. ብሉ

ለ. አትውሰዱ መ. አገናኝ

ከነዚህ አማራጮች **ሀ. አድርጉ** የሚለው መልስ እንደሚሆንና ይህንንም እንዲመርጡ ይጠበቃል፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

1. ያዳመጡትን ምንባብ ፍሬ ሀሳብ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ በማድረግ የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ከሚመልሱት ነገር በመነሳት ትክክለኛውን ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

2. ተማሪዎች የጤና ባለሞያዎችን በማማከር አልኮልነት ያላቸው መጠጦች በጤና ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ምን እንደሆነ መረጃ በማሰባሰብ ይዘው በመምጣት ክፍል ውስጥ በንግግር እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ክትትል ያድርጉ፡፡ ካቀረቡት በመነሳት ምን ግንዛቤ እንዳገኙ ይጠይቋቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-2 የቀረቡት ሀሳቦች ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ለቀረቡት ሀሳቦች ተማሪዎች የሚሰጡትን መልሶች በመከታተልና በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## የንባብጊዜ ጥያቄዎች

ከተራ ቁጥር 1-2 የቀረቡት ጥያቄዎች እያነበቡት ያለ ምንባብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ተማሪዎች ምንያህል እያነበቡ ያሉትን ምንባብ እንደተገነዘቡ ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ እያነበቡ ያሉትን ምንባብ በመሀል አቋርጠው ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡ ከተማሪዎች የሚገኘው ግብረመልስ ትክክል ካልሆነ እንደገና መልሰው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

# የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሶስት**

ከተራ ቁጥር 1-5 የቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ተማሪዎችም ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የሚሰጡት መልስ ከምንባቡ ፍሬ ሀሳብ ጋር የማይመሳሰል ከሆነ እንደገና እንዲያነቡና እንዲረዱ ምሳሌዎችን ከምንባቡ እየሰጧቸው ያለማምዷቸው፡፡

**መልመጃ አራት**

ሀ. ከምንባቡ ለተወሰዱ ቃላት በቡድን በመወያየት ፍቺያቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-4 ለቀረቡት ሀሳቦች ሱሰኝነት ምን አይነት ጉዳት እንደሚያደርስባቸው እንዲወያዩባቸው ያድርጉ፡፡ ከዚያም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

የአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ስርአተነጥቦችን በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማል፡፡ ከነዚህ ስርአተነጥቦች የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

1. አንድ ነጥብ .
2. ሁለት ነጥብ ፡
3. አራት ነጥብ ፡፡
4. ሁለት ነጥብ ከሰረዝ ፡-
5. ቃላአጋኖ !
6. ሶስት ነጥብ …
7. የጥያቄ ምልክት ?
8. ህዝባር /
9. ቅንፍ ( )
10. ትእምርተስላቅ ¡
11. ነጠላ ሰረዝ (፣)

እነዚህንና ሌሎች ስርአተነጥቦችን በመጠቀም በጽሁፍ መልእክት ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ ከላይ ከተዘረዘሩት ጥቂቶቹን በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

## ስርአተነጥብ

**ማስታወሻ**

ሰዎች በንግግር ሲግባቡ ድምጻቸውን ከፍ፣ዝቅ እንዲሁም ቆጣ በማለት ማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡ በጽሁፍ ሲግባቡ ግን ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ ካልተጠቀሙ በስተቀር ማስተላለፍ የፈለጉት መልእክት ግቡን አይመታም፡፡ በጽሁፍ ውስጥ ከምንጠቀምባቸው ስርዓተ ነጥቦች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**1. አንድ ነጥብ/ይዘት/.** አንድ ነጥብ ለሚከተሉት አገልግሎቶች ያገለግላል፡፡

አህጽሮተ ቃልን የሚመሰርቱ ሆሄያትን ለመለየት ምሳሌ፡ ከ.ነ.ማ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር

አንድን ቃል በተወሰኑ ሆሄያት አሳጥሮ ለማቅረብ ምሰሌ፡- ወሮ. ወይዘሮ

ብርና ሳንቲምን ለይቶ ለማመልከት ምሳሌ፡- 5.45 (አምስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም)

**2.ሁለት ነጥብ/ነቁጥ/፡** ሰዓትንና ደቂቃን ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡ 3፡40 (ሶስት ሰዓት ከአርባ ደቂቃ)

**መልመጃ አምስት**

ሀ. ቃላትና ሀረጋት አጥረው ሲጻፉ ማህበረሰቡ በለመዳቸው መልኩ መሆኑን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ከተራ ቁጥር 1-3 ላሉት ቃላትና ሀረጋት አንድ ነጥብ በመጠቀም አሳጥረው እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡ የቀረበውን ምሳሌ ደጋግመው ከተለማመዱ በኋላ መልመጃውን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የተማሪዎችንም መልስ በመከታተል ተገቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ሁለት ነጥብ በመጠቀም ሰአትና ደቂቃን በመለየት በምሳሌ ያሳዩዋቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ምሳሌውን ተከትለው ጥያቄ ቁጥር 1ና2 እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ተገቢውንም ግብረመለስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ስርዓተ ነጥብ**

3. **ሁለት ነጥብ ከሰረዝ** (፡-) ይህ ምልክት የዓረፍተነገር ሀሳብ ከማብቃቱ በፊት በዝርዝር የሚቀርቡ ነጥቦች መኖራቸውን ለማመልከት ያገለግላል፡፡

   ምሳሌ. የኤድስ መተላለፊያ መንገድ የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን እነዚህም፡- ልቅ የሆነ የግብረስጋ ግንኙነት፣ባልተቀቀለ መርፌ መጠቀም መሳሰሉት ናቸው፡፡

4. **ነጠላ ሰረዝ**(፣) በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተከታታይ ተደርድረው የሚቀርቡትን ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን የቃላት ክትትል ለመለየት ያገለግላል፡፡

   ምሳሌ፡- ከበደ መርካቶ ሄዶ ኮት፣ሱሪ፣ሸሚዝ፣የውስጥ ልብሶችና ጫማ ገዝቶ መጣ፡፡

   **5.አራት ነጥብ** (፡፡) የተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፍ ዓረፍተ ነገር መቋጫ ነው፡፡

   ምሳሌ፡- አበበ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

**መልመጃ ስድስት**

ሀ.ከተራ ቁጥር1-3 ላሉት አረፍተነገሮች ተገቢዎቹን ስርአተ ነጥቦች በተገቢው ቦታቸው በማስገባት የተሟላ አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ይርዷቸው፡፡ ከቀረቡት ጥያቄዎች ተራ ቁጥር አንድ ላይ የቀረበው <u>ልጁ መጽሃፉን ያነባል፡፡</u> በዚህ አረፍተነገር ውስጥ የገባው ስርአተነጥብ አራት ነጥብ ነው፡፡ ተማሪዎች በዚህ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ሀ. ተማሪዎች ከተራ ቁጥር 1-5 በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ይዘዟቸው፡፡ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ በመከታተል ተገቢውን ግብረመለስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ድርብ ዓረፍተነገር መመስረት**

ድርብ አረፍተነገር ሁለት ብቻቸውን ቆመው ሙሉ መልእክት ማስተላለፍ የሚችሉ አረፍተነገሮችን በአያያዥ ቃላት በማጣመር አረፍተነገሮቹ ሁለት ሳይሆኑ እንደ አንድ አረፍተነገር የማድረግ ተግባር ነው፡፡

ምሳሌ፡ ሀ 1. የእያንዳንዱ ቤተሰብ ቁጥር ጨምሯል።

2.የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ማደጉ አይቀርም።

የእያንዳንዱ ቤተሰብ ቁጥር ጨምሯል **ስለዚህ** የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ማደጉ አይቀርም። አጣማሪው አያያዥ ቃል **ስለዚህ** የሚለው ቃል ነው፡፡

ከቀረቡት ምሳሌዎች ነጠላ ዓረፍተነገሮችን በተለያዩ አያያገሮች በማጣመር ድርብ ዓረፍተነገር መመስረት መቻሉንና የሚጣመሩት (ነጠላ) ዓረፍተነገሮች የሃሳብ አንድነት ሊኖራቸው እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል።

### 4.ግምገማ

- የቀደመእውቀታቸውን ለመገምገም ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የማዳመጥና የማንበብ ጊዜ ላይ ያዳመጡትን/ያነበቡትን ምንባብ ምን ያህል እየተረዱ እያዳመጡ/እያነበቡ እንዳለ ለመረዳት የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ

- ምንባብን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከምንባቡ የተረዱትን እንዲገልጹ ማዘዝ
- ለቃላትና ሀረጋት ፍች እንዲሰጡ መጠየቅ
- ከቀረቡት አማራጮች ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት ትክክለኛ ፍች እንዲመርጡ መጠየቅ
- አልኮል መጠጦች በጤና ላይ የሚያደርሱትን ተጽእኖ በተመለከተ ባለሙያ ጠይቀው ዘገባውን በንግግር እንዲያቀርቡ ማዘዝ
- በቃላት የቋንቋውን መዋቅር በተከተለ መልኩ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ መጠየቅ
- የቀረቡትን አረፍተነገሮች ተገቢውን ስርአተነጥብ በማሟላት እንዲጽፉ ማዘዝ
- ነጠላ አረፍተነገሮችን በአያያዦች ተጠቅሞ ድርብ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ማዘዝ

# የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. ምርጫ**

1. ሀ
2. ሐ
3. ለ
4. መ
5. ሐ
6. ሀ
7. ለ
8. ለ
9. መ

**መልመጃ አራት**

**ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት**

1. ችግሮች
2. ግንኙነት
3. ሰውን የሚያደነዝዝ
4. የጭንቅላት ደህንነት
5. መራቅ
6. የሰው አካል ደህንነት
7. መቀነስ
8. እንዳይሰራ ማድረግ
9. ማስቸገር
10. ተቋም
11. አዲስ መንፈስ የሚገኝበት
12. ጥሩ መንፈስ አለመሰማት
13. እራስን አለመቻል
14. ጀግና
15. መስጠት
16. ስርዓት አለመያዝ
17. በተጨማሪ
18. መዘበራረቅ

**መልመጃ አምስት**

**ሀ.አንድ ነጥብ ተጠቅሞ ቃላትን አሳጥሮ መጻፍ**

1. ዓ.ም
2. ዶር.
3. 2.50

**ለ.ሁለት ነጥብ ተጠቅሞ ሰአት ማመልከት**

1. 6፡30
2. 12፡20

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ. ተገቢ ስርአተነጥብ ተጠቅሞ አረፍተነገር መመስረት**

1. ልጁ መጽሀፉን ያነባል፡፡
2. ጓደኞቹ ቶላ፣ ከበደ፣ ሕይወት እና ከሪም ናቸው፡፡
3. አለባቸው በግ፣ ፍየል፣ በሬ፣ ላም እና ፈረስ ያግዳል፡፡
4. ለቤት መስሪያ የተለያዩ ግብዓቶች ያስፈልጋሉ፡፡ እነሱም፡- እንጨት፣ ድንጋይ፣ ሲሚንቶ፣ አሸዋ፣ ሚስማር፣ ቆርቆሮ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
5. አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት ሲሄድ የሚከተሉት የመማሪያ ቁሳቁሶች ያስፈልጉታል፡፡ እነዚህም፡- ደብተር፣ እርሳስ፣ እስክሪፕቶ እና መጽሃፍ ናቸው፡፡

**መልመጃ ሰባት**

**ሀ. ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት**

1. የሚስቧቸው
2. ዋዛ
3. የፈተና ነጥብ
4. በሀብት ላይ
5. ምኞት

**መልመጃ ስምንት**

**ሀ. አያያዥ ቃላትን ተጠቅሞ ድርብ አረፍተነገሮችን መመስረት**

1. ሁልጊዜ ያረፍዳል **በዚህ ምክንያት** አባቱ በጣም ይናደዱበታል፡፡
2. የተማሩ እናቶች ልጆቻቸውን ያስጠናሉ **ስለሆነም** ልጆቻቸው ጎበዞች ናቸው፡፡
3. የክረምት ዝናብ በጥሩ ሁኔታ ዘንቧል **ይሁንእንጂ** የተዘራው እህል በደንብ አልበቀለም፡፡
4. በርትቶነግዷል **ነገር ግን** ብዙ ብር የለውም፡፡

# ምእራፍ ዘጠኝ

## አርበኝነት

**(ክፍለጊዜ አስራ ሁለት)**

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ያዳመጡትን ጽሁፍ መልእክት ከነባራዊ ህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- ስለአርበኝነት ጽንሰሀሳብ ይገልጻሉ፡፡
- ለውሱን አላማ ያነባሉ፡፡
- በተሰጣቸው ስእል ላይ መግለጫ ይጽፋሉ፡፡
- ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ድብልቅ ዓረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- ስለአርበኝነት መናገር
- ስላዳመጡት ምንባብ ፍሬ ሀሳብ መዘርዘር
- ለቃላት ተቃራኒ ፍች መስጠት

### 2.2. መናገር

- በቀረቡት ርእሶች ላይ መረጃ በማሰባሰብ በንግግር ማቅረብ

### 2.3. ማንበብ

- የቀደመእውቀትን የሚቀሰቅሱ ተግባራት
- የንባብ ጊዜ ተግባራት
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ መዘርዘር
- የቃላት ትርጉም ማዛመድ

2.4. **መጻፍ**

- የቀረበውን ምስል በመመልከት ከምስሉ የተረዱትን በጽሁፍ መግለጽ
- የምግብ አዘገጃጀት ቅደምተከተል መጻፍ

2.5. **ቃላት**

- ያልተሟሉ አረፍተነገሮችን አሟልቶ መጻፍ
- ቃላት በምንባብ ውስጥ የያዙትን ትርጉም መግለጽ

2.6. **ሰዋስው**

- ድብልቅ ዓረፍተነገር
- ዓረፍተነገሮችን ድርብ ወይም ድብልቅ ዓረፍተነገር በማለት መለየት
- ድርብ ዓረፍተነገሮችን መመስረት
- ድብልቅ ዓረፍተነገሮችን መመስረት

**3.የማስተማሪያ ዘዴ**

- ቅድመ ንባብ እውቀትን የሚቀሰቅሱ ተግባራትን ማሰራት
- እያዳመጡ ያሉትን ምንባብ ምንያህል እንደሚከታተሉ የንባብ ጊዜ ተግባራትን ማሰራት
- ያዳመጡትን ምንባብ ምንያህል እንደተረዱ ለመገምገም ድህረማዳመጥ ተግባርና መልመጃ ማሰራት
- ለቃላት ተቃራኒ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- ከተዘረዘሩት ርእሶች በአንዱ ላይ መረጃ በማሰባሰብ ንግግር እንዲያደርጉ ማበረታታት
- በተሰጠው ርእስ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ማበረታታት
- ቅድመንባብ ተግባራት እንዲሰሩ ማስተባበር
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ ማበረታታት
- ምስል በማየት የተገነዘቡትን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ማነሳሳት
- የተሰጣቸውን ምሳሌ በመመልከት ለቃላት አገባባዊ ትርጉም እንዲሰጡ ማገዝ
- ስለድብልቅ የቀረበውን ማስታወሻ በመገንዘብ ድብልቅ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ማበረታት
- ምሳሌዎችን መሰረት በማድረግ ድርብና ድብልቅ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማበረታታት

- እንደየ ትምህርት ይዘቶቹ ቻርቶችን፣ ስዕሎችን ወዘተ እንደመርጃ መሳሪያ መጠቀም

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-4 ለቀረቡት ተግባራት ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም ሀሳባቸውን እንዲያንጸባርቁ ያድርጉ፡፡ ለሚሰጡትም ሀሳብ ተገቢ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ

ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ በምዕራብ ወለጋ፣ በነጆ ወረዳ ኪዳነምህረት በተባለ አካባቢ በ1912 ዓ.ም ተወለዱ። ካደጉም በኋላ እድሜያቸው 14 ዓመት ሲሆን ገነት ጦር ትምህርት ቤት ገብተው በውትድርና ሙያ ሰለጠኑ። ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ በ1928 ዓ.ም አገራችን በፋሽስት ጣሊያን ስትወረር በወለጋ በኩል የመጣውን ጦር ለመመከት ከሌሎች አበርኞች ጋር በመሆን ዘመቱ። ከዚያም በየስፍራው በጀግንነት ሲዋጉ ቆስለው ተማረኩ። ፋሽስቶችም ብዙ ካጉሏኋቸው በኋላ በጣሊያን አገር ሲሲሊ ደሴት አሰሩአቸው።

ጣሊያን አገርም ሁለት ዓመት ተኩል ያህል እንደቆዩ አንዲት የእንግሊዝ አይሮፕላን እነ ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ በታሰሩበት ወህኒ ቤት ላይ ስታልፍ ወረቀት በተነች። ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳም አንድ ወረቀት አግኝተው አነሱና አጣጥፈው ኪሳቸው ውስጥ ከተቱት። ይህን ሲያደርጉ የተመለከተ እስረኛ ከሰሳቸውና ፖሊሱ መጥቶ እየደበደባቸው «ወረቀቱን አምጣ» አላቸው። ከዚያም ወደ ሌላ ወህኒ ቤት ወስደው አስሯቸው። ስቃዩንም አጠነከሩባቸው።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ከተራ ቁጥር 1-2 የቀረቡት የተግባር ጥያቄዎች ከላይ የቀረቡትን የምንባቡን አንቀጾች ተማሪዎች ምንያህል እየተገነዘቡት እንደሚያነቡ የሚፈትሹ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ጥያቄዎች በማቅረብ ተማሪዎች ምንያህል እየተገነዘቡ እንደሚያነቡ ይከታተሏቸው፡፡

1. ከምታዳምጡት ጽሁፍ አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. ቀጥሎ የሚመጣው ምንባብ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

ከዚያም አብረዋቸው ካሉት እስረኞች ጋር በመተዋወቅ ከአንድ የዮጐዝላቪያ እስረኛ፣ ጆሊዬ ከሚባል ጋር ተማክረው ለማምለጥ ቆረጡ። እንዳሰቡትም ምቹ ጊዜ ፈልገው ብርድ ልብስ ተልትለው እየቀጣጠሉ ቋጠሩ። የብርድ ልብሱን ትልታይ ከፎቅ መስኮት እንጨት ላይ አስረው ወደ መሬት ለቀቁት። የፖሊሶቹንም ሁኔታ በማጤን በብርድልብስ ተንጠልጥለው አመለጡ።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ አንድ**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-5 የቀረቡት ጥያቄዎች ለአዳምጦ መረዳት ከቀረበ ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ለመልሳቸውም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡ ሌ/ኮ አብዲሳ አጋ የተወለዱት የት ነው?

ሀ. ሀረር ሐ.ባሌ

ለ. አርሲ መ.ወለጋ

ከተማሪዎች የሚሰጠው መልስ **መ. ወለጋ** የሚል መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-10 ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ ለተማሪዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች ምሳሌ የሚሆን አንድ ጥያቄ አብረው ይስሩና ያሳዩዋቸው፡፡ በሚከተለው መልኩም መልስ ሊሰጡ ስለሚችሉ ተገቢውን ክትትል ያድርጉ፡፡ ተገቢውን ግብረመልስም ይስጧቸው፡፡ ምሳሌ፡ ቂም ቋጠሩ ተስማሙ

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተግባር አንድ**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-5 ከቀረቡት ርእሶች አንዱን መርጠው መረጃ በማሰባሰብ ይዘው ወደክፍል በመምጣት በንግግር እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ በንግግር ሲያቀርቡ ተገቢውን ክትትልና ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. ተማሪዎች ወደፊት ሲያድጉ በምን ሙያ ለአገራቸው አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚፈልጉ ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው ተራ በተራ በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

በሚከተለው መልኩ የተለያዩ የአርበኝነት መገለጫ ጽንሰሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ ጽንሰሀሳቦቹን በተመለከተ ሰዎችን በመጠየቅ ያገኙትን መረጃ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

1. የግብርና አርበኛ
2. የጦርሜዳ ውሎ አርበኛ
3. የስፖርት አርበኛ
4. የትምህርት አርበኛ
5. የጤና አርበኛ
6. የንግድ መስክ አርበኛ

**ክፍለጊዜ አምስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ሀ.ከተራ ቁጥር 1-2 ላሉት ጥያቄዎች ተማሪዎች የቀደመእውቀታቸውን በመጠቀም መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች ለራሳቸው ምንባቡን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

በተራ ቁጥር 1-2 የቀረበውን ተግባር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተግባራቱን በሚሰሩበት ጊዜ እያነበቡ ያለውን ምንባብ ምንያህል እየተረዱት እንደሆነ በመገምገም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

# የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**መልመጃ ሁለት**

ሀ.ከተራ ቁጥር 1-10 የቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ግን ሀሰት በማለት እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎቹ እውነት ወይም ሀሰት ያሉበትን ምክንያት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

ለምሳሌ፡1. አቡነ ጴጥሮስ ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስም መገርሳ በዳሳ ይባላል፡፡ ለሚለው መልሱ **እውነት** የሚል ነው፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

ለ. በሀ ስር ከተራ ቁጥር 1-10 ለተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት ከለ ስር ከተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍችያቸውን በመምረጥ እንዲያዛምዱ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትንም መልስ ይከታተሏቸው፡፡

ምሳሌ፡ ዛቻ ---- ማስፈራራት

ሐ. ከተራ ቁጥር 1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጡ ይዘዟቸው፡፡ ለተማሪዎችም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

# ተግባር አንድ

ሀ. የቀረበውን ምስል በመመልከት የተረዱትን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ከዚያም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ተግባር ሁለት**

ሀ. ከቀረቡት ርእሶች አንዱን በመምረጥ የአዘገጃጀት ሂደቱን በቅደም ተከተል በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች ሲያቀርቡ እርስ በርሳቸው እርማት እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ለ. መምህር፣ ተማሪዎች የተዘጋጁበትን ጽሁፍ በማቅረብ ከጓደኞቻቸው ጋር ተለዋውጠው እንዲተራረሙ ይዘዟቸው፡፡ በዚህን ጊዜ እየተዘዋወሩ የተማሪዎችን ስራ ይከታተሉ፡፡ ተማሪዎች ሲተራረሙ ስህተት ሆኖ ያገኙትን ስህተት ስለመሆኑ በምክንያት እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው፡፡ እርስዎም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት አምስት ፡ ቃላት

**መልመጃ ሶስት**

በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት በተገቢ ቦታቸው በማስገባት አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አስር**

**መልመጃ አራት**

ተማሪዎች በቀረቡት ሁለት አንቀጾች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ አገባባዊ ፍች በሚሰጡበት ወቅት በመከታተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡- አገሬ <u>ደጋ</u> ነው፡፡ ደጋ የሚለው ቃል ቆላ ያልሆነ የአየር ንብረቱ ቀዝቀዝ የሚል በማለት ከመለሱ መከታተልና ግብረመልስ መስጠት፡፡

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ስር ድብልቅ ዓረፍተነገር የሚል ይዘት አለ፡፡ ስለድብልቅ ዓረፍተነገር ከዚህ በፊት ያላቸውን ግንዛቤ በመጠየቅ ከተማሪዎች መልሳቸውን ይቀበሉ፡፡ በመቀጠል ድብልቅ

አረፍተነገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ካወያዩ በኋላ የሚከተለውን ማስታወሻ እንዲወስዱ ይዘዟቸው፡፡

**ድብልቅ ዓረፍተነገር**

**ድብልቅ ዓረፍተነገር፡** ድብልቅ ዓረፍተነገር ቢያንስ ከአንድ ጥገኛ ሐረግ (ዓረፍተነገር) እና መደበኛ ሐረግ (ነጠላ ዓረፍተነገር) ይመሰረታል። ድብልቅ ዓረፍተነገር ምን ጊዜም ቢሆን የሚኖረው አንድ ማሰሪያ አንቀጽ ወይም ግስ ብቻ ነው። ጥገኛ ሐረጋት ግን ከአንድ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ።

ምሳሌ፡ 1. ዛሬ በጣም ስለደከመኝ ወደ ቤት መሄድ አለብኝ።

… ስለደከመኝ = ጥገኛ ሐረግ (ዓረፍተነገር)

… አለብኝ = መደበኛ ሐረግ (ማሰሪያ አንቀፅ)

2. በጊዜ ምሳዬን በልቼ፣ ቡና ጠጥቼ፣ አልጋዬ ላይ ተጋድሜ ማንበብ አለብኝ።

… በልቼ … ጠጥቼ… እና ተጋድሜ - ጥገኛ ሐረጋት

አለብኝ = ማሰሪያ አንቀጽ /መደበኛ ሐረግ

**መልመጃ አምስት**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-8 የቀረቡትን ጥያቄዎች የሚሰጣቸውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ድርብ አረፍተነገር ወይም ድብልቅ አረፍተነገር በማለት እንዲመልሱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን መልስ በመከተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡ 1. ወንድሙ ስለመታኝ በጣም ተናድጃለው፡፡

2. ተስፋሁን ያለምግብ አንድ ቀን ሲውል ምንም አይመስለውም ነገርግን ውሃ ከጠማው ሰላሳ ደቂቃ መቆየት አይችልም፡፡

በተራ ቁጥር አንድ የቀረበው ምሳሌ ድብልቅ አረፍተነገር ሲሆን በተራ ቁጥር ሁለት የቀረበው ግን ድርብ አረፍተነገር ነው፡፡

ለ. ተማሪዎች ሶስት ድርብ አረፍተነገሮችና ሶስት ድብልቅ ዓረፍተነገሮች መስርተው እንዲያመለክቱ ይዘዟቸው፡፡ የተማሪዎችን መልስ ተከትሎ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## 4.ግምገማ

- የቀደመእውቀታቸውን የሚቀሰቅስ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- እያዳመጡ ያሉትን ምንባብ ምንያህል እንደሚከታተሉ የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ
- ያዳመጡትን ምንባብ ምንያህል እንደተረዱ ለመገምገም ድህረማዳመጥ ተግባርና መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ
- ለቃላት ተቃራኒ ፍች እንዲሰጡ መጠየቅ
- ከተዘረዘሩት ርእሶች በአንዱ ላይ መረጃ በማሰባሰብ ንግግር እንዲያደርጉ ማዘዝ
- በተሰጠው ርእስ ላይ በቡድን እንዲወያዩና ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- ቅድመንባብ ተግባራት እንዲሰሩ ማዘዝ
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ
- ምስል በማየት የተገነዘቡትን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- የተሰጣቸውን ምሳሌ በመመልከት ለቃላት አገባባዊ ትርጉም እንዲሰጡ ማዘዝ
- ስለድብልቅ አረፍተነገር የቀረበውን ማስታወሻ በመገንዘብ ድብልቅ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ማዘዝ
- ምሳሌዎችን መሰረት በማድረግ ድርብና ድብልቅ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ መጠየቅ

# የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

### መልመጃ አንድ

| ሀ.ምርጫ | | ለ. ተቃራኒ ፍች መልስ መስጠት | |
|---|---|---|---|
| 1. | መ | 1. | ተስማሙ |
| 2. | ለ | 2. | አሰሩ |
| 3. | መ | 3. | ፈቷቸው |
| 4. | ለ | 4. | ፈሪ |
| 5. | ሀ | 5. | ዳኑ |
| | | 6. | ሰበሰበች |

7. ከመሬት አንስተው
8. ወዳጅ
9. ማረኩ
10. ቀጨጨ

**መልመጃ ሁለት**

| ሀ. እውነት/ሀሰት | | ለ. ተመሳሳይ ፍች | | ሐ. ማዛመድ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | እውነት | 1. | ሠ | 1. | ሀ |
| 2. | ሀሰት | 2. | መ | 2. | ለ |
| 3. | ሀሰት | 3. | ለ | 3. | ሀ |
| 4. | እውነት | 4. | ረ | 4. | ሐ |
| 5. | ሀሰት | 5. | ሀ | 5 | መ |
| 3.1 | እውነት | 6. | ሸ | | |
| 3.2 | ሀሰት | 7. | ሐ | | |
| 3.3 | ሀሰት | 8. | በ | | |
| 3.4 | እውነት | 9. | ሰ | | |
| 3.5 | እውነት | 10. | ቀ | | |

**መልመጃ ሶስት**

**ሀ. ዓረፍተነገር አሟልቶ መጻፍ**

1. ማረሚያ ቤት
2. በማእረግ
3. ዛቻ
4. ህሊና
5. ባንዳ
6. አረፉ
7. መታሰቢያ
8. ጸኑ

**መልመጃ አራት**

**ሀ.ለቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍች መስጠት**

**መልመጃ አምስት**

| | ቃል | ትርጉም |
|---|---|---|
| 1. | ደጋ | ቀዝቃዛ |
| 2. | ውርጭ | ከባድ ቅዝቃዜ |
| 3. | ባለግርማ | ባለውበት |
| 4. | ለሰማይ ለምድር የከበደ | በጣም አምሮበት |
| 5. | ይልቅ | ይበልጥ |
| 6. | ግርጌ | ስር |
| 7. | ተሰማርተው | ስራቸው አድርገው |
| 8. | ከግዙፉ | ከትልቁ |
| 9. | ብጣቂ | ትንሽ |
| 10. | ድፍንፍን | ጭፍንፍን |
| 11. | ይገታል | ይቆማል |

**ሀ. ዓረፍተ ነገሮችን ድርብ/ድብልቅ በማለት መመለስ**

1. ድብልቅ ዓረፍተነገር
2. ድርብ ዓረፍተነገር
3. ድርብ ዓረፍተነገር
4. ድብልቅ ዓረፍተነገር
5. ድብልቅ ዓረፍተነገር
6. ድብልቅ ዓረፍተነገር
7. ድርብ ዓረፍተነገር

   ድብልቅ ዓረፍተነገር

# ምእራፍ አስር

## ቃላዊ ግጥም

(ክፍለጊዜ አስራ ሁለት)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ፡-**

- ያዳመጡትን ምንባብ መልእክት ይናገራሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ቃላዊ ግጥም የሚመስል ሌላ ቃላዊ ግጥም ያቀርባሉ፡፡
- ግጥምን በተገቢው የድምጽ ቅላጼ ያነባሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ቃላዊ ግጥም መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ግጥሞችን ይጽፋሉ፡፡
- በተለዋጭ ዘይቤ የቀረቡትን ቃላት ይገልጻሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ አያያዥ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- የቅድመ ንባብና የንባብ ጊዜ ተግባራት
- አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ መናገር
- ለቃላት ትክክለኛውን ፍቺ መምረጥ

### 2.2. መናገር

- በልጆች ጨዋታ ጊዜ የሚዜሙ ግጥሞች
- አጫጭር የልጆች ጨዋታ ግጥሞች

### 2.3. ምንባብ

- ቅድመንባብ የንባብ ጊዜ ተግባራት
- ምንባብ ማንበብ
- የምንባብ ፍሬ ሀሳብ መናገር
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

2.4. **መጻፍ**

- የስራ ቃል ግጥም መጻፍ
- የፍቅር ቃል ግጥም
- የክብረበአል ግጥም መጻፍ

2.5. **ቃላት**

- ዘይቤያዊ አነጋገር
- አረፍተነገሮችን በየትኛው የዘይቤ አይነት እንደተጻፉ መለየት

2.6. **ሰዋስው**

- ድርብ አረፍተነገር
- አያያዥ ቃላት
- አያያዥ ቃላትን በአረፍተነገር ውስጥ መጠቀም

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመእውቀታቸውን የተለያዩ ቅድመማዳመጥ ተግባራትን በማሰራት መቀስቀስ
- ምንባቡ በሚነበብላቸው ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙ መርዳት
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ በማድረግ ማጠናከሪያ መስጠት
- ለቀረቡት ጥያቄዎች ምሳሌዎችን በመስጠት እንዲሰሩ ማድረግ
- የልጆች ጨዋታ ማለት ምን እንደሆነ ማወያየት
- የልጆች ጨዋታ ግጥሞችን በማቅረብ በቀረበው ምሳሌ መሰረት እነሱም እንዲያቀርቡ ማበረታታት
- የተነበበላቸውን አጫጭር ግጥሞች መልሰው እንዲገልጹ ማድረግ
- የልጆች ጨዋታ ከነዜማቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ቅድመንባብ ተግባራትን በማቅረብ የቀደመእውቀታቸውን ማነሳሳት
- ምንባቡን እያነበቡ የንባብ ጊዜ ተግባራትን በማሰራት ምንባቡን እየተረዱ እንዲያነቡ ማድረግ
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲገልጹ ማድረግ
- በአከባቢያቸው የሚነገሩ ቃላዊ ግጥሞችን ይዘው በመምጣት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ

- የስራ ላይ ቃላዊ ግጥሞችን ጽፈው በመምጣት እንዲያቀርቡ ማድረግ
- የክብረበአልና የፍቅር ግጥሞችን በተመለከተ መረጃ በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ዘይቤያዊ አነጋገር ምንነት በማቅረብ ማወያየትና ማጠናከሪያ መስጠት
- የዘይቤ አይነቶችን በማቅረብ ማወያየት ለእያንዳንዱም ምሳሌ መስጠት ተማሪዎችም የተሠጠውን ምሳሌ በመከተል በራሳቸው ምሳሌዎችን እንዲሰጡ ማገዝ
- አረፍተነገሮችን በየትኛው የዘይቤ አይነት እንደተጻፉ እንዲለዩ ማድረግ፡፡ ተማሪዎችም አረፍተነገሮችን በየትኛው ዘይቤ እንደተጻፈ ማመልከት እንዲችሉ ማሰራት
- ድርብ አረፍተነገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወያየት
- ድርብ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማለማመድ
- አያያዥ ቃላትን በአረፍተነገር ውስጥ መጠቀም

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

*ሀ. ከተራ ቁጥር 1-2 ለቀረቡት ቅድመማዳመጥ ተግባራት የቀደመ ልምዳቸውን ተጠቅመው መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች በሚሰጡት መልስ ላይ ተገቢውን ግብረመልስ በመስጠት በዚህ መምሪያ ላይ ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡*

## የስራ ዘፈኖች

በአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በጋራም ሆነ በተናጠል አንድ ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራት እንዲያግዘው ግጥም እየደረደረ ያንጎራጉራል፤ ይጨፍራል፡፡ እንደደቦ በመሳሰሉት ቡድናዊ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ለምሳሌ ቤት ሲሰራ፣ አጥር ሲያጥር፣ ሳር ሲያጭድ ልዩ ልዩ የግብርና ስራዎች ሲያከናውን ያዜማል፡፡ በተናጠልም ቢሆን ማንጎራጎር የተለመደ ነው፡፡ ሴቷ ስትፈጭ፣ ስትፈትል፣ ልብስ ስታጥብ ሌላው ቀርቶ ልጅ አዝላ ስታባብል እንኳ እየዘፈነች ነው፡፡ ገበሬውም በሬዎቹን ጠምዶ በሚያርስበት ጊዜ እንደባህሉ ያንጎራጉራል፤ ይዘፍናል፤ ይገጥማል፡፡

የስራ ዘፈኖች ስራው አሰልቺ እንዳይሆንና ተሳታፊዎቹ ድካም እንዳይጫጫናቸው ያግዛሉ፡፡ ዜማውም ሆነ ግጥሙ ተሳታፊዎቹን ለስራው እንዲተጉና እንዲበረቱ ከመርዳቱም በላይ ለጊዜው ድካም እንዳይሰማቸው የማድረግ ሀይል አለው ተብሎ ይገመታል፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እዚህ ጋር ንባብዎን ቆም በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ጽሁፍ ምንያህል እየተከታተሉ እንደሆነ ይከታተሉ፡፡

1. የሚነበብላችሁን እያዳመጣችሁ የየአንቀጾቹን ፍሬ ሀሳብ መዝግቡ፡፡
2. የሚከተሉት አንቀጾች ስለምን የሚያወሱ ይመስላችኋል?

የስራ ዘፈኖችን በውል ለማወቅ በግብርና ላይ የሚሰሙ ግጥሞችን በምሳሌነት ወስደን እንመልከት፡፡ ገበሬዎች በአመቱ ወቅቶች ብዙ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ እንደየአከባቢያቸው የአየር ንብረት በጋ ከክረምት በማሳዎቻቸው ላይ የሚፈጽሟቸው የግብርና ስራዎች እንደየባህላቸው በዘፈኖችና በእንጉርጉሮዎች ይታጀባሉ፡፡ መሬቱን ለእርሻ ከማዘጋጀት ጀምሮ እስከ ምርት ማስገባት ድረስ በየወቅቱ በሚከናወኑ ስራዎች ላይ የተለያዩ ስነቃላዊ ግጥሞች ይሰማሉ፡፡ በእርሻ ጊዜ፣በጉልጓሎ፣ በዘር፣ በአረም፣ እንዲሁም ሰብል ከአራዊትና ከአእዋፍ በሚጠበቅበት ጊዜ፣ በአጨዳና በውቂያ ወቅት እንደየስራው ጠባይና እንደየአጋጣሚው ባህሪ ገበሬዎች አያሌ ግጥሞችን እየደረደሩ ያዜማሉ፡፡

በእያንዳንዱ የስራ አይነት ላይ የሚሰሙት ግጥሞች ከስራው እንቅስቃሴ ጋር የተጣጣሙ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን የዜማቸውን አወራረድና ክዋኔያቸውን እዚህ ለማሳየት ባይቻልም ከስራው እንቅስቃሴ በተገኘ እውቂያ ግምት በመውሰድ ጥቂት ምሳሌዎችን ማየት ይቻላል፡፡

በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጅ
እንዲያ ሰተት ብሎ ይጠመዳል እንጅ
እንረስ ሻሾ እንረስ መጋል
እንድንበላ ገብስ እንድንለሰልስ፡፡

*(ዘሪሁን አስፋው፡፡(1996፣46)፡፡የስነጽሁፍ መሰረታውያን፡፡አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡)*

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-10 ላሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ተገቢውን መልስ በመምረጥ እንዲመልሱ ይዘዟቸው፡፡ ለምሳሌ የሚሆን የመጀመሪያውን ጥያቄ አብረው በሚከተለው መልኩ በመስራት ያሳዩዋቸው፡፡

ምሳሌ፡ በአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በጋራም ሆነ በተናጠል አንድ ስራ **በሚያከናውንበት** ጊዜ ያንጎራጉራል፡፡

ሀ. በሚጨፍርበት ጊዜ ሐ. በሚተገብርበት ጊዜ

ለ. በሚያዳምጥበት ጊዜ መ. በሚያይበት ጊዜ

መልሱ ሐ. በሚተገብርበት ጊዜ የሚል መሆኑን ይንገሯቸው፡፡

ለ. ከተራ ቁጥር 1-3 የቀረቡት ድህረንባብ ጥያቄዎች ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት በማድረግ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡ ለምሳሌ የአንደኛውን ጥያቄ በዚህ መልኩ መስራታቸውን ይከታተሏቸው፡፡

የገጠሩ ማህበረሰብ ግጥም እየደረደረ በመጨፈርና በማንጎራጎር ከሚሰራቸው ስራዎች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ሶስቱን ጥቀሱ፡፡

ምሳሌ፡ 1. ቤት ሲሰራ

2. የእርከን ስራ ሲሰራ

3. አጨዳ ሲያጭድ

4. እህል በደቦ ሲወቃ

**ክፍለጊዜ ሶስት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

ሀ. በልጆች ጨዋታ ጊዜ ከሚዜሙት ግጥሞች መካከል አንዱን እቤታቸው አጥንተው በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

ለ. የሚከተለውን ግጥም ለተማሪዎች ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ደግመው ግጡሙን እንዲሉ ያድርጉ፡፡

ጉልበቴ በርታ በርታ

ጉልበቴ በርታ በርታ

አበላሃለሁ የሽንብራ ቂጣ

አሁንም አይደል ወደማታ

ወደማታ ወደማታ

ሐ. ሌሎች የልጆች ጨዋታ ግጥሞችን ከነዜማቸው ለጓደኞቻቸው በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

# ትምህርት ሶስት፡ ምንባብ

## የሰርግ ግጥም

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ሀ.ከተራ ቁጥር 1-3 ለቀረቡት ቅድመንባብ ተግባራት ተማሪዎች የቀደመ ልምዳቸውን በመጠቀም መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ከተራ ቁጥር 1-3 የቀረቡት የንባብ ጊዜ ተግባራት ተማሪዎች እያነበቡት ያለውን ምንባብ ምን ያህል እየተገነዘቡት እንደሚያነቡ ለማወቅ ይረዳሉ፡፡ እያነበቡት ያለውን ምንባብ ቆም እንዲሉ ካደረጉ በኋላ ተግባራቱን ያሰሩዋቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-8 የቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ አውዳዊ ፍቺ መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ለ. ግጥሙ ሲነበብ ዜማው ተሳክቶ የቀረበባቸው ስንኞች የትኞቹ እንደሆኑ በመለየት ደግመው ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያድርጉ፡፡

ሐ. ግጥሙ ሲነበብ ዜማው ተሳክቶ ያልቀረበባቸው ስንኞችን ከለዩ በኋላ እንዲሳካ አድርገው መልሰው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

### ተግባር አንድ

ከላይ የቀረበው የሰርግ ግጥም ሙሽራውን በተመለከተ የቀረበ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት የሚያውቁትን በሙሽሪት ዙሪያ የሚባሉ ግጥሞችን በማሰባሰብ ለምንና መቼ እንደሚባል ለክፍል ተማሪዎች ከነዜማው አቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ አምስት**

መ. ከተራ ቁጥር 1-4 የቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች ማህበረሰቡ ምን ለመግለጽ ወይም በምን ስነስርዓት ላይ እንደሚባሉ እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡ በበጋ እረስ ቢሉት ጸሀይን ፈራና

በሀምሌ እረስ ቢሉት ዝናቡን ፈራና

ልጁ እንጀራ ቢለው በጅቡ አስፈራራ

ከላይ በምሳሌነት የቀረበው ቃላዊ ግጥም ማህበረሱ ሰነፍ ገበሬ ስራውን በትኩረት የማይሰራውን ገበሬ ለመግለጽ እንደሚጠቀም መግለጻቸውን መከታተል፡፡

**ክፍለጊዜ ስድስት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### መልመጃ ሶስት

ሀ. የሚያውቋቸውን የልጆች ጨዋታ ግጥሞች ጽፈው ለክፍል ተማሪዎች ዜማውን ጠብቀው እንድያነቡ ያድርጉ፡፡

**ምሳሌ፡** መሀረቤን ያያችሁ እባካችሁ

አላየንም መሀረብ አላየንም

መሀረቤን ያያችሁ እባካችሁ

አላየንም መሀረብ አላየንም

ለ. የቀረበላቸውን የስራ ቃላዊ ግጥም ምሳሌ በማድረግ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ያገኙትን የስራ ቃላዊ ግጥም አሰባስበው በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ያቀረቧቸው ቃላዊ ግጥሞች መልእክት ምንእንደሆነ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

ምሳሌ 1፡- ዝሩ በየገደሉ ስር

በቅሎ ተገዛ አሉ በአንድ ቁና ምስር

ተላላው ገበሬ ይውላል ከጥላ

ውርጭ የመሰለ ብር ከመሬት ሲፈላ

አላየኸውም ወይ የምስሩን ተራ

እንደክረምት አግቢ ሽልንጉ ሲፈላ

ሐ. ከዚህ በታች የቀረበውን የፍቅር ቃላዊ ግጥም ምሳሌ በማድረግ በአከባቢያችው የሚነገሩ የፍቅር የቃል ግጥሞችን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡ አስራ ሁለት ሆነን እንድ ሰው ወደን

እሱ ይጫወታል እኛ ተጨንቀን

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**መልመጃ አራት**

ሀ. የቀረቡትን የቃል ግጥሞች ምሳሌውን መሰረት በማድረግ እንዲተረጉሙ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ በመከታተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡ 1. ረጅም መቀነት ሳይስቡት ይጠብቃል

የዘመኑ ፍቅር ሳይጀምሩት ያልቃል

የዚህ ግጥም አጠቃላይ መልእክት ሰዎች ከሚወዱት ሰው ጋር ጸንተው አይዘልቁም የሚል ነው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ተግባር ሁለት**

ከስራ፣ ከክብረበአል፣ ከፍቅር ቃል ግጥሞች ሶስት ሶስት በናሙናነት በመውሰድ የአከባቢያቸውን አዋቂ ሰዎች በመጠየቅ ለምን አላማ በቃል ግጥሞቹ እንደሚጠቀሙ እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ተማሪዎች ሲያቀርቡ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ዘይቤያዊ አነጋገር በሚል የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ላይ ከመውሰዳቸው በፊት የቀደመ እውቀታቸውን የሚቀሰቅሱ ዘይቤን በተመለከተ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ርእስ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ ተማሪዎች ሲወያዩ በመከታተል ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ማስተወሻውም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

# ዘይቤያዊ አነጋገር

ዘይቤ አንድን ሀሳብ፣ድርጊት ወይም ሁነት፤ የአንድን ነገር ቅርጽ ወይም ሁኔታ እንዲሁም የሰውን ባህሪ ስሜትና መልክ አጉልቶና አድምቆ ለተመልካቹም ሆነ ለሰሚው ምናባዊ ፍስህ በመስጠት የሚቀርብ የአነጋገር ስልት ነው፡፡ የዘይቤ አይነቶች ብዙ ቢሆኑም በስፋት አገልግሎት ላይ ውለው ከምናያቸው መካከል አነጻጻሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ ዘይቤዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

1. አነጻጻሪ ዘይቤ፡- ይህ ሁለት ነገሮችን፣ ባህሪዎችን፣ድርጊቶችን በመውሰድ በማነጻጸር ወይም በማወዳደር የሚፈጠር ዘይቤ ነው፡፡ ለማነጻጸርም እንደ፣ ይመስላል፣ ትመስላለች ወዘተ ቃላትን ይጠቀማል፡፡

   ምሳሌ፡ ኤልያስ እንደህጻን አለቀሰ፡፡

2. ተለዋጭ ዘይቤ፡- ተለዋጭ ዘይቤ የአንዱን ባህሪ ለሌላ በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   ምሳሌ፡ ረሂማ ጸሀይ ነች፡፡

3. ሰውኛ ዘይቤ፡- የሰውን ልዩ ልዩ ባህሪያት፣ድርጊትና ችሎታ ሰው ላልሆኑ ለእንስሳት፣ለተክሎችና ለግኡዛን በመስጠት የሚፈጠረው ዘይቤ ሰውኛ ዘይቤ ይባላል፡፡

   ምሳሌ፡ ዝናቡ ከኔ ቂም ያለው ይመስል አሯሩጦ ደበደበኝ፡፡

**ክፍለጊዜ አስር**

**መልመጃ አምስት**

ሀ. ከተራ ቁጥር 1-10 ላሉት ጥያቄዎች አረፍተነገሮቹን በትኩረት እንዲያነቡና ከዘይቤ አይነቶች በየትኛው የዘይቤ አይነት እንደቀረቡ እንዲናገሩ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡ 1. ቦና እንደነብር ይዘላል፡፡

ይህ አረፍተነገር የቀረበበት የዘይቤ አይነት አነጻጻሪ ዘይቤ ነው፡፡

ለ. ለአነጻጻሪ፣ ተለዋጭና ሰውኛ ዘይቤዎች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ሁለት አረፍተነገሮችን እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ድርብ አረፍተነገር በሚል የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ላይ ከመውሰዳቸው በፊት የቀደመ እውቀታቸውን የሚቀሰቅሱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም ድርብ አረፍተነገር የሚለውን ርእስ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ ተማሪዎች ሲወያዩ በመከታተል ተገቢውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ ማስተወሻውም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

# አያያዥ ቃላትን ተጠቅሞ ድርብ አረፍተነገር መመስረት

ድርብ ዓረፍተነገሮችን በመመስረት ሂደት አያያዦች ከፍተኛ ሚና አላቸው። የአያያዦች አገባብ በአረፍተነገሮቹ ሃሳብ የሚወሰን በመሆኑ ተገቢውን አያያዥ በማጣመር ለመጠቀም በነጠላ አረፍተነገሮቹ የተገለፀውን ሃሳብ መረዳት ያስፈልጋል።

ምሳሌ፡ የሂሳብ ትምህርት መማር እወዳለሁ።

ጥሩ ውጤት አላመጣሁም።

የሂሳብ ትምህርትን እወዳለሁ **ይሁን እንጂ** ጥሩ ውጤት አላመጣሁም።

በምሳሌው መሰረት “ይሁን እንጂ” የሚለው አያያዥ ሁለቱን ነጠላ ዓረፍተነገሮች በማያያዝ ድርብ ዓረፍተነገር ለመመስረት አስችሏል። የሃሳብ ዝምድናውን ለማመልከት “ነገር ግን”፣ ቢሆንም፣ ዳሩግን፣ ሊገቡ ይችላሉ። “ስለዚህ”፣ ስለሆነም፣ የመሳሰሉትን ግን አንጠቀምም።

**መልመጃ ስድስት**

ሀ. አያያዥ ቃላትን በተገቢው ቦታቸው በማስገባት ድርብ አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ይዘዟቸው፡፡ ምሳሌ በሚከተለው መልኩ በመስጠት ተማሪዎች ሰርተው የሚያቀርቡትን ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡ በዚህ ምክንያት

ሀ. አሸብር ልብሴ አልታጠበልኝም በሚል ከትምርት ቤት ቀረ

ለ. የአማርኛ ቋንቋ ፈተና አመለጠው፡፡

አሸብር ልብሴ አልታጠበልኝም በሚል ከትምህርት ቤት ቀረ <u>በዚህ ምክንያት</u> የአማርኛ ቋንቋ ፈተና አመለጠው፡፡

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**መልመጃ ሰባት**

ሀ. በሰንጠረዡ ግራና ቀኝ የቀረቡትን ነጠላ አረፍተነገሮች መሀል ላይ የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ድርብ አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች መስርተው ሲያቀርቡ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ቁርስ አልበላሁም ይሁን እንጂ የረሃብ ስሜት አልተሰማኝም፡፡

## 4.ግምገማ

- የቀደመእውቀታቸውን ለመቀስቀስ የተለያዩ ቅድመማዳመጥ ተግባራትን ማሰራት
- ምንባቡ በሚነበብላቸው ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግና የንባብ ጊዜ ተግባራትን ማሰራት

- ያዳመጡትን ምንባብ ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ መጠየቅ
- ለቀረቡት ጥያቄዎች ምሳሌዎችን በመስጠት እንዲሰሩ ማዘዝ
- የልጆች ጨዋታ ግጥሞችን በማቅረብ በቀረበው ምሳሌ መሰረት እነሱም እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- የተነበበላቸውን አጫጭር ግጥሞች መልሰው እንዲገልጹ መጠየቅ
- የልጆች ጨዋታ ከነዜማቸው እንዲያቀርቡ ማዘዝ
- ቅድመንባብ ተግባራትን በማቅረብ የቀደመእውቀታቸውን የሚያነሳሱ ተግባራትን ማሰራት
- ምንባቡን እያነበቡ የንባብ ጊዜ ተግባራትን በማሰራት ምንባቡን እየተረዱ እንዲያነቡ ማድረግ
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲገልጹ መጠየቅ
- በአከባቢያቸው የሚነገሩ ቃላዊ ግጥሞችን ይዘው በመምጣት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማዘዝ
- የስራ ቃላዊ ግጥሞችን ጽፈው በመምጣት እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- የክብረበአልና የፍቅር ግጥሞችን በተመለከተ መረጃ በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማዘዝ
- ዘይቤያዊ አነጋገር ምንነት እንዲናገሩ መጠየቅ
- የዘይቤ አይነቶችን በማቅረብ ማወያየት ለእያንዳንዱም ምሳሌ መስጠት ተማሪዎችም የተሠጠውን ምሳሌ በመከተል በራሳቸው ምሳሌዎችን እንዲሰጡ ማዘዝ
- አረፍተነገሮችን በየትኛው የዘይቤ አይነት እንደተጻፉ ለይተው እንዲያመለክቱ መጠየቅ፡፡
- ተማሪዎችም አረፍተነገሮችን በየትኛው ዘይቤ እንደተጻፈ ማመልከት እንዲችሉ ማዘዝ
- ድርብ አረፍተነገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልጹ መጠየቅ
- ድርብ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማዘዝ
- አያያዥ ቃላትን በአረፍተነገር ውስጥ ተጠቅመው ድርብ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ መጠየቅ

# የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

**ሀ.ተገቢውን መልስ መምረጥ**

1. ሐ
2. ለ
3. ሀ
4. መ
5. ሐ
6. ሐ
7. መ
8. ለ
9. ለ

**ለ. ተገቢ መልስ ስጡ**

1. ሀ. ቤት ሲሰራ
   ለ. የእርከን ስራ ሲሰራ
   ሐ .አጨዳ ሲያጭድ
   መ.እህል በደቦ ሲወቃ
2. ሀ. ስትፈጭ
   ለ. ስትፈትል
   ሐ. ልብስ ስታጥብ
   መ. ልጅ ስታባብል
3. ሀ. ድካም እንዳይሰማቸው
   ለ. እንዲዝናኑ
   ሐ. ብሶታቸውን እንዲተነፍሱ
   መ.ትውልድን ለማስተማር

## መልመጃ አምስት

**ሀ. በየትኛው የዘይቤ አይነት እንደተጻፈ ግለጹ**

1. አነጻጻሪ ዘይቤ
2. ተለዋጭ ዘይቤ
3. አነጻጻሪ ዘይቤ
4. ሰውኛ ዘይቤ
5. አነጻጻሪ ዘይቤ
6. ሰውኛ ዘይቤ
7. ተለዋጭ ዘይቤ
8. አነጻጻሪ ዘይቤ
9. ተለዋጭ ዘይቤ
10. ሰውኛዘይቤ

ሀ. አያያዥ ቃላትን በተገቢ ቦታቸው በማስገባት ድርብ ዓረፍተነገር መመስረት

በርትቶ ያጠናል **ለዚህም** አንደኛ ይወጣል፡፡
ጨለማን ትፈራለች **ምክንያቱም** አውሬ አስደንግጧት ያውቃል፡፡
ነፍሰጡሮች ይመጣሉ **ስለዚህ** ማዋለጃ ክፍሉን እናዘጋጅላቸው፡፡

# ሙዳየ ቃላትና ሀረጋት

| | |
|---|---|
| የሚጠበቅ ውጤት | ተማሪዎች የቀረበውን የትምህርት ይዘት ከተማሩ በኋላ የሚያገኙት እውቀት |
| አዳምጦ መረዳት | የሚነበበውን ወይም የሚነገረውን አዳምጦ መረዳት |
| ምንባብ ተኮር ጥያቄዎች | መልሳቸው ከተነበበው/ከተደመጠው ምንባብ ውስጥ የሚገኝ ጥያቄዎች |
| መረዳት/መተርጎም | በጽሁፍ ወይም በንግግር የቀረበን መልዕክት በትክክል መረዳት/መተርጎም |
| ምሥርት ቃል | በቋንቋዉ ሥርዓት መሠረት ከአንድ ቃል የተፈጠረ ሌላ አዲስ ቃል |
| ገላጭ ጽሁፍ | መረጃ ሰጪ የሆነ የጽሑፍ ዓይነት |
| ትምህርት | በእለቱ የሚቀርብ የትምህርት ይዘት |
| አንብቦ መረዳት | የጽሑፍን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት |
| ማስታወሻ | የቀረበውን የትምህርት ይዘት የሚያዳብር ማብራሪያ |
| ማጣመር | ፊደላትን፣ ቃላትንና/ወይም ቅጥያዎችን ማቀናጀት/ማዋቀር |
| ምሥርት ቃል | በቋንቋዉ ሥርዓት መሠረት ከአንድ ቃል የተፈጠረ ሌላ አዲስ ቃል |
| የሂደት ጥያቄ | በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት በመካከል ንባብን/ማዳመጥን ተገ አድርጎ የሚመለስ ጥያቄ |
| አመራማሪ ጥያቄ | መልሱ ሙሉበሙሉ በቀጥታ ከጽሁፉ ውስጥ የማይገኝ፣ ምንባቡንና የቀደመ ዕውቀትን መሠረት አድርጎ የሚመለስ ጥያቄ |
| ቅጥያ | በዚህ መርሃ-ትምህርት መሠረት ላይ አዳዲስ ቃላትንም ሆነ የቃላት ቅርጾችን ለማግኘት በቃላት ላይ የሚገባ ቅንጣት ወይም ፍቺ አዘል አሃድ |
| የአጻጻፍ ሥርዓት | በቃላት ውስጥ የፊደላትን አጠቃቀምን (ፍደላን)፣ ሥርዓተነጥብንና የመሣሰሉትን የሚመለከት ሥርዓት |
| ማዘዝ/መምራት | እንዴት ማድረግና መሥራት እንደሚቻል ማሳያና ተማሪዎችን መፈተሽና መገምገም የሚቻልበት መስፈርት |
| ማገዝ/መርዳት | ለተማሪው ተገቢ ድጋፍ ማድረግ (ቀስ በቀስ ግን ድጋፉን መቀነስ) |
| ተተኳሪ ቃላት | በምዕራፍ ትምህርት ትኩረት የሚሰጣቸው ቃላት |

| | |
|---|---|
| የቃላት ዕውቀት | የተማሪዎችን የቃላት ሀብትና የቃላቱን ፍቺ ዕውቀት |
| ምንባብ ተኮር ጥያቄዎች | መልሳቸው ከተነበበው/ከተደመጠው ምንባብ ውስጥ የሚገኝ ጥያቄዎች |
| ቆም ብሎ ማሰብ | በማንበብ ሂደት ተማሪዎች ማንበባቸውን ቆም አድርገው ምን ያህል እንደተረዱና ወደፊት ምን ሊመጣ እንደሚችል ለመገመት የሚደረግ |
| የቃላት አገባብ | በቋንቋ ሥርዓት መሠረት በመዋቅር ውስጥ ቃላትን በዓረፍተነገር ውስጥ ማቀናበር |
| የንባብ ሂደት | በማንበብ ሂደት ምን ያህል እንደተረዳን የምንከታተልባቸው ብልሃቶች |
| ተዘውታሪ ቃላት | በእለት ተእለት ህይወታችን የምንጠቀምባቸው ቃላት |
| ቃላዊ ግጥም | ሰዎች በቃል እየገጠሙ የተሰማቸውን ስሜት የሚያስተላልፉበት |

# ዋቢዎች

ሽለማ ካቤ፡፡2009፡፡**የኦሮሞ ጀግኖች ታሪክና ሌሎች**፡፡ግራፊክ ማተሚያ ቤት፤አዲስ አበባ፡፡

ቤተልሂም ታፈሰ፡፡2013፡፡ **እኔና የኤልተቪ ምስጥሮቼ** ፡፡ፋርኢስት ትሬዲንግ ሓላ.የተ.የግ ማኅበር፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ባየ ይማም፡፡2004፡፡ **አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡** አልፋ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፡፡

ብርሃኑ ገ/ጻዲቅ፡፡1994፡፡**አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መመሪያ**፡፡ ሜጋ ማተሚያ ድርጅት፤አዲስ አበባ፡፡

አዲሱ ገረመው፡፡ 2012፡፡ **አዲስ ዘመን**፤ አዲስአበባ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡1996፡፡ **የስነጽሁፍ መሰረታውያን**፡፡ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤አዲስ አበባ፡፡

ዜና ልሳን Zena-Lissan Volume XXVI Number 2 December 2017 (http://ejol.ethernet.et)

የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡2010፡፡ወንጪ ሀይቅና አካባቢው፡፡ አዲስ አበባ፡፡

የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴርና የኦሮሚያ ትምርት ቢሮ፡፡2007፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ የተዘጋጀ መጽሀፍ፤አዲስ አበባ፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡1989 ፡፡ **የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ**፡፡ንግድ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፡፡

ጌታቸው ምትኩ “በሰዎች መነገድ/ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ምንድነው?”. አብሲኒያለው ድህረ ገጽ. (https://elearn.moe.gov.et)

ጻሀይ ተፈረደኝ፡፡2011፡፡አዲስ አድማስ ጋዜጣ፤ አዲስ አበባ፡፡ ድህረ ገጽ (http://www.addisadmassnews.com)

## የ7ኛ ክፍል የአፍመፍቻ ቋንቋ መርሃ ትምህርት

### የአንደኛ መንፈቀ አመት

ምእራፍ አንድ ፡ **ተፈጥሮን ማድነቅ** (9 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የሌሎችን ሀሳብ ያዳምጣሉ
- በተፈጥሮ ምንነት ላይ መወያየት
- ለክፍል ደረጃው የሚመጥን ሪዘም ያለ ጽሁፍ ማንበብ
- የተፈጥሮን የተለያዩ ገጽታዎች ማድነቅ
- አንቀጽ መጻፍ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከዚህ ትምህርት በኋላ፡ የሌሎችን ሀሳብ በትኩረት ያዳምጣሉ | ማዳመጥ | **ቅድመ ማዳመጥ:-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ **ምሳሌ:-** ስለወንዝ ምን ታውቃላችሁ? **በማዳመጥ ጊዜ:-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ **ምሳሌ:-** አዋሽ ወንዝ **ድህረ ማዳመጥ:-** ያዳመጡትን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎችን መስራት | ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ ምሳሌ:- አዋሽ ወንዝ በኦሮሚያ ክልል በየትኛው ዞን ይገኛል |
| ቋንቋን በተለመዱ ሁኔታዎች ውስጥ በተገቢ መንገድ መጠቀም | ንግግር | ተፈጥሮን ወይም ወንዝን ለማድነቅ በተገቢው ቋንቋ መጠቀም በተሰጠው ርእስ ወይም ስለወነወዝ ከጓደኞቻቸው ጋር መወያየት በርእሱ ዙሪያ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ | ተማሪዎች ስለተፈጥሮ የሚያውቀትን እንዲናገሩ ማድረግ ምሳሌ:- የአዋሽ ወንዝ ለምን ይጠቅማል? |
| ለክፍል ደረጃው የሚመጥንና ተዘውታሪና ተዘውታሪ ባልሆኑ ቃላት የተዋቀረ ፅሁፍን ትክክለኛነትን በሚያጎለብት ሁኔታ ቀስ በቀስ ማንበብ | ንባብ | **ቅድመ-ንባብ:-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ **ምሳሌ:-** ስለተፈጥሮ ምን ታውቃላችሁ? **በንባብ ጊዜ:-** ተማሮዎች ምንባቡን በዝምታና በትክክለኝነት ማንበብ መምህሩ/ቷ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ **ድህረ ንባብ:-** ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ መልመጃዎችን መስራት (ስእል ያስፈልጋል) | ተማሪዎች የተለመዱና እንግዳ ቃላትን ከምንባቡ በማውጣት ስለቃላቱ የተሰማቸውን ለሌሎች መግለጽ |
| የተለመደ ሀሳብ መሰረት በማድረግ አንቀፅ መፃፍ | ጽኅፈት | ተፈጥሮን የተመለከተ ስእል በመጠቀም አጭር አንቀጽ በመጻፍ ጓደኞቻቸው እንዲያርሙላቸው ማድረግ | ተማሪዎች አንቀጽ ለመጻፍ የሚሆን ሀይለቃል እንዲጽፉ መጠየቅ |
| ለተዘውታሪ ቃላት ትርጉም መስጠት | ቃላት | ለተዘውታሪ ቃላት ፍቺ መስጠት | ተማሪዎች ለተወሰኑ ተዘውታሪ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ መጠየቅ |
| የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰረታዊ መዋቅሮችን መለየት | ሰዋስው | ተማሪዎች ስለአፍ መፍቻ ቋንቋው መሰረታዊ መዋቅሮች ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ ማድረግ | ተማሪዎች ስለአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መሰረታዊ መዋቅሮች አስመልክቶ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ መጠየቅ |

ምዕራፍ 2፡- **የቤተሰብ ምጣኔ** *(9 ክፍለ ጊዜ)*

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በጥሞና ማዳመጥ
- ስለቤተሰብ ምጣኔ ምንነት መወያየት
- ስለቀላል ገጠመኞቻቸው መተረክ
- ስለቤተሰብ ምጣኔ መከራከር
- ስእሎችን ማንበብ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከዚህ ትምህርት በኋላ፡<br>• የሚነበብለቸውን ጽሁፍ በጥሞና ያዳምጣሉ | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-**ስለቤተሰብ ምጣኔ ፣ምን ታውቃላችሁ?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ **ምሳሌ፡-** ቤተሰብ<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎችን መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ ምሳሌ፡- የቤተሰብ ምጣኔ ምንድነው ? |
| • ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል መተረክ | ንግግር | • ቀላል ሁነቶችን በቅደም ተከተል መተረክ<br>• የቤተሰብ ምጣኔ ስለሚለው ርእስ ከጓደኞቻቸው ጋር መወያየት<br>• ስለርእሱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማቅረብ | • ስለቤተሰብ ምጣኔ ጥቅም ተማሪዎችን መጠየቅ |
| • አንብብና ስለቀረበው ስእል ግለጽ/ጪ | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ **ምሳሌ፡-** ስለቤተሰብ ምጣኔ ምን ታውቃላችሁ?<br>• **በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮቹ በምንባቡ ውስጥ የቀረበውን ስእል አንብበው ስለስእሉ ይገልጻሉ፡፡ መምህሩ/ቷ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ ከምንባቡ የወጡ የመረዳት መልመጃዎችን መስራት<br>• (ስእል ያስፈልጋል) | • ተማሪዎች የምንባቡን ዋና ዋና መልእክቶችን ጨምቀው እንዲያቀርቡ መጠየቅ |
| • ሶስት አንቀጽ ያሉት አስረጅ ድርሰት መጻፍ | ጽኀፈት | • አስረጅ ድርሰት ለመጻፍ መረጃዎችን መሰብሰብ<br>• በተሰጠው ርእስ በመመርኮዝ ሶስት አንቀጽ ያለው አስረጅ ድርሰት መጻፍ<br>• ድርሰቱን ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ማረም | • ለያንዳንዱ አንቀጽ ሀይለቃል እንዲጽፉ መጠየቅ |
| • አዳዲስ ቃላትን መለየትና ፍች መስጠት | ቃላት | • አዳዲስ ቃላትን መለየትና በምንባቡ መሰረት ፍች መስጠት | • ተማሪዎች ለተወሰኑ አዳዲስ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ መጠየቅ |
| • የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅሮችን ጠብቆ ትክክለኛ አረፍተነገር መጻፍ | ሰዋስው | • የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅሮችን ጠብቆ ትክክለኛ አረፍተነገር መጻፍ | • የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅሮች እንዲያብራሩ መጠየቅ |

ምዕራፍ 3፡- **በጎ ፈቃደኝነት** *(9 ክፍለ ጊዜ)*

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ማዳመጥና የተረዱትን መናገር
- የበጎ ፈቃደኝነትን ጽንሰሀሳብ መግለጽ
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ ማስታወስ
- የመልካም ፈቃደኝነት መተግበሪያ አካባቢዎችን መለየት
- ከምንባቡ ውስጥ ቃላትን ማውጣት

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • አዳምጦ ስሜታቸውን መግለጽ | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-**በጎ ፈቃደኝነት ምንድነው?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ **ምሳሌ፡-** መረዳዳት<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎችን መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ ምሳሌ፡- የመረዳዳት ጠቀሜታ ምንድነው? |
| • ከክፍል ጓደኞች ጋር በሚደረግ ጭውውት ውስጥ መሳተፍ | ንግግር | • መረዳዳትን መግለጽ<br>• የክፍል ተማሪዎች ስለመረዳዳት እርስበርስ መዋያየት | • እርስመርስ መራዳዳት ያለውን ጠቀሜታ እንዲያስረዱ ተማሪዎችን መጠየቅ |
| • ማንበብና የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ ማስታወስ<br>• ማንበብና የተለመዱ ቃላትን ለይቶ ማውጣት | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** የተማሪዎቹ ዋና ዋና ቃላትን እንዲያወጡ መጠየቅ **ምሳሌ፡-** በጎ ፈቃደኝነት<br>• **በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮቹ የምንባቡ ዋና ሃሳብ ለማስታወስ ያነባሉ፡፡ መምህሩ/ሯ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ ምንባን የሚመለከቱ የመረዳት መልመጃዎችን ይሰራሉ (የቃላት ሰንጠረዥ ያስፈልጋል) | • ተማሪዎች የምንባቡን (በጎፈቃደኝነት) ዋና ዋና መልእክቶችን ጨምቀው እንዲያቀርቡ መጠየቅ<br>• ከምንባቡ የወጡ ቁልፍ ቃላት ፍቺ መጠየቅ |
| አራት አንቀጾች ያሉት የማግባቢያ ድርሰት መጻፍ | ጽኅፈት | • አራት አንቀጾች ያሉት የማግባቢያ ድርሰት መጻፍ (በጎፈቃደኝነት)<br>• ድርሰቱን ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ማረም | • ተማሪዎቹ ለያንዳንዱ አንቀጽ ሀይለቃል እንዲጽፉ መጠየቅ |
| ጥምር ቃላትን መለየትና ፍቻቸውን መስጠት | ቃላት | • አዳዲስ ቃላትን መለየትና በምንባቡ መሰረት ፍች መስጠት | • ጥምር ቃላትን መተርጎም |
| የቃላትን የነጠላና የብዙ ቁጥር ቅርጽ መለየት | ሰዋስው | • የቃላትን የነጠላና የብዙ ቁጥር ቅርጽ መለየት | • ተማሪዎቹ ስለተወሰኑ ቃላት የነጠላና ብዙ ቁጥር ቅርጽ መጠየቅ |

ምዕራፍ 4፡- **የታዋቂ ግለሰብ ህይወት ታሪክ** *(12 ክፍለ ጊዜ)*

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የሚሰጣቸውን ማብራሪያ ማዳመጥ
- የህይወት ታሪክ ምንነትን መግለጽ
- ከምንባቡ የምክንያትና ውጤትን ትስስር ይለያሉ
- የታዋቂ ሰዎችን የህይወት ታሪክ ይጽፋሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • አዳምጦ የቀረበውን ሀሳብ ማድነቅ | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-**ስለህይወት ታሪክ ምን ታወቃላችሁ?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ **ምሳሌ፡-** ዝነኛ ሰው<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎችን መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ ምሳሌ፡- የህይወት ታሪክ ለመጻፍ ሲታለፍባቸው የሚገቡ ደረጃዎች ምንድናቸው? |
| • በቡድን በመሆን በቀረበ መመሪያ ላይ መወያየት | ንግግር | • የህይወት ታሪክ በመጻፍ መሳተፍ<br>• በቡድን በመሆን በቀረበ መመሪያ ላይ መወያየት<br>• በህይወት ታሪክ ላይ መወያየት | • ተማሪዎችን ስለ አንድ ዝነኛ ሰው እንዲናገሩ መጠየቅ |
| • ማንበብና የተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለይቶ ማውጣት | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** ተማሪዎች ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ **ምሳሌ፡-** የእግር እሳት<br>• **በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮቹ የምንባቡን ዋና ሃሳብ ለማስታወስ ያነባሉ። መምህሩ/ቷ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ ምንባቡን የሚመለከቱ የመረዳት መልመጃዎችን ይሰራሉ<br>• ለተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቺ ይሰጣሉ | • ስለህይወት ታሪክ አጻጻፍ ደረጃዎች ተማሪዎችን መጠየቅ |
| የመሸጋገሪያ ቃላትን መለየት | ጽኅፈት | • የመሸጋገሪያ ቃላትን መጻፍ | • ተማሪዎች ስማዊ ሀረግ እንዲጽፉ መጠየቅ |
| ተዘውታሪ ቃላትን ለተለያዩ አገልግሎቶች መጠቀም | ቃላት | (የህይወት ታሪክ እንዴት እንደሚጻፍ የሚያስረዳ መግቢያ)<br>• በመሸጋገሪያ ቃላት ላይ መወያየት<br>• ሀሳብን ለመግለጽ ተዘውታሪ ቃላትን መጠቀም | • ተማሪዎች ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን እንዲገልጹ መጠየቅ |
| ሀረግን መለየት | ሰዋስው | • ሀረግን ከአረፍተነገር መለየት | • ተማሪዎችን ስለስማዊ ሀረግ መጠየቅ |

ምዕራፍ 5፡- **ውሃና ጠቀሜታው** *(9 ክፍለ ጊዜ)*

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ከሚያዳምጡት ማበራሪያ ማስታወሻ መውሰድ
- ስለውሃ ጥቅም መግለጽ
- ስለፍላጎታቸውና ስለሚመለከታቸው ጉዳይ በግልጽ መናገር
- የቃላት እውቀታቸውን መስፋት
- የውሃ አይነቶችን መዘርዘር

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • በንቃት አዳምጦ መልእክቱን መረዳት | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-**የውሃ ጥቅም ምንድነው?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ<br>**ምሳሌ፡-** የውሃ አስተዳደር<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎችን መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>ምሳሌ፡- የውሃ አይነቶች የትኞቹ ናቸው? |
| • ቀላል መረጃዎችን መጠየቅ | ንግግር | • ስለውሃ አይነቶች (ለመጠጥ የሚውልና የማይውል) እንዲሁም ስለውሃ አስተዳደር ጥቅም ለማወቅና ቀላል መረጃ ለማገኘት በመጠየቅና በመወያየት አጭር መረጃዎችን መውሰድ | • ተማሪዎችን ስለውሃ አስተዳደር ቃላል መረጃ ለማግኘት ጥያቄ እንዲያቀርቡ ማድረግ |
| • ስለምክንያትና ውጤት ግንኙነት ምንባቡን በማንበብ ይለያሉ | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** ተማሪዎችን በቀረበው ርእስ ውስጥ ምክንያትና ውጤት ያላቸውን ግንኙነት አስመልክቶ መጠየቅ<br>• **በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮች ምክንያትና ውጤት ያላቸውን ግንኙነት ለመለየት ያነባሉ<br>መምህሩ/ሯ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ የምንባቡን ሀሳብ በመረዳት ምንክንያትና ውጤት ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከቱ መልመጃዎችን ይሰራሉ | • ተማሪዎችን ስለውሃ አስተዳደር ብልሃት ከምንባቡ መጠየቅ |
| ተራኪ ድርሰት መጻፍ | ጽኀፈት | • በሚሰጥ ርእስ ተራኪ ድርሰት መጻፍ<br>• ድርሰቱን ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ማረም | • ተማሪዎች ተራኪ ድርሰት እንዲጽፉ መጠየቅ |
| የቃላት እማሬያዊ ፍች መለየትና ፍቺያቸውን መበየን | ቃላት | • ስለቃላት እማሬያዊ ፍቺ ማብራራት | • ተማሪዎች ለተወሰኑ ቃላት እማረያዊ ፍቺ እንዲሰጡ መጠየቅ |
| ገቢርና ተገብሮ አረፍተ ነገሮችን መለየት | ሰዋስው | • ገቢርና ተገብሮ አረፍተ ነገሮችን መለየት | • ተማሪዎችን በገቢርና በተገብሮ አረፍተ ነገሮችን መካከል ያለውን ልዩነት መጠየቅ |

# የ7ኛ ክፍል የአፍመፍቻ ቋንቋ መርሃ ትምህርት

## የሁለተኛ መንፈቀ አመት

ምእራፍ ስድስት ፡ **የሰዎች ዝውውር** (9 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ከሚያዳምጡት ዋና ዋና ነጥቦችን መለየት
- ስለሰዎች ዝውውር ጽንሰሀሳብ መግለጽ
- በራስ በመተማመን ከጓደኞቻቸው ጋር ይነጋገራሉ
- አቀላጥፈው ያነባሉ
- ስለሰዎች ዝውውር ተጽእኖ ይመረምራሉ

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ብልሃቶች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| • በትኩረት በማዳመጥ የምንባቡን ይዘት ይመረምራሉ | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-**የሰዎች ዝውውር ምንድነው?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ<br>**ምሳሌ፡-** የሰዎች ዝውውር የሚያስከትለው ጉዳት<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** በትኩረት ያዳመጡትንና የመረመሩትን መሰረት በማድረግ መልመጃዎችን መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ምሳሌ፡- የሰዎች ዝውውር የሚያስከትላቸው ችግሮች ምንድናቸው? |
| • በሚሰጥ ርዕስ ላይ በራስ በመተማመን ከጓደኞቻቸው ጋር | ንግግር | • ስለሰዎች ዝውውር ጥቅምና ጉዳት በራስ በመተማመን ከጓደኞቻቸው ጋር መነጋገር | • ተማሪዎች የሰዎች ዝውውር ስለሚያስከትለው ጉዳት [illegible] |
| • የቀረበን ጽሁፍ አቀላጥፎ ማንበብ | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** ተማሪዎችን ስለርእሱ መጠየቅ **ምሳሌ፡-** ስለሰዎች ዝውውር ምን ታውቃላችሁ?<br>• **በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮች ምንባቡን አቀላጥፈው ያነባሉ መምህሩ/ሯ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ | • ተማሪዎቹ ከምንባቡ የተወሰነውን ክፍል አቀላጥፈው እንዲያነቡ መጠየቅ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | • **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ ምንባቡን አቀላጥፈው በማንበብ የምንባቡን መልእክት ይረዳሉ (ስእል ያስፈልጋል) | |
| የገላጭ ድርሰትን መዋቅር መመርመር | ጽኁፈት | • የገላጭ ድርሰት መዋቅርን ከመረመራችሁና ከጻፋችሁ በኋላ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት | • ተማሪዎች ስለሰዎች ዝውውር አስረጅ ድረሰት እንዲጽፉ መጠየቅ |
| የቃላትን ፍካሬያዊ ፍች መለየትና ፍቺያቸውን መበየን | ቃላት | • ስለቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ማብራራት | • ተማሪዎች ለተወሰኑ ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ መጠየቅ |
| አረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎት አንጻር መለየት | ሰዋስው | • አረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎት አንጻር መለየት | • ተማሪዎችን አረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎት አንጻር እንዲጽፉ መጠየቅ |

ምእራፍ ሰባት ፡ **ማህበራዊ ግንኙነት** (12 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በጥልቀት ያዳምጣሉ
- ስለማህበራዊ ግንኙነት ጠቀምታ ይገልጻሉ
- በተለያዩ ርእሶች ጽሁፍ ማዘጋጀት
- ውስብስብ አረፍተነገሮችን መመስረት

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • መረጃ ሰጪ ጽሁፍን በትኩረት ያዳምጣሉ | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-**ማህበራዊ ግንኙነት ምንድነው?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ<br>**ምሳሌ፡-** ማህበራዊነት<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መሰረት በማድረግ መልመጃዎችን በትኩረት መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ምሳሌ፡- የማህበራዊነት ጠቀሜታ ምንድነው? |
| • በተወሰነ ጉዳይ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር መደራደር | ንግግር | • በተወሰነ ጉዳይ ላይ ለምሳሌ በማህበራዊ ግንኙነት ጠቀሜታ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር መደራደር | • ተማሪዎች ስለማህበራዊ ግንኙነት ጠቀሜታ እንዲደራደሩ መጠየቅ |
| • ተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን አንብቦ መጠቀም | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** ተማሪዎችን ስለተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ጠቀሜታ መጠየቅ<br>• **በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮቹ ለተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ትኩረት በመስጠት ያነባሉ<br>መምህሩ/ሯ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ ከምንባቡ የወጡ የመረዳትና ተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገር መልመጃዎች ይሰራሉ (ስእል ያስፈልጋል) | • ተማሪዎቹ ስለማህበራዊ ግንኙነት ጠቀምታ በተዘውታሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በመጠቀም አሳጥረው እንዲያቀርቡ መጠየቅ |
| በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ ፅሑፍ መፃፍ | ጽኀፈት | • በተለያዩ ርዕሶች ስለማህበራዊ ግንኙነት ጠቀሜታ መፃፍ | • ተማሪዎች ስለማህበራዊ ግንኙነት ጠቀሜታ ድረሰት እንዲጽፉ መጠየቅ |
| ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት መዘመድ | ቃላት | • ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት መዘመድ | • ተማሪዎች የተወሰኑ ቃላን በተመሳሳይ ፍቺ እንዲያዛምዱ መጠየቅ |
| አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ሰዋስው | • አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | • ተማሪዎችን አገልግሎታዊ አረፍተነገር ክፍሎች መጠየቅ |

ምእራፍ ስምንት ፡ **ሱሰኝነት** (9 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ሱሰኝነት ያለውን ተጽእኖ መግለጽ
- ስለምንባቡ ዋና ሀሳብ መዘገብ
- አድማጮችን ለመርዳት የምንባቡን ሀሳብ እንደገና ማቀናጀት

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ብልሃቶች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| • ማዳመጥና ተመሳሳይ ጽሁፍ መጠር | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-** ሱሰኝነት ምንድነው?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ **ምሳሌ፡-** ሲጋራ ማጤስ<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን የሚስል ጽሁፍ የማዘጋጀት መልመጃ መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ምሳሌ፡- የሱሰኝነት ተጽእኖ ምንድነው? |
| • አድማጭን ለመርዳት ሀሳቦችን መልሶ ማዋቀር | ንግግር | • አድማጮችን ለመርዳት የምንባቡን ሀሳብ እንደገና በማቀናጀት በተሰጠ ጉዳይ ላይ (ሲጋራ ማጤስ ያለውን ተጽእኖ) መናገር | • ተማሪዎች ንግግራቸውን እንደገና አቀናጅተው |
| • ማንበብና ዋናውን ሀሳብ በቃል ማቅረብ | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** ተማሪዎችን ስለርእሱ መጠየቅ **ምሳሌ፡-** ስለሱሰኝነት ምንታውቃላችሁ?<br>• **በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮቹ የበምንባቡን ዋና ሀሳብ በቃል ለመዘገብ እንዲያስችላቸው በማትኩረት ያነባሉ መምህሩ/ሯ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ ከምንባቡ የወጡ የመረዳት መልመጃዎችን ይሰራሉ (ስእል ያስፈልጋል) | • ተማሪዎቹ ስለሱሰኝነት ተጽእኖ በቃላቸው ዘገባ እንዲያቀርቡ መጠየቅ |
| በጽሁፍ ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም | ጽኀፈት | • ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ይጽፋሉ | • ተማሪዎችን ስርዓተ ነጥቦችን እንዴት እንደሚጠቀሙ መጠየቅ |
| የተዘውታሪ ቃላት አገባባዊ ፍቺን መግለጽ | ቃላት | • የተዘውታሪ ቃላት አገባባዊ ፍቺን መግለጽ | • ተማሪዎች የተዘውታሪ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ እንዲገልጹ መጠየቅ |
| ድርብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ሰዋስው | • የቋንቋውን ስርአት ጠብቆ ድርብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | • ተማሪዎች ድርብ አረፍተ ነገሮችን እንዲያስተካክሉ መጠየቅ |

ምእራፍ ዘጠኝ ፡ **አርበኝነት** (12 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ያዳመጡትን መልእክት ከነባራዊ ህይወታቸው ጋር ማዛመድ
- ስለአርበኝነት ጽንሰሀሳብ መግለጽ
- ለውሱን አላማ ማንበብ
- አርበኝነትን ማድነቅ
- የተረዱትን ለመግለጽ አይታዊ ወካይ ነገሮችን መፍጠር

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| • ያዳመጡትን መልእክት ከነባራዊ ህይወታቸው ጋር ማዛመድ | ማዳመጥ | • ቅድመ ማዳመጥ፡- የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ምሳሌ፡- አርበኝነት ምንድነው?<br>• በማዳመጥ ጊዜ፡- መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ<br>ምሳሌ፡- የአድዋ ድል<br>• ድህረ ማዳመጥ፡- ያዳመጡትን መልእክት ከህይወታቸው ጋር በማገናኘት መልመጃዎችን መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ምሳሌ፡- የሱሰኝነት ተጽእኖ ምንድነው? |
| • በተሰጠው ርእስ ላይ ከሌሎች ጋር መደራደር | ንግግር | • በተሰጠ ርእስ (አርበኝነት ጠቀሜታ) ላይ ከልሎች ጋረ መደራደርና መወያየት | • ተማሪዎች በአርበኝነት ላይ እንዲደራደሩ መጠየቅ ምሳሌ: የአድዋ ድል |
| ለተወሰነ አላማ ማንበብ | ንባብ | • ቅድመ-ንባብ፡- ተማሪዎችን ስለርእሱ መጠየቅ ምሳሌ፡- ስለአርበኝነት ምንታውቃላችሁ?<br>• በንባብ ጊዜ፡- ተማሮቹ ምንባቡን የተወሰነ አላማ ላይ በማተኮር ያነባሉ መምህሩ/ቷ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ድህረ ንባብ፡- ተማሪዎቹ ከምንባቡ የወጡ የመረዳት መልመጃዎችን ይሰራሉ<br>(ስእል የስረል ጋል) | • ተማሪዎቹ አርበኝነት የሚለውን ምንባብ በአሰሳ እንዲያነቡ መጠየቅ |
| ስለተሰጠ ስእል መግለጫ መጻፍ | ጽኀፈት | • ስለተሰጠ ስእል መግለጫ መጻፍ (ስለአድዋ ድል ከቀረበው)<br>• የቀረበን ገለጻ ከጓደኞቻቸው ጋር ማረም | ስለአረበኝነት የሚገልጽ ጽሁፍ አዘጋጁ |
| ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት | ቃላት | • ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት | • ተማሪዎች ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍች እንዲሰጡ መጠየቅ |
| ድብልቅ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ሰዋስው | • የቋንቋውን ስርአት ጠብቆ ድብልቅ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | • ተማሪዎች ድብልቅ አረፍተ ነገሮችን እንዲያስተካክሉ መጠየቅ |

ምእራፍ አስር ፡ **ቃላዊ ግጥሞች** (12 ክፍለ ጊዜ)

**የሚጠበቁ ውጤቶች፤**

ተማሪዎቹ የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ሳዳመጡት ምንባብ መልእክት ትርጉም መስጠት
- ስለቃላዊ ግጥሞች ጽንሰሀሳብ ማግለጽ
- ስለቃላዊ ገጥም አይነቶች መግለጽ
- ግጥምን በተገቢው ቅላጼ ማንበብ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ማዳመጥና የተረዱትን መልእክት መተርጎም | ማዳመጥ | • **ቅድመ ማዳመጥ፡-** የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚፈትሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ምሳሌ፡-** ቃላዊ ግጥም ምንድነው?<br>• **በማዳመጥ ጊዜ፡-** መምህሩ ወይም ተማሪው የተሰጠውን አጭር ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ መያዝ<br>**ምሳሌ፡-** አጭር ግጥም<br>• **ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን መልእክት ከህይወታቸው ጋር በማገናኘት መልመጃዎችን መስራት | • ካዳመጡት ነገር ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• ምሳሌ፡- የቃላዊ ግጥሙ መልእክት ምንድነው? |
| • ያዳመጡትን ቃላዊ ግጥም የሚመስል ማቅረብ | ንግግር | • ማዳመጥና ያዳመጡትን ቃላዊ ግጥም የሚመስል ማቅረብ | • ተማሪዎች ያዳመጡትን ቃላዊ ግጥም የሚመስል እንዲያቀርቡ |
| ግጥምን በተገቢ ቅላጼ ማንበብ | ንባብ | • **ቅድመ-ንባብ፡-** ተማሪዎችን ስለርእሱ መጠየቅ<br>**ምሳሌ፡-** ስለቃላዊ ግጥም ምን ታውቃላችሁ?<br>**በንባብ ጊዜ፡-** ተማሮቹ ምንባቡን በተገቢው ቅላጼ ማንበብ ያነባሉ<br>መምህሩ/ሯ በየደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• **ድህረ ንባብ፡-** ተማሪዎቹ ምንባቡን በተገቢው ቅላጼ የማንበብ መልመጃ ይሰራሉ<br>(ተጨማሪ ቃላዊ ግጥሞች ያስፈልጋሉ) | • ተማሪዎቹ ቃላዊ ግጥም እንዲያነቡ መጠየቅ |
| ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥሞችን መጻፍ | ጽኁፈት | • ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥሞችን ይጽፋሉ<br>• ተማሪዎቹ ከጓደኞቻቸው ጋር ቃላዊ ግጥሙን ይተረጉማሉ | • ተማሪዎቹ ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥሞችን እንዲጽፉ መጠየቅ |
| በተለዋጭ ዘይቤ የቀረቡትን ቃላት መግለጽ | ቃላት | • በተለዋጭ ዘይቤ የቀረቡትን ቃላት መግለጽ | • ተማሪዎች በተለዋጭ ዘይቤ የቀረቡትን ቃላት ትርጉም እንዲገልጹ መጠየቅ |
| በጽሁፍ ውስጥ አያያዥ ቃላትን መጠቀም | ሰዋስው | • አያያዥ ቃላትን ተጠቅሞ ድርብ አረፍተነገር መጻፍ | • ተማሪዎቹ በምንባብ ውስጥ ያሉ አያያዥ ቃላትን እንዲለዩ መጠየቅ |